# አዲስ ዘመን

እሁድ 82ኛ ዓመት ቁጥር 211 ሚያዝያ 1 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!






# “ጠንካራ ሃገር ያለጠንካራ ሠራዊት ሊጸና አይችልም”

-ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡-የኢትዮጵያ ሕልም የተፈራች እና የተከበረች ሀገር እንድትኖር የሚያደርግ ሠራዊት መገንባት ነው ሲሉ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር እና የጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ተናገሩ።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በሁርሶ ሰላም ማስከበር ኮንቲንጀንት ትናንት በተካሄደው የመስመራዊ መኮንኖች የምረቃ መርሐ-ግብር ላይ ተገኝተው ባስተላለፉት መልዕክት፣ “የኢትዮጵያ አይበገሬነት ማሳያ እናንተ ናችሁ፤ ኢትዮጵያ በጀግንነትም በታታሪነትም የምትጠራ፣ ለሚበልጥ ሥራ የምትተጋ ሀገር ናት፤ ይህችን ሀገር ማገልገል መመረጥ ነው” ብለዋል።

ጠንካራ ሃገር ያለጠንካራ ሠራዊት ሊፀና አይችልም ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ወታደር ሁልጊዜም ወታደራዊ ዝግጁነቱን የጠበቀ፣ ታታሪ፣ ደፋር እና እርግጠኛ ሆኖ ሀገሩን የሚጠብቅ ሊሆን ይገባዋል ሲሉም አስገንዝበዋል።

የኢትዮጵያ ሕልምም የተፈራች እና የተከበረች ሀገር እንድትኖር የሚያደርግ ሠራዊት መገንባት ነው ብለዋል። ጀግንነት ለሚበልጥ ዓላማ ራስን አሳልፎ መስጠት ነው ሲሉም ለተመራቂዎቹ ሀገርን በጀግንነት እንዲያገለግሉ መመሪያ ሰጥተዋል።

በሁርሶ ሰላም ማስከበር ኮንቲንጀንት የመስመራዊ መኮንነት ትምህርታቸውን ሲከታተሉ የነበሩ ከአንድ ሺህ 100 በላይ የሚሆኑ ዕጩ መኮንኖች ትምህርታቸውን በአግባቡ አጠናቅቀው በምክትል መቶ አለቃነት ተመርቀዋል።




# “እንደ ሀገር ከተጀመረው የለውጥ ጉዞ ጋር የሚጣጣም የኮሙኒኬሽን ሥራ ያስፈልጋል”

- ለገሰ ቱሉ (ዶክተር)
  የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር

**ጌትነት ተስፋማርያም**

አዳማ፡-እንደ ሀገር ከጀመርነው የለውጥ ጉዞ ጋር የሚጣጣም የኮሙኒኬሽን ሥራ ያስፈልጋል ሲሉ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር ዶክተር ለገሰ ቱሉ (ዶክተር) ገለጹ።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የሥልጠና ማዕከል ከመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ጋር በመተባበር

“እንደ ሀገር ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



# “ኢፍጣራችን ለወገናችን”

## የጎዳና ላይ ኢፍጣር መርሐ ግብር ተካሄደ

ገጽ 4

- ሼህ ሐጂ ኢብራሂም

# "ሪፎርሙ የክልል ልዩ ኃይልን በምርጫቸው ወደ መከላከያ፣ፌዴራል እና መደበኛ ፖሊስ እንዲገቡ የሚያደርግ ነው"

- ጄኔራል አበባው ታደሰ
  የጦር ኃይሎች ምክትል ጠቅላይ ኤታማዦር ሹም

**መዓዛ ማሞ**



አዲስ አበባ፡- እየተተገበረ ያለው ሪፎርም የክልል ልዩ ኃይል ክብርን፣ሞራልን እና ጥቅምን በማይነካ መልኩ በራሳቸው ምርጫ ወደ መከላከያ፣ፌዴራል እና መደበኛ ፖሊስ እንዲገቡ ማድረግ እንደሆነ የጦር ኃይሎች ምክትል ጠቅላይ ኤታማዦር ሹም ጄኔራል አበባው ታደሰ ገለጹ።

የጦር ኃይሎች ምክትል ጠቅላይ ኤታማዦር ሹም ጄኔራል አበባው ታደሰ በወቅታዊ ጉዳይ ላይ ከኢትዮጵያ

“ሪፎርሙ የክልል ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



# ብቁ የጨርቃጨርቅ ባለሙያዎችን ለማፍራት የሚያስችል ስምምነት ተፈረመ

**ማሕሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ፡ የሥራና ክህሎት ሚኒስቴርና የቻይናው ኦሪየንት ኢንተርናሽናል ሆልዲንግ ካምፓኒ ጋር የተደረገው ስምምነት በኢትዮጵያ የሚገኙ የጨርቃጨርቅ ባለሙያዎችን ለማፍራት ትልቅ ሚና እንዳለው ተገለጸ።

የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር የቴክኒክና ሙያ ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር ተሻለ በሬቻ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤታቸው የጨርቃጨርቅ አምራች ከሆነው ከቻይናው ኦሪየንት ኢንተርናሽናል ሆልዲንግ ካምፓኒ ጋር ትናንትና የስምምነት ፊርማ ሲፈራረሙ እንደተናገሩት፤ የተደረገው ስምምነት በኢትዮጵያ የሚገኙ ብቁ የጨርቃጨርቅ ባለሙያዎችን ለማፍራት ትልቅ ሚና አለው። ይህም ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ እድገትም ትልቅ አቅም ይሆናል።

በኢትዮጵያ የኢኮኖሚ እድገት ትልቅ አስተዋጽኦ እያደረገ ባለው የጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ብቁ የሆኑ ባለሙያዎችን ማፍራት ወሳኝ ነው ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ለዚህም የተደረገው ስምምነት በኢንዱስትሪው የሰለጠነ የሰው ሀብት በማፍራት ረገድ አስፈላጊ ነው ብለዋል፡፡

በዚህ ስምምነትም በሀገር ውስጥ ሥልጠና ከመስጠት ባለፈ ከ100 በላይ ለሚሆኑ ኢትዮጵያውያን ወደ ቻይና ሀገር ሄደው ሥልጠና እንደሚወስዱ ቃል ተገብቷል። ይህም ሠልጣኞቹ ዓለም አቀፍ ብቃት እንዲኖራቸው ከማድረግ ባለፈ የቴክኖሎጂና የእውቀት ሽግግር በማድረግ ለሀገሪቱ የጨርቃጨርቅ ዘርፍ ዕድገት ትልቅ ሚና እንደሚጫወት ተናግረዋል።

በቀጣይ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ከድርጅቱ ጋር በመሆን በተወሰኑ ፖሊ ቴክኒክ ተቋማት በጋራ የሥልጠና ማዕከል በማቋቋም በሚፈለገው ልክ ለማሠልጠን ፍላጎት እንዳላቸው ገልጸዋል።



የኦሪየንት ኢንተርናሽናል ሆልዲንግ ሊቀመንበር ቶንግ ጂሸንግ በበኩላቸው ስምምነቱ በኢትዮጵያ ያለውን የጨርቃጨርቅ ባለሙያዎችን የማሠልጠንና ብቁ ማድረግ ዓላማ ያለው ነው ብለዋል።

የቻይና የመንግሥት የልማት ድርጅት የሆነው ሻንግቴክስ የጨርቃጨርቅ ድርጅት በኢትዮጵያ ከዓመታት በፊት ቦሌ ለሚ ኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ የጨርቃጨርቅ ፋብሪካ ከፍቶ ከ3ሺህ 500 በላይ ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ እድል ፈጥሯል። በቀጣይም ከ4 ሺህ በላይ ተጨማሪ ዜጎችን ለመቅጠር እንዲሁም በዘርፉ ሥልጠና ለመስጠት ከቴክኒክና ሙያ ተቋማት ጋር እንደሚሠራም ገልጸዋል።

ካምፓኒው ባለፈው ዓመት ከአንድ ነጥብ 5 ሚሊዮን የጨርቃጨርቅ ምርቶች ለውጭ ገበያ እንዳቀረበ ገልጸው፤ በዚህ ዓመትም ከ4 ሚሊዮን በላይ ዋጋ ያላቸው የጨርቃጨርቅ ምርቶችን ለማምረትና ለውጭ ገበያ ለማቅረብ እየተሠራ መሆኑ እንደሆነ ተመላክቷል። በቀጣይም ዘርፉ የሚያስፈልውን ብቁ ባለሙያ ለማፍራት እና የሥራ ዕድል ለመፍጠር እንደሚሠሩም ሊቀመንበር ቶንግ ተናግረዋል፡፡

# የቦረናን የውሃ ጥም ያስታገሰው የፊና ምርባቴ ግድብ

**አስቴር ኤልያስ**

እግር ጥሎት ከሰሞኑን ወደ ቦረና ዞን ያቀና ሰው፣ አካባቢው ለምልሞ ስለሚያይ ሲወራ የነበረው ድርቅ የቱጋር ነበር ማለቱ አይቀሬ ነው። ከያቤሎ ከተማ 30 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በፊና ኦሮሚያ ወደተገነባው የፊና ምርባቴ ግድብ ፕሮጀክት ባቀናንበት ወቅት በግራና ቀኝ የሚታየው ተክል ከልምላሜው የተነሳ አካባቢውን በአረንጓዴ ቀለም የተሸለመ አስመስሎታል ። ወደ ግድቡ ስንቃረብ ደግሞ በርቀት ተንጣሎ የሚታየው ውሃ በተወሰኑ ቀናት ዝናብ የተያዘ አይመስልም።

የፊና ምርባቴ ግድብ ፕሮጀክት ኦፊስ መሐንዲስ ኢንጂነር ዋቅጂራ ቢረሳ እንደሚሉት፤ የፊና ምርባቴ ግድብ ፕሮጀክት በቦረና ካሉት ፕሮጀክቶች ውስጥ አንዱ ነው። በአሁኑ ወቅት ሥራው 96 በመቶ ደርሷል። ለማጠናቀቅም የሚቀረው የኮንክሪት ሥራ ብቻ ነው። ይህ ፕሮጀክት በዲዛይኑ መሠረት 2 ነጥብ 3 ሚሊዮን ሜትር ኪዩብ ውሃ መያዝ የሚችል ነው። ነገር ግን በአሁኑ ወቅት የያዘው 1 ነጥብ 5 ሚሊዮን ሜትር ኪዩብ ውሃ ነው፡፡

ፕሮጀክቱ ሲያልቅ ለ480 አባወራ ለመስኖ አገልግሎት መስጠት ይችላል። 120 ሔክታር መሬት ደግሞ ማልማት የሚያስችል አቅም አለው። ይህን ያህል ውሃ መያዝ የተቻለው በሁለት ቀን ዝናብ ብቻ ነው ያሉት ኢንጂነር ዋቅጂራ፣ ከዚህ በኋላ ቢዘንብ ደግሞ በተሠራለት ማስተንፈሻ በኩል እንዲወጣ እየተደረገ ቀጣይ መያዝ የሚችለውን ያህል ውሃ ለመያዝ እንደሚሠራ ይናገራሉ።

የፊና ምርባቴ ግድብ ፕሮጀክት በሁለት ሳምንት ውስጥ ይጠናቀቃል ተብሎ እንደሚጠበቅ የሚናገሩት የፕሮጀክቱ ኦፊስ መሐንዲስ፣ በዚሁ መሠረት አጠናቅቀው ለማስረከብ እንደሚያስቡም ነው የሚያስረዱት። በዚህ የግድብ ሥራ በስፍራው የሚገኘው አርብቶ አደር በእጅጉ ተባባሪያቸው እንደሆነ ጠቅሰው፤ አካባቢው ከዚህ ቀደም ድርቅ የሚያጠቃው አካባቢ በመሆኑም ውሃ ተይዞ በማየታቸው ደስታቸው ወደር እንደሌለው አመልክተዋል። በተለይ ለመጠጥ ውሃ አገልግሎት መዋሉና ለእንስሳቱም ያለምንም እንግልት ውሃ በቅርበት ማግኘት የሚያስችል በመሆኑ ተስፋቸው መለምለሙን ገልጸዋል፡፡

እርሳቸው እንደሚሉት፤ ከዚህ ቀደም እንዲህ አይነት ግድብ በወረዳውም ሆነ በዞኑ ባለመኖሩ ግድቡ ከተሠራ በኋላ የዞኑም ሆነ የወረዳው አመራር የአካባቢው ኅብረተሰብ በአግባቡ መጠቀም የሚያስችላቸውን ግንዛቤ ማስጨበጥ ይኖርባቸዋል። በመጀመሪያው ዋና ዓላማ በዝናብ አማካይነት የሚገኘውን ውሃ መያዝ ነው። በቀጣይ ደግሞ የዞኑም ሆነ የወረዳው አመራር ዘርፈ ብዙ አገልግሎት መስጠት እንዲችል ሥልጠናም ቢሰጥ የተሻለ ይሆናል፡፡

በቦረና ዞን የጎመሌ ወረዳ ዋና አስተዳዳሪ አቶ ቀላ ዴንጌ በበኩላቸው፤ የአርብቶ አደሩ ዋናው ችግር ውሃ መሆኑ የሚታወቅ ነው ይላሉ። በተለይ በቦረና አካባቢ ዘንድሮ የታየው የውሃ ችግር ከመቼውም ጊዜ ከፍ ብሎ እንደታየም ነው የሚናገሩት። አሁን ግን ግድቡ የውሃን ችግር በተለይ በወረዳዋ ላሉ አርብቶ አደሮች ፈትቷል ማለት እንደሚቻል ያስረዳሉ፡፡

እርሳቸው እየተገነባ ያለው የፊና ኦሮሚያ ምርባቴ ግድብ ፕሮጀክት ፋይዳው ብዙ ነው ይላሉ። በመጀመሪያ ደረጃ ለወረዳውም ሆነ ለዞኑ አዲስ ሥራ መሆኑ ተጠቃሽ እንደሆነ ገልጸው፤ በወረዳቸው እየተገነባ ያለው ምርባቴ ግድብ ለመጠጥ ውሃነት ፣ ለመስኖ ሥራ ብሎም ለዓሣ ርባታ እንደሚሆን ነው የሚናገሩት። ከዚህ አንጻር የወረዳው ሕዝብ በተለይ ለአባወራዎች አጫጭር ሥልጠና እና ግንዛቤ እንዲያገኝ እንደሚደረግ ይጠቅሳሉ፡፡ከዚሁ ጋር ተያይዞ ከግድቡ በስተጀርባ ሊለማ የተዘጋጀ መሬት በመኖሩ ወደልማት ሥራ እንደሚገባ ያመለክታሉ፡፡

በጎመሌ ወረዳ፣የአቡኑ ቀበሌ ነዋሪ የሆኑት አርብቶ አደር በኩ ሊበን፣ ከዚህ ቀደም ለተከታታይ አራት ዓመታት ዝናብ ባለመዘነቡ ውሃ የሚባል ነገር ለዓይናችን ናፍቆን ቆይቷል ይላሉ። ከብቶቻችን የሚበሉት አጥተው ምንም እንኳ በሕይወት ለመኖር ባያስችላቸውም በአካባቢው ከተገኘው ግራር ልጣጩን እየገፈፉ ለመብላት ሲሞክሩ ነበር በማለት ይናገራሉ። በተለይም የከብቶቻችንን ሕይወት ለማቆየት ስንል ገሚሱን እንስሳት ሸጠን ጭድም ፉርሽካም ለመግዛት ሞክረን ነበር፤ ነገር ግን ለተወሰነ ጊዜ ብቻ እንዲቆዩ ከማድረግ የዘለለ ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስ ስላቃታቸው ፋይዳ እንዳልነበረው ነው የገለጹት።

አሁን ግን የዚህ የግድብ ውሃ ተስፋ ሰጥቶናል ይላሉ። ለራሳቸውም የመጠጥ ውሃ፣ ለከብቶቻቸውም መጠጥነት እንዲሁም ለመስኖ እንደሚገለገሉበት ይናገራሉ። አርብቶ አደሩ የነበሯቸው ከብቶች በሙሉ አልቀው ባዶ እጃቸውን የቀሩ መሆናቸውን ተናግረው፤ ይህ ግድብ ግን ከፍ ያለ ደስታ የፈጠረላቸው በመሆኑ እንደገና መነሳት ይቻላል ብለዋል፡፡

ሌላኛው የዚያው ቀበሌ ነዋሪ ወጣት አርብቶ አደር ዱባ ቀንጮራ በበኩሉ፤ በግድብ ሥራው ላይ የሥራ እድል የተፈጠረለት ወጣት ነው። ወጣቱ፣ የኦሮሚያ ክልል መንግሥትን ማመስገን እንደሚፈልግ ተናግሮ፤ በተለይ እርሱ በሚኖርባት ቀበሌ እንዲህ አይነት ፕሮጀክት በመሠራቱ የቀን ገቢ ማግኘት ከመቻሉም በላይ ውሃው ትልቅ ተስፋን ይዞ መምጣቱን ተናግሯል። እንስሳቶቻቸው ከዚህ ቀደም መሬቱን በመቆፈር በብዙ ሜትር ርቀት የምትገኘዋን ውሃ እንደሚጠጡ ጠቅሶ፤ አሁን እሱ ችግር መቀረፉን ነው ያመለከተው።

# “ልዩ ኃይልን መልሶ ማደራጀት የሕዝብን ሠላምና ደኅንነት በአስተማማኝ ሁኔታ ለማረጋገጥ ያስችላል”

-የክልል የጸጥታ ኃላፊዎች

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- ልዩ ኃይልን መልሶ ማደራጀት የሕዝብ ሠላምና ደኅንነትን በአስተማማኝ ሁኔታ ለማረጋገጥ ያስችላል ሲሉ የክልሎች የጸጥታ ኃላፊዎች አስታወቁ፡፡

የክልል ልዩ ኃይልን በአዲስ መልክ ለማደራጀት በተዘጋጀው የማስፈጸሚያ እቅድ ላይ የመከላከያ ሠራዊት ከፍተኛ አመራሮች፣ የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽነሮችና የክልል ፖሊስ ኮሚሽነሮች ትላንት ውይይት አካሂደዋል። የክልሎች ፀጥታ ኃላፊዎች ከወይይቱ በኋላ በሰጡት መግለጫ፣ ልዩ ኃይልን መልሶ ማደራጀቱ ሃገራዊ ራዕይ ያለውን የፀጥታ መዋቅር ከመገንባት ባሻገር የሕዝብ ሠላምና ደኅንነትን በአስተማማኝ ሁኔታ ለማስፈን እንደሚያስችል አስታውቀዋል።



ኮሚሽነር አሊ ዲኒ



ደሳለኝ ጣሰው፤

የአፋር ክልል ፖሊስ ኮሚሽነር አሊ ዲኒ እንዳሉት፤ ልዩ ኃይል በአዲስ መልክ የሚደራጀው የሀገሪቷን የጸጥታ ኃይል ለማጠናከር ነው። ሕጋዊ መሠረት የሌለውን አደረጃጀት ወደ ሕጋዊ አደረጃጀት በማምጣት የሀገርን ራዕይ ተላብሶ የሕዝብን ሰላምና ደህንነት በአስተማማኝ ሁኔታ ለማስፈን ያስችላል፡፡

ልዩ ኃይል ስያሜው እንጂ የሃገራቱም ሆነ የክልሉ የፀጥታ አካል ሆኖ እንደሚቀጥል በመጥቀስ፤ በዚሁ ዙሪያ በክልሉ ካሉ አደረጃጀቶች ጋር ውይይት እየተደረገ እንዳለም ገልጸዋል። የሪፎርሙ አደረጃጀት ተግባራዊ ሲደረግ ሃገርን የሚያስከብር መዋቅር ለመገንባት ትልቅ ሚና ያለው መሆኑን ጠቅሰዋል።

የአማራ ክልል ሰላምና ጸጥታ ቢሮ ኃላፊ ደሳለኝ ጣሰው፤ ልዩ ኃይልን መልሶ የማደራጀቱ ሥራ በጥናት ላይ የተመሠረተ መሆኑን ገልጸዋል። ከዚህ ቀደም በሃገሩና በክልሉ የነበሩ ጉዳዮችን ግምት ውስጥ ያስገባ ከሁለት ዓመታት በላይ የወሰደ ጥናት ተጠንቶ በሀገሪቷ ምን አይነት የፀጥታና ሕግ አስከባሪ ተቋም መገንባት አለበት የሚል ውይይት ተደርጎ ሃገርን ሊያሻግርና ሊናበብ የሚችል የሕግ አስከባሪ አካላት መገንባት አለባቸው ተብሎ ስምምነት ላይ መደረሱንም አንስተዋል። በተፈጠሩ ሃገራዊ ሁኔታዎች ምክንያት ጊዜ ተወስዶ ዛሬ ላይ ደረሰ እንጂ አዲስ ነገር እንዳልሆነ ጠቁመዋል፡፡



ኮሚሽነር ጀነራል አራርሳ መርዳሳ

አዲሱ አደረጃጀት ዜጎች እኩል አመኔታ የሚጥሉበትና ሁሉንም የፀጥታ ኃይል የእኔ ነው የሚል ማኅበረሰብ እንዲፈጠርና አስተማማኝ ደኅንነት እንዲኖር ያደርጋል ብለዋል። የክልሉ ልዩ ኃይል ያበረከተው አስተዋፅዖ ሁልጊዜም ቢሆን ይዘከራል ያሉት የቢሮ ኃላፊው፤ ልዩ ኃይሉ ሃገርን ያስጠበቀና ታሪክን የሠራ መሆኑን እውቅና ሰጥተዋል። የተጀመረው የመልሶ ማደራጀትም ይህንኑ በማጠናከር ለበለጠ ሃገራዊ ተልዕኮ የሚያዘጋጅ እንደሆነ ገልጸዋል።



ጠይብ አህመድ

እንደ እርሳቸው ገለጻ፤ አንዳንድ ወገኖች የልዩ ኃይሉን አደረጃጀት ወደሚፈለግበት ሀገራዊ መዋቅር ውስጥ ሆኖ ለተጨማሪ ተልዕኮ እንደሚደራጅ የተገለጸውን ከሁኔታዎች የተለየ ጥቅም እናገኛለን በማለት “ልዩ ኃይሉን አፈረሱት፣ ትጥቅ ሊፈታ ነው” የሚል ሐሰተኛ ወሬ ማናፈሳቸውን ተከትሎ መደናገር መፈጠሩን ጠቅሰዋል። ይህም በውይይትና በጋራ መግባባት ግልጽ ለማድረግ ተሞክሯል፡፡

የኦሮሚያ ክልል ፀጥታና አስተዳደር ቢሮ ኃላፊ ኮሚሽነር ጄነራል አራርሳ መርዳሳ፣ ልዩ ኃይሉ ተደራጅቶ ከበፊቱ የበለጠ አገልግሎት እንዲሰጥ ይደረጋል በማለት፣ መልሶ የማደራጀት ሥራው ሕገ መንግሥታዊ አሠራርን ተከትሎ የሚከናወን እንደሆነ ጠቅሰዋል። ይህንን ተግባራዊ ለማድረግም በክልሉ ባሉ የተለያዩ መዋቅሮች ስምምነት ላይ መደረሱን ገልጸዋል። መልሶ ማደራጀቱም የሕዝብን ደኅንነት የበለጠ ለማጠናከር ያግዛል ብለዋል።

የሶማሌ ክልል የጸጥታ ዘርፍ ቢሮ ኃላፊ ጠይብ አሕመድ በበኩላቸው፣ ሪፎርም ሁልጊዜም በተቋማት ደረጃ እንደሚተገበር ጠቁመው፣ ልዩ ኃይልን መልሶ የማደራጀት ሪፎርምም ኃይሉን የመበተን ሳይሆን ለጠንካራ ተልዕኮ ማዘጋጀት እንደሆነ ተናግረዋል። በክልል ደረጃ ውይይት ተደርጎ ስምምነት ላይ እየደረስን ነው ብለዋል።

ልዩ ኃይሉ መልሶ ሲደራጅ እንደ ፍላጐቱና እንደ ሀገር የፀጥታ መዋቅር በተቀመጠው መመዘኛ አማካኝነት የመከላከያ ሠራዊት፣ የፌዴራል ፖሊስና መደበኛ ፖሊስ ሆኖ ሀገርን በበለጠ እንዲያገለግል ይደረጋል ሲሉ ነው የፀጥታ ኃላፊዎች የገለጹት።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ትልቁን የሃገር መከታ በማጠናከሩ ሂደት ሁሉም አካል የሚጠበቅበትን ይወጣ!

አንድ ሀገር ታላቅ እና ሉዓላዊ ከሚያስብሏት አቅሞች መካከል አንዱ እና ቀዳሚው የመከላከያ እና ደህንነት ኃይሏ ተቋማዊ አቅም ነው:: በዚህ ረገድ የበለጸጉትም ሆኑ ያደጉ ሃገራት ኢኮኖሚያዊ ግስጋሴያቸው በውስጥም ሆነ በውጪ የሚመጡ ትንኮሳዎችና ወረራዎችን ተቋቁሞና አሸንፎ እንዲቀጥል ማድረጊያ ዋና መሣሪያ አድርገው የሚጠቀሙትና ሲጠቀሙ የሚስተዋለው ይሄንኑ የመከላከያ እና ደህንነት ኃይላቸውን ነው:: ኢትዮጵያ በዚህ ረገድ ትልቅ ታሪክ ያላት ሀገር ብትሆንም፤በተለይ ባለፉት ሦስት እና አራት ዓመታት በዘርፉ እየተከናወኑ ያሉ የሪፎርም ሥራዎች ግን እጅጉን የሚያበረታቱና ተጨባጭ ውጤቶችን ያሳዩም ናቸው፡፡

የኢትዮጵያ ብሔራዊ የፀጥታ ኃይል የሪፎርም ሥራ መነሻ ያደረገው ደግሞ የሃገርን የግዛት አንድነትና ሉዓላዊነትና የሕዝቦችን ሰላምና ደህንነት ባስተማማኝ መሠረት ላይ ማጽናት መቻል ነው:: ይሄን ማድረግ የሚቻለው ደግሞ የሪፎርም ሥራው በሦስት መሠረታዊ ነገሮች ላይ ትኩረት ሲያደርግ ነው:: ከእነዚህ አንዱ ብሔራዊ የፀጥታ ኃይሉ የኢትዮጵያዊነት አስተሳሰብን የተላበሰ እና በኢትዮጵያዊነት መንፈስ የተገነባ ሆኖ ለሁሉም ሕዝብ እኩል አለኝታና መከታ የሆነ ኃይል ማድረግ ሲቻል ነው:: ሁለተኛው፣ የግዛት አንድነትን የሚያስጠብቅ አቅምና ችሎታን መፍጠር ነው:: ሦስተኛው፣ የተሟላ ትጥቅ እንዲኖረው እና በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ ማድረግ፤ እንዲሁም ዘመናዊ አሠራርና አካሄድን መከተል ነው፡፡

ኢትዮጵያዊነትን ከችሎታ፣ ችሎታን ከትጥቅ አቅም እና ከቴክኖሎጂ ጋር ያዳመረ እና በዘመናዊ አሠራርና አካሄድ የሚመራ ብሔራዊ የጸጥታ ኃይል መፍጠር ማለት ደግሞ፤ ከውስጥ የሚነሱ ችግሮችን መግራት፣ ከውጭ የሚቃጡ ጥቃቶችንም መከላከል የሚያስችል ሃገራዊ አቅም መፍጠር ማለት ነው:: ምክንያቱም ኢትዮጵያ በአንድ በኩል አካባቢያዊ ስጋት አለባት፤ በሌላ በኩል መልኩን እየቀያየረ የሚከሰተው ዓለም አቀፋዊ ሁኔታ የሚያሳድርባት ተጽዕኖ አለ:: በመሆኑም እነዚህን በልካቸው ተገንዝቦ ለመመከት የሚችል የፀጥታ ተቋም መገንባት ጊዜ የማይሰጠው ሥራ እንደመሆኑ ላለፉት አራት ዓመታት ይሄው ሲከናወን ቆይቷል፡፡

የጦር ኃይሎች ምክትል ጠቅላይ ኤታማዦር ሹም ጄኔራል አበባው ታደሰ ከትናንት በስቲያ በወቅታዊ ጉዳዮች ላይ በሰጡት ቃለ ምልልስ ያስረዱትም ይሄንኑ ሐቅ ነው:: ጄኔራሉ በማብራሪያቸው እንዳስቀመጡት፤ የሪፎርም ሥራው ሲጀመር ታሳቢ ያደረገው አንደኛው ጉዳይ የሕዝቦችን ሰላም ማረጋገጥ እና የተጀመረው ሃገራዊ የልማት ጉዞ በሰላም እንዲራመድ ማስቻል ነው:: ለዚህ ደግሞ በሕዝቦች ሰላምም ሆነ በልማት ጉዞው የተጋረጡ ፈተናዎችን ከመለየት አንስቶ ሥራውን ከውስጥ መጀመር ተገቢነት ነበረው:: ይሄ ሥራ ደግሞ ዝም ብሎ የሚከናወን አይደለም፤ ይልቁንም ሕገ መንግሥቱን መነሻ በማድረግ እንጂ:: በሕገ መንግሥቱ መሠረት የፌዴራል መንግሥቱ የመከላከያ ሠራዊትን ጨምሮ የደህንነት እና የፖሊስ ተቋማትን የማደራጀት ኃላፊነት ተሰጥቶታል:: በአንጻሩ ክልሎች የክልል መደበኛ ፖሊስ የማደራጀትና የክልሉን ሰላምና ፀጥታ የማስጠበቅ ኃላፊነት ተሰጥቷቸዋል፡፡

በኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ግን ክልሎች ከመደበኛ ፖሊስ በዘለለ ልዩ ፖሊስ ማቋቋማቸው የታወቀ ነው:: ይሄ ምንም እንኳን ከሕገ መንግሥቱ ድንጋጌ ውጪ ቢሆንም፤ እነዚህ የክልል ልዩ ኃይሎች በተለያዩ ጊዜያት ሃገር ችግር ላይ በሆነች ወቅት ከመከላከያ ሠራዊቱ ጎን ሆነው ተዋድቀዋል፤ የሃገርንም ሉዓላዊነትና ክብር አስጠብቀዋል:: ይሄ ደግሞ ለእነዚህ ኃይሎች የፈጠረላቸው አቅምና ችሎታ መኖሩ እሙን ነው:: ይሄ አቅም ደግሞ መባከን ስለሌለበትና እነዚህ ኃይሎች የብሔራዊ የጸጥታ ኃይሉ የሪፎርም አካል እንዲሆኑ ማድረግ ተገቢነት ያለው በመሆኑ የክልል ልዩ ኃይሎችን መልሶ ወደማደራጀት ተግባር ተገብቷል፡፡

ይሁን እንጂ ይሄ ሃገራዊ አቅም የመፍጠር እና የኢትዮጵያን ሉዓላዊነትም ሆነ የኢትዮጵያውያንን ሰላምና ደህንነት በአስተማማኝ መሰረት ላይ የማጽናት ጉዞ ያልተዋጠላቸውና ሆን ብሎ ለማወናበድ የሚፈልጉ አካላት፤ ስለሂደቱ የተዛባ መረጃ በመልቀቅ ድብቅ ዓላማቸውን ለማሳካት ሲጥሩ ይታያል:: ይህ ግን ፈጽሞ ተቀባይነት የሌለው በመሆኑም ሕዝብ ድበቅ ዓላማቸውን ሊረዳና እንዲታቀቡ ሊያደርግ ይገባል፡፡

ምክንያቱም የሪፎርሙ መሠረታዊ መነሻ የሀገርን የግዛት አንድነትና ሉዓላዊነት ማስጠበቅን፤ የዜጎች ሰላምና ደህንነት ተረጋግጦ ሕዝቦች ያለ ስጋት ወጥተው የሚገቡባትን ሃገር እውን ማድረግ ነው:: ይሄ ደግሞ ታስቦ የሚቀር ሳይሆን የሚፈጸም ነው:: በምንም ዓይነት እንቅፋትም ወደኋላ የማይመለስ ተግባር ነው:: ዘርን ተገን ያደረገ አካሄድ፣ የፀጥታ መዋቅር፣ የሃይማኖት እሳቤ፣ ሌብነትና ሌሎችም ለተጀመረው የግዛት አንድነት፣ ሰላምና ይሄን ማዕከል አድርገው የሚንቀሳቀሱ ኃይሎችም ከኪሳራ ውጪ ለድል ስለማይበቃቸው አደብ ሊገዙ ይገባል:: መላው ሕዝብ፣ የጸጥታ ኃይሉ እና ፖለቲከኞችም ይሄንኑ ተገንዝበው በሪፎርሙ አንድ ጠንካራ ብሔራዊ የጸጥታ ኃይል የመፍጠሩን ሂደት ማፋጠንና ለውጤታማነቱም የድርሻቸውን ማበርከት ይኖርባቸዋል!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

## የሽግግር ፍትሕ ሂደቱ ሲመራባቸው የሚገቡ መርሆዎች እና የማስተባበር አደረጃጀት አማራጮች

**የሽግግር ፍትህ ሂደቱ ሲመራባቸው የሚገቡ መርሆዎች**

በሀገራችን የሚታሰበው የሽግግር ፍትሕ ሂደት የሚከተሉትን መርሆዎች ባማከለ መልኩ የሚቀየስ እና የሚተገበር መሆን ይኖርበታል።

**1-1 ሀገራዊ ባለቤትነትን ማረጋገጥ፡**

የሽግግር ፍትሕ ሂደት በመሠረቱ አንዲት ሀገር በራሷ ለራሷ ተግባራዊ የምታደርገው ፍፃሜ ነው። ሂደቱ ሊመራ የሚገባው በራስ ተቋማት እና ዜጎች ነው። ይህም የሀገር ሉዓላዊነት መርሕን በመጠበቅ የብሔራዊ ኩራት መገለጫ ጭምር ሆኖ እንዲታይ ያደርገዋል፡ ቀጣይት ላለው የሕግ የበላይነት እና ዘላቂ ተቋማዊ ግንባታም መሠረት የሚጥል ይሆናል።

**ዐውድ-ተኮር ፤**

የሽግግር ፍትሕ አቀራረጽ እና አተገባበር ከማኅበረሰብ የፍትሕና እርቅ እሳቤዎችና ፍላጎቶች የፈለቀ፣ ዐውዳዊ ልዩ ሁኔታዎችን ያገናዘበ መሆን ይኖርበታል። በተጨማሪም በተጋለጠ ሁኔታ ውስጥ ያሉ ሴቶችና ሕጻናት እንዲሁም ሌሎች አካላት ያሉበትን ሁኔታ ጨምሮ የግጭቱን ባሕሪና ያስከተለውን የሙብቶች ጥሰት ይዘት ያገናዘበ መሆን ይኖርበታል።

**የሕዝብ ተሳትፎን ማረጋገጥ ፤**

የሽግግር ፍትሕን ለመተግበር የሚደረግ የትኛውም ዓይነት ተቋማዊ አደረጃጀት የሕዝብ ተሳትፎ እና ሕጋዊነትን፣ የሂደቱን ነፃነት፣ ገለልተኝነት፣ ብቃት፣ አካታችነት፣ ውጤታማ እና ቀልጣፋ ክዋኔ፡ በቂ የሃብት ክፍፍልን፡ እና የሥልጣን ግልፅነትን እና በቂነትን መሠረት ያደረገ መሆን አለበት።

**አካታችነት ፤**

የሽግግር ፍትሕ ሂደት በሁሉም ምዕራፎች ሁሉንም አካላት በእኩልነትና በፍትሐዊነት ሊያሳትፍ ይገባል። እንዲሁም እንደ ሴቶችና ልጃገረዶች፣ አረጋውያን፣ አካል ጉዳተኞች እና ወጣቶች ያሉ የተገፉ፡ የተገለሉና ተጋላጭ የሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ልዩ ሁኔታና ፍላጎት መሠረት ያደረገ መሆን ይኖርበታል፡፡

**የተቀናጀ አተገባበር ፤**

በተጨማሪም ሂደቱ የተለያዩ የሽግግር ፍትሕ ስልቶች እና መንገዶችን በማቀናጀት በተናበበ መልኩ ለመተግበር እና ውጤት ለማስገኘት የሚያስችል ሊሆን ይገባል:: አንዱን የሽግግር ፍትሕ ዘዴ ብቻ ተግባር ላይ ማዋል ወይም የተለያዩ መንገዶችን ሳያቀናጁ በሥራ ላይ ማዋል የተሳካ ውጤት እንዳይገኝ ያደርጋል።

በተጨማሪም ቁጭቶችን እና ጥያቄዎችን በመፍጠር ከሚያስገኘው ጥቅም ይልቅ ጉዳቱ ያመዝናል። ስለሆነም የተሳካ የሽግግር ፍትሕ ሂደት በሀገራችን እንዲኖር ካስፈለገ አንዱ የሽግግር ጊዜ ፍትሕ መንገድ ሌላውን የሚተካ ሳይሆን፡ ሁሉም የሚደጋገፉ እና የሚመጋገቡ መሣሪያዎች እንደሆኑ በመገንዘብ፣በመደጋገፍ እና በትብብር እንዲተገበሩ ማድረግ ያስፈልጋል።

**የሽግግር ፍትሕ ዓላማዎችን ቅደም ተከተል እና ሚዛን መጠበቅ፡**

የሽግግር ፍትሕ አማራጭ ሥልቶችን በማጣመር ለመተግበር የሚደረግ ውሳኔ በአንድ ወገን የሰላምና እርቅ፣ በሌላ ወገን የኃላፊነትና ተጠያቂነት ግቦችን እርስ በእርስ ለማጠናከር እና ተመጋጋቢነታቸውን ለማስጠበቅ፡ እንዲሁም አካታች እድገትን ለማምጣት ያለመ መሆን ይኖርበታል፡፡

**ገለልተኛነት ፤**

አሠራሩ በሽግግር ፍትሕ ሂደትና አተገባበር ላይ ተሳታፊ በሆኑ አካላት መካከል መተማመንን መገንባት የሚያስችል፡ ወገንተኛ ያልሆነ በዓላማና በመርሕ ላይ የተመሠረተ መሆን ይኖርበታል፡፡

**የማስተባበር አደረጃጀት አማራጮች ፤**

በኢትዮጵያ ለሚተገበረው የሽግግር ፍትሕ ሂደት ከላይ ከተቀመጡት የትኛውንም አማራጭ ብንከተል ተግባራቶቹ ከአንድ በላይ በሆኑ ተቋማት መከናወናቸው አይቀርም:: አዲስ ኮሚሽን በማቋቋም የሽግግር ሂደቱን ማከናወን የሚለው አማራጭ በክፍል ሁለት በተደጋጋሚ ቀርቧል:: ኮሚሽኑ አንዳንዶቹን ስልቶች በባለቤትነት የሚመራ፣ ሌሎች ተቋማትንም የሚያስተባብር እና የሚያቀናጅ ይሆናል። ስያሜው የሐቅ እና የእርቅ ኮሚሽን፣ ወይም የእርቅ እና የሰላም ኮሚሽን ወይም የእውነት እና እርቅ አፈላላጊ ኮሚሽን ወይም የሀቅ፣ የፍትሕ እና የእርቅ ኮሚሽን ሊባል ይችላል።

ይህም ተቋቁሞ ከነበረው የእርቀ ሰላም ኮሚሽን ትምህርት በመውሰድ እና ዓለማቀፍ ልምዶችን ግምት ውስጥ በማስገባት - በሕግ የሚሰጡትን ሥልጣን እና ኃላፊነቶች መወጣት የሚችል ተቋም ማደራጀትን ይጠይቃል::

ይሁንና ይህ አዲስ ኮሚሽን የማቋቋም አማራጭ ተቀባይነት ቢያገኝ እንኳ ቢያንስ ክስ ከመመሥረት እና ከማካካሻ ሥርዓት አንፃር የመሪነት ሚና የሚጫወቱ ሌሎች ተቋማት ኃላፊነት ይኖርባቸዋል::

በመሆኑም እነዚህን ተግባራት የማቀናጀት እና የማስተባበር ተግባር የሚቀር አይደለም:: ስለሆነም ስኬታማ እና የተሟላ ሂደት እንዲኖር ለማድረግ በሂደቱ ኃላፊነት ያለባቸውን ተቋማት ለማስተባበር የሚያስፈልገውን አደረጃጀት መተለም ያስፈልጋል:: ስለሆነም ፖሊሲውን በባለቤትነት የሚያስፈፅም እና በአተገባበሩ ላይ ክትትል የሚያደርግ ብሔራዊ የሽግግር ፍትሕ አስተባባሪ ቦርድ (ምክር ቤት) ማቋቋም አስፈላጊ ይሆናል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በተጠቀሰው የማስተባበር አደረጃጀት ላይ አዲስ አቅም በማቆም ከላይ ከተቀመጡት ሁለት ተቋማዊ አማራጮች ጠንካራ ጎኖች እና ስጋቶችን በማቀናጀት የተለየ አደረጃጀት የሚፈጠርበት እድል ሊኖር ይችላል:: ይህ አማራጭ የሚከተለው መልክ ይኖረዋል፡፡

**ብሔራዊ የሽግግር ፍትሕ አስተባባሪ ቦርድ (ምክር ቤት) ማቋቋም ፤**

ተቋሙ የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲውን በባለቤትነት የማስፈፀም እና በፖሊሲው መሠረት ተቋማት ተግባሮቻቸውን ማከናወናቸውን የማረጋገጥ ኃላፊነት ይኖርበታል:: እንደ አግባብነቱ ተመሳሳይ አደረጃጀቶች በክልል ደረጃም ሊቋቋሙ ይችላሉ:: አባላቱም በፖሊሲው ላይ የተጠቀሱ ተግባራትን ለመፈፀም፣ ለመቆጣጠር ወይም ለመደገፍ ኃላፊነት ካለባቸው ተቋማት የተወከሉ እንዲሁም በነፃና አሳታፊ ሂደት ከባሕላዊ አደረጃጀቶች እና ከኅብረተሰቡ የሚመረጡ ሰዎች ይሆናሉ፡፡

ዝርዝር ጉዳዩ በሕግ የሚወሰን ቢሆንም የሚፈጠሩ አዲስ ተቋማትን ጨምሮ በውክልና የሚመደቡት የቦርዱ አባላት ከሚከተሉት ተቋማት የሚወከሉ ሊሆኑ ይችላሉ :: ከሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ ከፌዴራል ፍርድ ቤቶች፣ ከፍትሕ ሚኒስቴር፣ ከፌዴራል ፖሊስ፣ ከኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን፣ ከብሔራዊ ምክክር ኮሚሽን፣ ከባሕላዊ ሥርዓቶች፣ ከታዋቂ ሰዎች፣ እና ከሀገር ሽማግሌዎች፡፡

ከኅብረተሰቡ የሚመረጡ አባላትን በሚመለከት - አዲስ ኮሚሽን ቢቋቋም አባላትን በመመልመል ሂደት ሊኖር የሚችለው ነፃ እና ገለልተኛ አካሄድን በመከተል የሚሰየሙ መሆን ይኖርባቸዋል:: የኮሚሽኑ ሰብሳቢ እና የሚቋቋመው ሴክሬታሪያት ኃላፊነት በነዚህ አባላት የሚያዝ ይሆናል። የቦርዱ አባላት በሙሉ ተዓማኒነት እና መልካም ስብዕና ያላቸው፡ በኅብረተሰቡ ዘንድም የሽግግር ፍትሑ ባለቤቶች ተደርገው ሊሳሉ የሚችሉ መሆን ይኖርባቸዋል::

**ብሔራዊ የሽግግር ፍትሕ አስተባባሪ ቦርድ ሴክሬታርያት ፤**

አስተባባሪ ቦርዱ በሽግግር ፍትሕ ሂደቱ በተቋማቱ በቀጥታ የማይከናወኑ ተግባራትን የሚያከናውንበት እንዲሁም የማስተባበር ኃላፊነቱን የሚወጣበት በባለሙያዎች የተሟላ ሴክሬታሪያት ይኖረዋል:: አዲስ ኮሚሽን ከተቋቋመ ሴክሬታርያቱ በኮሚሽኑ ስር የሚደራጅ ይሆናል::

ይህ ካልሆነ ግን በሌሎች ሀገሮች ልምድ ለኮሚሽኖች የሚሰጡ እንደ እውነትን ማጣራት፣ ምሕረት፣ የእርቅ ሂደቶች እና የማካካሻ ሂደት ጉዳዮች ላይ ሴክሬታርያቱ መመሪያዎችን ያዘጋጃል፣ እንደ አግባብነቱ ይፈፅማል፣ተግባራቱ በሌሎች ተቋማትም ትኩረት ተሰጥቷቸው እንዲፈፀሙ የማድረጊያ አቅም ይሆናል።

**ምንጭ /ኢትዮጵያ የሽግግር ፍትህ የፖሊሲ አቅጣጫ አማራጮች በሚል ጥር 2015 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ከባለድርሻ አካላት ግብዓት ለመሰብሰብ በተዘጋጀ መድረክ ለውይይት ከቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ የተወሰደ**

# የኮሙኒኬሽን ሥራዎች ሀገራዊ አንድነት ላይ ባተኩሩ ትርክቶችና ስትራቴጂዎች መቃኘት እንዳለባቸው ተገለጸ

**ጌትነት ተስፋማርያም**

አዳማ ፡- የኮሙኒኬሽን ሥራዎች ሀገራዊ አንድነት ላይ ባተኮሩ ትርክቶችና ስትራቴጂዎች ዙሪያ መቃኘት እንዳለባቸው የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የኮሙኒኬሽንና ሕዝብ ግንኙነት ከፍተኛ አማካሪ እና የብሔራዊ ሚዲያና ኮሙኒኬሽን ኮሚቴ አባል ቢቂላ ሁሪሳ (ዶክተር) ተናገሩ።

"ውጤታማ ተግባቦት ለኢትዮጵያ ልዕልና" በሚል ሃሳብ በኢፕድ ስልጠና ማዕከልና ከመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ጋር በመተባበር ለኮሙኒኬሽን አመራሮችና ባለሙያዎች በተሰጠው ሥልጠና ላይ ቢቂላ ሁሪሳ (ዶክተር) "የመደመር ትርክትና የኢትዮጵያ ብልጽግና ጉዞ በሚል ርዕስ ጽሑፍ አቅርበዋል።

በወቅቱ ዶክተር ቢቂላ፤ አንድነትንና ኅብረትን የሚያሳዩ እሳቤዎችን አጉልተው የሚያሳዩ የኮሙኒኬሽን ሥራዎችን በማከናወን የሀገር ግንባታውን ውጤታማነት ማጠናከር ይገባል ብለዋል። "ብቻችንን ጎዶሎ ነን ስንሰባሰብ እንሞላለን" የሚል እሳቤ እንደሀገር ውጤት እንደሚያመጣም ዶክተር ቢቂላ ተናግረዋል።


ቢቂላ ሁሪሳ (ዶክተር)

የነገው ትውልድ በእጃችን ነው ያሉት ዶክተር ቢቂላ፤ የመደመር ትርክትን ለሀገራዊ ግንባታ ማዋልና ትውልድ ለመቅረጽ ልንጠቀምበት ይገባል ሲሉ አስረድተዋል። ኮሙኒኬሽን በሕዝቦች መካከል ዘላቂ መስተጋብርና ወንድማማችነት እንዲኖር ከፍተኛ አቅም አለው። በመሆኑም የኮሙኒኬሽን ዘርፉ ዋነኛ ግብ ኅብረ ብሔራዊ ሀገራዊ አንድነትን ማምጣት መሆን አለበት ብለዋል።

መነጠል ያጎድላል፤ ያሉት ዶክተር ቢቂላ፤ የአብሮነት እሳቤዎችን በማጉላት በጋራ መሻገር ይቻላል የሚሉ እሳቤዎችን ማጉላት እንደሚገባ አንስተዋል። ዶክተር ቢቂላ እንዳስታወቁት፤ በመደመር ሀገራዊ ትርክት የተቃኙና የአብሮነት እሳቤዎችን ላይ ያተኮሩ ሚዛናዊ የኮሙኒኬሽን ሥራዎች እንደሀገር በስፋት ያስፈልጋሉ።

ቅንጅታዊ የኮሙኒኬሽን ሥራ በዋናነት በሕዝቦች መካከል አብሮነትን ለማጠናከር እንዲሁም ለሀገር ግንባታ ውጤታማነት አስፈላጊ ነው። ለዚህ ውጤታማነት ደግሞ ትብብርና መደመር ላይ ያተኮረ እሳቤ ያስፈልገናል ብለዋል።

የአንተ ቤት ሲንኳኳ እኔ ቤት ይሰማል የሚለውን ሃሳብ የያዘና የአንዱ ችግር የእኔም ነው ብሎ በማሰብ የሚተገበር የኮሙኒኬሽን ሥራ ለሀገር ግንባታ ውጤታማነት አስፈላጊ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

ዶክተር ቢቂላ እንደገለጹት፤ የኮሙኒኬሽን አመራሮችና ባለሙያዎች በሀገር ግንባታው ታሪካዊ ኃላፊነት ስላለባቸው፤ የሚያስተላልፏቸውን መረጃዎች በተለያዩ አቅጣጫዎች ማየት ይገባል። በዚህ ረገድ ሕዝብን ወደኋላ የሚመልስ ሳይሆን ሀገራዊ እሳቤ ላይ ትኩረት አድርጎ የሚያሰባስብ የኮሙኒኬሽን ሥራ ያስፈልጋል ።

በሁለት ሕዝቦች መካከል ፍቅር እንዲኖር ከፈለግን አንድነት ያስፈልጋል የሚለውን እሳቤ በሕዝብ ዘንድ እንዲሰርጽ ማድረግ ይገባል ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል።

ዶክተር ቢቂላ እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ የጋራ ግባችን በመሆኗ በሀገሬ ጉዳይ ያገባኛል የሚል ከእንግድነት ይልቅ ጠንካራ የባለቤትነት ስሜት ያለው የኮሙኒኬሽን አመራርና ባለሙያ አስፈላጊ ነው።

አላስፈላጊ ትርክቶችን ለማስቀረት ሥራዎች የሚከናወኑት በትውልድ ቅብብሎሽ መሆኑን መረዳትና ቅብብሎሹን እያሳዩ መሄድ ያስፈልጋል። ከዚህ ባለፈ ስር የያዙ አንዳንድ ትርክቶችን በሀገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ ተወያይተን እንፈታቸዋለን ብለዋል።

# "ኢፍጣራችን ለወገናችን" የጎዳና ላይ ኢፍጣር መርሐ ግብር ተካሄደ

- ሼህ ሐጂ ኢብራሂም

**አማን ረሺድና ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡ የሦስተኛው ዙር ታላቁ የጎዳና ላይ የኢፍጣር ሥነ ሥርዓት "ኢፍጣራችን ለወገናችን" በሚል መሪ ሐሳብ በአዲስ አበባ በትናትናው ዕለት ተካሂዷል። የዘንድሮ የጎዳና ላይ ኢፍጣር የተቸገሩ ወገኖችን ለመርዳት ያለመ መሆኑ ልዩ ያደርገዋል ሲሉም ሼህ ሐጂ ኢብራሂም ቱፋ ተናግረዋል፡፡

የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ሼህ ሐጂ ኢብራሂም ቱፋ በመርሐግብሩ ላይ እንደገለጹት፤ የተቸገሩ ወገኖችን መርዳት የእስልምና አስተምሕሮ ነው። በዚህም የዘንድሮ የጎዳና ላይ ኢፍጣር የተቸገሩ ወገኖችን ለመርዳት ያለመ በመሆኑ ልዩ ያደርገዋል፡፡

እንደ ሐጂ ኢብራሂም ገለጻ የዘንድሮውን የረመዷን የጎዳና ላይ ኢፍጣር መርሐ ግብር ከራስ ምቾትና ደስታ ባለፈ በተለያዩ ሰው ሠራሽና ተፈጥሯዊ ምክንያቶች የተቸገሩ ወገኖችን መርዳት በሚል መሪ ሃሳብ የሚካሄድ በመሆኑ ልዩ ያደርገዋል።

የአዲስ አበባ እስልምና ጉዳዮች ከፍተኛ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ሼህ ሱልጣን ሐጂ አማን በበኩላቸው፤ የረመዷን ወር የመተዛዘን፣የመደጋገፍና የመረዳዳት ወቅት ነው። በዚህም የዘንድሮው የጎዳና ላይ ኢፍጣር መርሐ ግብር ኢፍጣራችን ለወገናችን በሚል መሪ ሃሳብ መርሐ ግብሩ እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡

እንደ ሼሕ ሱልጣን ሐጂ ገለጻ ታላቁ የጎዳና ላይ ኢፍጣር ለረመዷን ወር ተጨማሪ ድምቀት ሆኗል። የሙስሊሙን ሃይማኖታዊ እሴቶችን ከማጎልበት ባሻገር የማኅበረሰቡን አንድነት የሚያጠናክር መሆኑን በመግለጽ ለወገን የመድረስ ተልዕኮንና በሃገራዊ የልማት እንቅስቃሴ ላይ ጠንክሮ የመሳተፍን ዓላማን በማንገብ የተካሄደ ነው ብለዋል፡፡

በኢፍጣር መርሐ ግብሩ የእምነቱ አባቶች፣ ተከታዮችና ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች ተገኝተዋል። ሙስሊሙ ማኅበረሰብ አንድነቱንና ሃገራዊ አብሮነቱን አጠናክሮ ለማስቀጠል የጎዳና ላይ ኢፍጣሩ ፋይዳ ከፍተኛ መሆኑም በመርሐ ግብሩ ላይ ተገልጿል፡፡

# "እንደ ሀገር ከተጀመረው የለውጥ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ያዘጋጀው "ውጤታማ ተግባቦት ለኢትዮጵያ ልዕልና" የተሰኘ የኮሙኒኬሽን አመራሮችና ባለሙያዎች ሥልጠና ትናንትና ተጀምሯል።

ውይይቱን በንግግር የከፈቱት የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር ዶክተር ለገሰ ቱሉ፤ እንደ ሀገር ከጀመርነው የለውጥ ጉዞ፣ አዲስ ተላምዶና አቅጣጫ ጋር የሚጣጣም የኮሙኒኬሽን ሥራ ያስፈልጋል ሲሉ ተናግረዋል።

የኮሙኒኬሽን ሥራዎቻችን በሕዝቦች ዘንድ መልካም መስተጋብር በመፍጠር ረገድ ጉልህ ሚና አላቸው ያሉት ዶክተር ለገሰ፤ በዚህ ረገድ በየተቋማቱ የሚገኙ የኮሙኒኬሽን ሥራዎች ውጤታማ እንዲሆኑ ጥረት ማድረግ እንደሚገባ አስታውቀዋል።

ኮሙኒኬሽን የሕዝቦችን ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ፍላጎት ለማሳካት እንዲሁም መልካም መስተጋብርን ለመፍጠር የሚረዳ የተግባቦት ዘዴ በመሆኑ ከእስካሁኑ በበለጠ አግባብ ልንጠቀምበት ይገባል ብለዋል።

ዶክተር ለገሰ እንደገለጹት፤ በሕዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ሥራ የሕዝብን ፍላጎትንና ጥቅም እንዳይሳካ ከታሪክ የወሰድናቸው ትርክቶችና ጽንፈኝነቶች ፈተና ይሆናሉ። ችግሮቹን ተቋቁሞ የተሳካ ውጤት ለማምጣት የተግባቦትና ሕዝብ ግንኙነት ሥራ ወሳኝነት አለው፡፡

የኢትዮጵያን ሕዝብ ወደፊት የሚያራምዱ ሁኔታዎችን ለመፍጠር በኮሙኒኬሽን ዘርፉ የበለጠ ተቀናጅቶ መሥራት ይጠበቃል ።

የኮሙኒኬሽን ሥራ ውሳኔና ጊዜን ታሳቢ ያደረገና በባሕሪው ከወታደር ሙያ ጋር የሚመሳሰል ነው። ወታደር ተኩስ በተባለ ሰዓት ካልተኮሰ አደጋ ይፈጠራል፤ የኮሙኒኬሽን ሙያተኛም መናገር ባለበት ሰዓት ካልተናገረ ሌላ ይናገርለትና፤ ችግር ይፈጠራል ብለዋል። በመሆኑ ክህሎት፣ የጊዜ አጠቃቀምና እሳቤ በኮሙኒኬሽን ሥራ ውጤታማነት ላይ ወሳኝ መሆናቸውን አውቆ መሥራት እንደሚገባ አስታውቀዋል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የሥልጠና ማዕከል ከመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ጋር በመተባበር ያዘጋጀው የኮሙኒኬሽን አመራሮችና ባለሙያዎች ሥልጠናው ከሥራ ባሕሪ ጋር የተያያዘና የዘርፉን አሠራር ለማሳደግና ክህሎትን ለማጎልበት ያለመ መሆኑን ተናግረዋል።

ከባለሙያው ውስጣዊ ችግሮችና ከውጫዊ ተጽዕኖዎች የተነሳ የሚፈጠሩ የተግባቦት ጉድለቶችን በማስተካከል ውጤት ማምጣት እንደሚቻል የተናገሩት ሚኒስትሩ፤ ሥልጠናው የኮሙኒኬሽን ባለሙያዎችንና አመራሮችን አቅም በማሳደግ ረገድ እንደሀገር የተሻለ ሥራ ለማከናወን የሚረዳ መሆኑን ገልጸዋል።

ለውጤታማ የሀገር ግንባታ ሀገራዊ ዕይታ ያለው የኮሙኒኬሽን ስትራቴጂና አቅጣጫ መከተል ይገባናል ያሉት ዶክተር ለገሰ፤ በዚህ ረገድ ሥልጠና መሰጠቱ በዘርፉ ያሉ ባለሙያዎች ተቀራርበው እንዲሠሩ ይረዳል ሲሉ አስረድተዋል።

በሥልጠና መድረኩ ምን አይነት የተግባቦት መንገድ መከተል ይገባል?፤ ምን አይነት የኮሙኒኬሽን ስትራቴጂዎች ውጤታማ ያደርጋሉ? የሚሉና ሌሎችም ሀገራዊ እሳቤ ያላቸው ጉዳዮች ላይ ትኩረት መደረጉን አስታውቀዋል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ጌትነት ታደሠ በበኩላቸው፤ "ውጤታማ ተግባቦት ለኢትዮጵያ ልዕልና" በተሰኘው ሥልጠና በአራት ጉዳዮች ላይ ትኩረት መደረጉን ገልጸዋል።

አቶ ጌትነት እንዳስታወቁት፤ የመጀመሪያው የሥልጠና ርዕስ "የመደመር ትርክትና የኢትዮጵያ ብልጽግና ጉዞ" ሲሆን፤ ሁለተኛው ርዕስ ደግሞ "የሕዝብ ግንኙነት መሠረቶች አጀንዳ ቀረጻና የቀውስ ኮሙኒኬሽን" ነው።

"ሚዲያ ማኔጅመንትና ፐብሊክ ስፒች" እንዲሁም "የማኅበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም" በሚሉ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ሥልጠናው እንደሚሰጥ አስታውቀዋል። በሥልጠናው በኮሙኒኬሽን ዘርፉ ጥልቀት ያላቸው ሃሳቦች ላይ ሰፊ ውይይት ይደረጋል ብለዋል።

ለኮሙኒኬሽን አመራሮችና ባለሙያዎች የተዘጋጀው "ውጤታማ ተግባቦት ለኢትዮጵያ ልዕልና" የተሰኘው የሥልጠና መድረክ ከመጋቢት 30 ቀን 2015 እስከ ሚያዚያ 3 ቀን 2015 ዓ.ም ድረስ ለአራት ቀናት እንደሚካሄድ ተገልጿል።

# "ሪፎርሙ የክልል ልዩ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት ጋር በነበራቸው ቆይታ እንደገለጹት፤ የሪፎርም ፕሮግራሙ የክልል ልዩ ኃይልን መበተንና ትጥቁን ማስፈታት ሳይሆን ይሄንን ኃይል እንደገና ሪፎርም ተደርጎ የሚያደራጅ ነው፡፡

የየክልሉ ልዩ ኃይሎች የየክልላቸውን ጸጥታ በመጠበቅ እንዲሁም ከመከላከያ ጋር አብረው ሃገር ለመጠበቅ መታገላቸው ትልቅ ጥንካሬ ቢሆንም አወቃቀሩ ላይ ግን ጉድለት አለው ያሉት ጄኔራል አበባው ፤ሕገ መንግሥቱ እውቅና የሚሰጠው ለመከላከያ፣ ለፌዴራል ፖሊስ እና ለመደበኛ ፖሊስ ብቻ በመሆኑ የክልል ልዩ ኃይል አወቃቀር ሕጋዊ እንዳልሆነ ተናግረዋል ፡፡

የኃይል አገነባቡ ብሔር ተኮር በመሆኑም የሕዝቦች አብሮ የመኖር አንድነትን እንደሚሸረሽር የገለጹት ጄኔራል አበባው፤ አወቃቀሩን ማስተካከል እና ሥርዓት ማስያዝ የግድ አስፈላጊ እንደሆነ አመልክተዋል፡፡

ሥራው የተገባበት ለረጅም ጊዜ ጥናት ተደርጎበትና እኩል በጋራ እየተፈጸመ እንደሆነ ጠቁመው አንዱን ክልል ኃይል እንዲኖረው ሌላኛውን ኃይል እንዳይኖረው እንደማይደረግ ተናግረዋል። ሪፎርሙ ዓላማው በኢትዮጵያዊነት የተገነባ ለሁሉም ሕዝብ እኩል የሆነ ፤ ለኢትዮጵያዊነት ጠቅላይ ግዛት ሊሞች የሚችል ችሎታ ያለው በቴክኖሎጂና በትጥቅ እንዲሁም በአሠራር የዘመነ የጸጥታ ግብረ ኃይል ማደራጀት እንደሆነ አብራርተዋል። በዋናነት የሚያጠነጥነው የሃገሪቱ ግዛት አንድነት ፣ሉዓላዊነት፣የሕዝቦች ደህንነት መነሻ አድርጎ መጠበቅ እና መከላከል ላይ መሆኑንም ነው የገለጹት፡፡

በሪፎርሙ የትግራይ ክልልም እንደ ማንኛውም ክልል መደበኛ ፖሊስ ብቻ እንደሚኖረው የገለጹት ጄኔራል አበባው ፤ የታጠቀ ኃይል በፍጹም ሊኖረው እንደማይችል ተናግረዋል። የተፈጠረውን የኮሙኒኬሽን ችግር እየፈታተነው ነው ያሉት ጄኔራሉ ፣በአንዳንድ የአማራ አካባቢዎች እና ዩኒቶች ካልሆነ በስተቀር አማራ ልዩ ኃይል በአብዛኛው እንደተቀበለው ገልጸዋል።

የሁሉም የክልል የጸጥታ ኃይሎች ተግባራዊ እንዲሆን ታስቦ እየተሠራ ያለ ፕሮግራም እንደሆነ ስለሚታወቅ አንዳንድ ቦታ ላይ ያልተረዱ አባላት ቆም ብለው እንዲያስቡ እና ወደ ፕሮግራሙ እንዲመጡም ጠይቀው የኢትዮጵያ ሕዝብም አንድ መከላከያ እንዲኖር ከጎናችን መሆን አለበት ብለዋል፡፡

እንደ ጄኔራል አበባው ገለጻ ፤በሃገር ውስጥ እና ከሃገር ውጭ ያሉ ጽንፈኞች በጉልበት እና በአመጽ መንግሥት መገልበጥ እንደማይቻል በመረዳት ወደ ንግግር መምጣት አለባቸው። አንድን መንግሥት ማውረድ የሚቻለውም በምርጫ ብቻ ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ በኃይል ስልጣን መያዝ የማይታሰብ በመሆኑ በሰላማዊ መንገድ የማይመጡ ከሆነ ዝግጁ የሆነ ኃይል እንዳለም ጠቁመዋል።

አማራ አካባቢ ላይ የነበረው የአገው ሸንጎ እና ቅማንት እንዲሁም ቤንሻንጉል እና ጋምቤላ ላይ የነበረው ችግር በንግግር እየተፈታ ነው ያሉት ጄኔራሉ፤ የትጥቅ ትግል ስለማያዋጣ በንግግር ወደ ሰላም እየተመጣ መሆኑን አመላክተዋል።

# ነፃ ሃሳብ



የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፣ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

(በጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

# የሀገር ታሪክ በዘር እህል ይመሰሳል

**"በዱሮ በሬማ ታርሷል!"፤**

የተሸከሙትን መልእክት ልብ ብለን ሳንመረምር ለዕለት ተዕለት አኗኗራችን ከምንገለገልባቸው የተግባቦት ብሂሎቻችን መካከል አንዱ፤ "በዱሮ በሬ ያረሰ የለም" የሚለው አባባል ቀድሞ ይጠቀሳል፡፡ ሽምተን ወይንም አርሰን "የዕለት ጉሮሯችንን ለመድፈን" የምንመገባቸው የዛሬዎቹ የእህል ዓይነቶች በትናንት በሬ ታርሰው ዘራቸው በቅብብሎሽ ከእኛ ዘንድ መድረስ ስለቻለ ብቻ ነው፡፡ የዛሬው አርሶ አደር ከትናንት ወንድሙ (እህቱ) በማሳው ላይ የሚዘራውን ዘር "በአደራ" ባይቀበል ኖሮ የሀገራችን ማሳዎች በሙሉ ጦም ውለው ጦም ባሳደሩን ነበር፡፡

እርግጥ ነው፡- በቅብብሎሽ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፍ የኖረው የእህል ዘር ምናልባትም ሳይለቀም ወይንም ከአስተላላፊው "ቸልተኛነት" የተነሳ ጥቂት የእንክርዳድ ፍሬዎች ሊቀላቀሉበት ይችሉ ይሆናል። ልቅም ያለ ንፁህ የእህል ዘር ከትውልድ ትውልድ ቅብብሎሽ ተደርጎም እያለ ተቀባዩ ገበሬ ዘሩን በራሱ ማሳ ላይ ከዘራ በኋላ "ተቀብረው ያንቀላፉ" አንዳንድ የአረም ዘሮች የእርሻው መለስለስ ተመችቷቸው በመንቃት ከአዝመራው ጋር መሳ ለመሳ በማደግ ከዋናው ምርት ጋር ተቀላቅለው ጎተራ ሊገቡ ይችሉ ይሆናል፡፡

በጭካኔ የታወሩና በግፍ አብሾ የሰከሩ አንዳንድ ክፉ ግለሰቦችም በዕለት ግጭት ከተቀያየሙት አርሶ አደሮች ማሳ ውስጥ በጨለማ እንክርዳድ በመዝራት "ደመኛቸውን" ለመበቀል እንደሚሞክሩ በአንዳንድ የሀገር ቤት የእሳት ዳር የቤተሰብ ጭውውቶች ውስጥ "በአያ እከሌ ማሳ ውስጥ ጠላት እንክርዳድ ዘርቶበት ሰብሉ ተበላሸ" እየተባለ መተረኩ የተለመደ ነው፡፡ እንዲያውም እኮ በቅዱስ መጽሐፍ ውስጥም ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ ከላይ የተጠቀሰውን መሰል ምሳሌ በማብራራት አስተምሯቸዋል፡፡

"ኢየሱስም ምሳሌው እንዲህ ሲል ነገራቸው፡፡ መንግሥተ ሰማይ በእርሻው ቦታ ምርጥ ዘር በዘራ ገበሬ ትመሰላለች፡፡ ነገር ግን ገበሬውና ቤተሰቡ ተኝተው ሳሉ፣ ጠላት መጥቶ በስንዴው መካከል እንክርዳድ ዘርቶ ሄደ፡፡ ስንዴው በቅሎ ማፍራት ሲጀምር እንክርዳዱም አብሮ ብቅ አለ፡፡ የእርሻው ባለቤት አገልጋዮች ወደ እርሱ ቀርበው ‹ጌታ ሆይ፣ በእርሻህ ቦታ ጥሩ ዘር ዘርተህ አልነበረምን? እንክርዳዱ ከየት መጣ?› አሉት፡፡

እርሱም የጠላት ሥራ ነው አላቸው፡፡ አገልጋዮቹም፣ ‹እንክርዳዱን ሄደን እንድንነቅለው ትፈልጋለህ?› ብለው ጠየቁት፡፡ እርሱ ግን፣ ‹አይሆንም፣ ምክንያቱም እንክርዳዱን እንነቅላለን ስትሉ ስንዴውንም አብራችሁ እንዳትነቅሉ ተውአቸው፤ እስከ መከር ጊዜ አብረው ይደጉ። በአጨዳ ወቅት እንክርዳዱን አስቀድማችሁ ንቀሉ፤ በእሳትም እንዲቃጠል በየነዶው እሰሩት፤ የስንዴውን አዝመራም ሰብስባችሁ በጎተራዬ ክተቱ አላቸው፡፡" (ማቴዎስ 13፡24 - 30)፡፡

ለትንተናችን ማጠንጠኛ የምናደርገው ዛሬ የምንዘራው የእህል ዘር በትናንት በሬ ታርሶ ትውልድና ዘመን እየተሻገረ የተቀባበልነው በረከት እንጂ እንደ ኢንዱስትሪ ሸቀጦች በፋብሪካ ተፈብርኮ የምናገኘው ያለመሆኑን አስረግጦ ለመናገር ነው፡፡ ስለዚህም የዘር እህል ክቡር ነው፡፡ ለእለት ፍጆታ አይቆላም፤ አይፈጭምም። የሚቀመጠውም በጥንቃቄ ነው፡፡ የዘር እህል ተስፋም ነው፡፡ በአንድ ጭብጥ የዘር እህል ውስጥ መቶ እጥፍ በረከት ታጭቆበታል፡፡

"መቼም አላለልኝ ከዘሩ ቁይልኝ" እንዳለው ባለሀገር፤ የዘር እህል ቋጠሮ ተፈትቶ ለዕለት ችግር ወይንም ለነፍስ አድንነት ይዋል ቢባል እንኳን በምክንያትነት የሚጠቀሰው የከፋ የድርቅ፣ የጦርነት ወይንም የመፈናቀል መከራ በአርሶ አደሩ ላይ ውድቆ ንብረቱም መቅኖ አጥቶ ከቀዬው ነቅሎ እንዲሰደድ ግድ ሲሆን ብቻ ነው፡፡ እንዲያም ቢሆን ግን አንዳንድ ጽኑ እምነት ያለው አርሶ አደር "የዘር እህሌን ከምበላ ሞቴን እመርጣለሁ" የሚለውን መሃላውንና ቃል ኪዳኑን ላለማፍረስ ሲል ለዘር የቋጠራትን እፍኝ እህል በዱላው ጫፍ አንጠልጥሎ ለመሰደድ መጨከኑ አይቀርም፡፡

እግር ባደረሰው አካባቢ ሲደርስ ተፈጥሮ ፊቷን መልሳ የሚታረቁ ከሆነ ሊዘራ ተስፋ በማድረግ መሆኑን ልብ ይሏል፡፡ "የዘር እህል የትናንትናና የዛሬ ብቻ ሳይሆን፤ የነገ ተስፋም ጭምር ነው" የሚባለውም ስለዚሁ ነው። እናስ የዘር እህልና የሀገር ታሪክ እንዴት ተመሳሰሉ? ቀጥለን የምናብራራው ይሆናል፡፡

**"ያለ ታሪክ ሀገር አይደምቅ"፤**

ታሪክ ማን ነበርንን፣ እንዴት እየኖርን ነውንና የነገውን ውሎ አምሸቷችንን ተስፋ በሦስትዮሽ ሸርቦ ለአኗኗራችን ትርጉም የሚሰጠን የሕይወት ጉዟችን አሻራ የታተመበት የተመልካችን መስታወት ነው። ስለዚህም ነው፤ "History is not the past but a map of the past, drawn from a particular point of view, to be useful to the modern traveller." የሚባለው፡፡ በዓለማችን ላይ በጎ ተጽእኖ አሳርፈው ካለፉት ተጠቃሽ ነፍሰ ሄር ግለሰቦች መካከል ጥቂቶች ስለ ታሪክ ፋይዳ የተናገሩትን አጫጭር ዘመን ተሻጋሪ ጥቅሶች በተቀራራቢ ትርጉም አስታውሰን ወደ ዋናው መዳረሻችን እንገሰግሳለን፡፡

አሜሪካዊው የሳይንስ ፊክሺን መጻሕፍት ደራሲውና የኤሮኖቲካል ኢንጂነር የነበረው ሮበርት ሔይንሌይ (እ.ኤ.አ 1907 - 1988) ስለ ታሪክ የተናገረው ተጠቃሽ አባባል በብዙዎች ዘንድ ይታወስለታል፡፡ እንዲህ ነበር ያለው፡- "ታሪኩን የማያከብር ትውልድ ትናንትም ይሁን ነገ በፍጹም የእርሱ አይደሉም፡፡" በፍልስፍና እውቀቱና በኮሚዩኒኬሽን የጥናት ዘርፍ ዘመን ተሻጋሪ ቀመር ያወረሰን ካናዳዊው ኸርበርት ማርሻል መክለኻን (1911 - 1980) ደግሞ ለታሪክ ብያኔ የሰጠው እንዲህ በማለት ነው፡- "ታሪክን የሚያከብሩና የሚያስታውሱ አሸናፊዎች ናቸው፤ ለታሪክ ክብር የማይሰጡት ግን በሦስቱ የጊዜ (ትናንት፣ ዛሬና ነገ) የትውልድ ቅብብሎሽ ሲኮነኑ መኖራቸው አይቀርም፡፡"

ለነጻነት ባደረገው ተጋድሎ በጥቁር አሜሪካዊያን ዘንድ ታሪኩ ደምቆ የሚነገርለት ማርቲን ሉተር ኪንግ ጁኒዬር (1929 - 1968) እና የትውልድ ሀገሩ የአሜሪካ 34ኛ ፕሬዚዳንት የነበሩትና በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት የተባበሩትን የተለያዩ ሀገራት የቃል ኪዳን ጦረኞች በዋና አዝማችነት በማስተባበር ዝናን የተጎናጸፉት ድዋይት አይዘንሀወር (1890 - 1969) ስለ ታሪክ ምንነት እምቅ ሃሳብ የታጨቀባቸውን አባባሎች ትተው ያለፉት እንዲህ በማለት ነበር፡- "እኛ ታሪክ ሰሪዎች ሳንሆን በታሪክ የተሰራን ሕዝቦች ነን፡፡"፣ "የታሪክ ሁነቶች ሁሉ እኛ የዛሬዎቹ በምናይበት ምልከታ የሚፈረጁ ሳይሆኑ በትናንት ውጤታቸው የሚመዘኑ ሊሆኑ ይገባል፡፡"

የእነዚህን ዓለም አቀፍ ተጽእኖ ፈጣሪዎች ድንቅ አባባሎች በቀላል አገላለጽ ለመጭመቅ ብንሞክር የምንደርስበት ውጤት "ታሪክ እንደ ዘር እህል የሚታሰብና የሚከበር እንጂ የአንድ ሰሞን የወረት ስንቅ ያለመሆኑን ነው፡፡" እርግጥ ነው ታሪክ ልክ ከላይ እንዳስታወስነው እንደ ዘር እህል ሁሉ አልፎ አልፎ በእንክርዳድ ቅንጣቶች የሚመሰሉ ድርጊቶች ከውስጡ እየተመዘዙ መዘባበቻም ሆነ መዘበቻ ተደርጎ ሲቆጠርና ሲታሰብ እያስተዋልን ነው። ስህተት ነው። በዛሬ መነጽር እየተመረመረ እንክርዳዱ ብቻ ገዝፎ እየወጣ አሸናፊ ለመሆኑ ለውርርድ መቅረቡ ወይንም እንደ አስፈሪ የነገ ውርስ ያልኖሩበትን ታሪክ እየወንጀሉ መደንበር ያልሰከነ ማንነት መገለጫ ከመሆን ውጭ ምንም ፋይዳ አይኖረውም፡፡

በየትኛውም ሀገር ታሪክ ውስጥ "እንክርዳዱና ስንዴው" አብሮ መጎዳኘታቸው የተለመደ ሂደት ነው። "ከታሪክ መሰዊያ ላይ አመዱን ሳይሆን እሳቱን ጫሩ" የሚለውን አባባል በዚሁ አንጋፋ ጋዜጣ ላይ ደጋግመን ማስታወሳችንም ይኼው እውነታ ግድ ስለሚለን ነው። "ታሪክ ለጨዋ ሰው ክብሩ፤ አእምሮ ለጎደለው ነውሩ" እንዲል ሀገራዊ ብሂላችን፤ የታሪክ መደላድላችንን ንቅን ዛሬያችንን በራሳችን መሠረት ላይ ብቻ ለመጣል ብንሞክርና ብንኩራራ ትርፉ "በድቡሽት (አሸዋ)" ላይ ቤትን ከመገንባት እኩል መታየቱ አይቀሬ ይሆናል፡፡

ከአባቶቻችንና ከእናቶቻችን እየተላለፈልን የመጣውን ቋንቋ፣ ባህልና ወግ እሶሶ እያልንና እየዘመርን አክብረን በመቀበል፤ የታሪክ ጉዳይ ሲነሳ ግን ስለምን "የመፋለሚያ ሻምላችንን" ከሰቀልንበት ለማውረድ እንደምንጣደፍ ግራ ያጋባል፡፡ በማንኛውም ሀገር ታሪክ ውስጥ "እልል" ተብሎ የሚከበር ታሪክ እንደሌለ የዘርፉ ምሁራን አስረግጠው ይነግሩናል፡፡ መሠረታቸው ሲጣል ከእንክርዳድ ጋር "ተቦክተዋል" የሚባሉ የአንዳንድ ሀገራት ታሪኮች ዛሬ የሚታወሱት ቁስሉ በደረቀ ጠባሳ እንጂ፤ በሚያመረቅዝ ደዌ እየተፈረጁ አይደለም፡፡

አንድ ወዳጄ ሲመሰክር እንደሰማሁት- "የዛሬው የጀርመን ትውልድ በጎዎቹንና የሚኮሩባቸውን የታሪክ ውርሶቻቸውን ብቻ ሳይሆን በዘመነ ናዚ የተፈጸሙ አሰቃቂ ድርጊቶችንም ሳይቀር እንዲያውቃቸው የሚደረገው ለመበቃቀልና እንዲፋጁበት ታስቦ ሳይሆን የታሪካቸው እንክርዳድ መሆናቸውን እንዲማሩበት ለማሳሰብ ነው። ስለዚህም በጀርመን ውስጥ ባሉ ሁሉም የቴሌቪዥን ጣቢያዎች ይህ ኮምጣጣ ታሪክ አዘውትሮ እንዲቀርብ የሚደረገው በዛሬና በነገ ታሪካቸው ውስጥ መሰል ስህተቶችና ድርጊቶች እንዳይፈጸሙ ለማስተማር እንጂ ትውልዱ ‹በእባብ ጉድጓድ ውስጥ› እጁን የመክተት ያህል እንዲዳፈር አይደለም፡፡"

የሀገራችንንም የታሪክ አረዳድ በዚሁ እውነታነት ብንፈትሸው ሳይበጀን አይቀርም። መቶና ሁለት መቶ ዓመታት፣ አርባና ሃምሳ ዓመታት ወደ ኋላ እየተንደረደርን "የታሪካችንን አረሞች" እየቃረምን "የታሪክ ፈጻሚዎቹ አጽም ከመቃብር ተቆፍሮ ወጥቶ የሞት ፍርድ እንዲፈረድባቸው" መወትወቱና "ያረጁ ዶሴዎችን" አቧራ እያራገፉ "አቃቤ ዛሬ" ለመሆኑ መጣደፍና መሸቀዳደም ትርጉም አይኖረውም። የሚሻለው "ያለፈው የታሪክ ስህተት እንዴት ይታረም? መሰል ጥፋቶች እንዳይፈጸሙስ ምን ይደረግ? ማን የትኛውን ድርሻ ይወጣ? ወዘተ." በሚሉት መሠረታዊ ጉዳዮች ላይ መሥራት እንጂ ከትናንቱ የከፋ ታሪክ ለመፈጸም መጀገን ከላይ እንደተገለጸው መሸነፍ ነው፤ እናም "ነፋስን እንደመጎሰም" የሚያስቆጥርም ነው፡፡

**"በአንዱ ስትጠቁም ከጣቶችህ መሃል፣ ሦስቱ ግን ራስህን ይመለከቱሃል፡፡"**

እንዳለው ዜመኛው፤ ያለፈን ታሪክ ወደ ኋላ ተንጠራርተን እየተቸንም ሆነ እየረገምነው ዳግም ተመልሰህ ና! ወይንም ስህተትህን አርም ብለን ፍልሚያ ብንገጥም ጀሮው የተደፈነው ትናንት ምንም ምላሽ አይሰጠንም፤ ጆሮ ያላበቀለው ነገም መስሚያ የለውም።

ጆሮውን ያቀበቀበው ዛሬ ካለፈው ታሪክ ጋር ግብግብ ፈጥረን በእልህ እንጋልብብህ ብለን "ኮርቻችንን ብናመቻች" ይታዘበን ካልሆነ በስተቀር አበጃችሁ ሊለን አይችልም። የሚያዋጣው ሰከን ብለን በማስተዋል ስህተት ያልነውን የታሪክ እንክርዳድ እየነቀስን ማስወገድ እንጂ "በስንዴ ከሚመስለው ትሩፋቱ ጋር አብረን ለመንቀል መዳፈሩ በጀግንነት አያሸልምም፡፡ "ድምጻዊው እንዳለው ባሸለበው ትናንት ላይ "ጣታችንን እየቀሰርን" መፎከሩና ማስፎከሩ ምን እርባና ይኖረዋል? ከትናንት ከወረስነው የታሪክ ህፀፅ በከፋ ደረጃ እኛ የዛሬዎቹ ሦስት እጥፍ ስህተት እየሠራን ነጋችንን እያቆሸሽን እንደሆንስ? እንምከርበት፤ እንመካከርበት፡፡ ሰላም ለሕዝባችን፤ ለዜጎቻችን በጎ ፈቃድ፡፡

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

## የካፌ ኢንዱስትሪው ፈርጥ

**ሰሳማዊት ውቤ**

ወይዘሮ ፀደይ አስራት ይባላሉ፡፡ በንግዱ ዓለም ከተሰማሩ ስኬታማ ሴቶች አንዷ ናቸው፡፡ መለያ መታወቂያቸው ካልዲስ ኮፊ ነው፡፡ አሁን ላይ ስማቸው በካልዲስ ጎልቶ ይጠራ እንጂ በፋሽን ሞዴሊንግ ኢንዱስትሪውም ብዙዎች ያውቋቸዋል፡፡ በዚህ ዘርፍ መታወቅ የጀመሩትም ገና በ17 ዓመታቸው ነበር፡፡ የፋሽን ሙያቸው በወላጆቻቸው ባይወደድላቸውም ለውስጥ ጥሪያቸው ግን መልስ ሰጥተውበታል፡፡ ከዚያም አልፈው ለእነሱ ጆሮ ሳይሰጡ በመሥራታቸው ጥሩ መሸጋገሪያ እንዲያገኙ ሆነዋል፡፡ አሁን ላሉበት የከፍታ ማማም በቅተዋል፡፡

የካልዲስ ኮፊ መሥራችና ባለቤት እንዲሁም ዋና ዳይሬክተር ፀደይ በሥራቸው መካከል የሚገጥሟቸውን ችግሮች ወደ መልካም አጋጣሚ መለወጥ የሚወዱ ናቸው፡፡ ችግር መፍትሄ እንደሚያመላክት፤ ስኬታማ እንደሚያደርግ ያምናሉ፡፡ ለዚህም ማሳያው ለካልዲስ ኮፊ የሚቀርበው ወተት ጥራት መጓደል ሲገጥመው ፈጥነው የወተት ማቀነባበሪያ ፋብሪካ በማቋቋም አደጋውን መመለስ የቻሉበት ነው፡፡

ወይዘሮ ፀደይ “እኔ ካልዲስን የከፈትኩት ተሰጥቶኝ ነው፡፡ እኔስ የተሰጠኝን የጋራ የማደርገው ምን ሰጥቼ ነው” በሚል ወተት የሚያቀርቡላቸውን የሱልልታ እናቶች በዶሮ እርባታ በማደራጀት በቀን ከአራት ሺህ በላይ እንቁላል ለካልዲስ ካፌ በማቅረብ ራሳቸውን እንዲችሉ አድርገዋል፡፡ 50 ሴት ልጆችንም በዩኒቨርሲቲ በማስተማር ማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ ችግሮችን እየፈቱ ናቸው፡፡

ሴቶችን ማብቃት የወይዘሮ ፀደይ የሰርክ መመሪያ ነው፡፡ ትጋት ግብራቸው ሲሆን፤ ከሌሊቱ 10 ሰዓት ከመኝታቸው መነሳታቸው ለአብነት ይጠቀሳል። ንቁና ፈጣን ናቸው፡፡ በአራዶቹ መንደር ቂርቆስ መወለዳቸውና ለተወሰነ ጊዜ በዚያው ማደጋቸው ለዚሁ ሥራቸው እንደረዳቸው ይናገራሉ፡፡ በሴትነታቸው በግል የገጠማቸው ችግር ባይኖርም በሌሎች ሴቶች ላይ የሚደርሱ ችግሮችን አብዝተው ማስተዋላቸው ሴቶች እንዲያበቁ ከማድረግ ባሻገር ለሙብትና ጥቅማቸው ትኩረት እንዲቸሩ አስቿሏቸዋል፡፡

### ልጅነት

የካልዲስ ኮፊ መሥራችና ባለቤት እንዲሁም የካፌ ኢንዱስትሪውን አስጀማሪ ናቸው የሚባልላቸው ወይዘሮ ፀደይ የተወለዱት በ1968 ዓ.ም አዲስ አበባ ውስጥ ቅዱስ ቂርቆስ ቤተክርስቲያን አካባቢ ነው፡፡ ‹‹ቂርቆስ በጣም የምወደውና አራድነቴን የሚያስታውሰኝ ሰፈር ነው›› ይላሉ ሰፈራቸውን ወደኋላ ዞር ብለው በአሳለፉት ጊዜ ሲያስታውሱት፡፡ ከዚያ ደግሞ ወላጆቻቸው ቂርቆስን ለቅቀው ወደ ጎፋ ካምፕ መብራት ኃይል አካባቢ ሲዘዋወሩ እርሳቸውም አብሮ መሄድ ግዴታቸው ነውና ያንንም ሰፈር የሚረሱት አይደለም፡፡ ብዙ የልጅነት ትዝታ በዚያም ነበራቸው፡፡ ይሁን እንጂ እንደ ቂርቆስ ግን አይሆንላቸውም፡፡ ምክንያቱም ከዚያ ሰፈር የለቀቁት የአምስተኛ ክፍል ተማሪ ሳሉ ነው፡፡

የቂርቆስ ሰፈር ትዝታ አሁንም ከልባቸው አይጠፉም፡፡ የቂርቆስ ሰፈር የአራድነት ትምህርት አሁን ላለው ማንነታቸው መሰረት ነው፡፡ ስለዚህም ማህበረሰቡን፣ የእድሜ ጓደኞቻቸውን፤ ልጅነታቸውን በፍቅር የሚያስታውሱበት ሰፈር ስለሆነም አጥብቀው ይወዱታል፡፡

### ትምህርት

ትምህርታቸውን አሀዱ ያሉት በልደታ ካቴድራል የልጃገረዶች ትምህርት ቤት ነው፡፡ ከትምህርት ቤቱ ሳይለቁም እስከ ስምንተኛ ክፍል ተምረውበታል፡፡ ከዚያ ወደ ጥቁር አንበሳ ትምህርት ቤት በማምራት እስከ 12ኛ ክፍል ያለውን ትምህርታቸውን ተከታትለዋል፡፡ በዚህ የትምህርት ቆይታቸው በጣም ፈጣንና ጎበዝ ተማሪ ሲሆኑ፤ ይህ አቅማቸው መባከን ስለሌለበትም ሌሎች አማራጮችን ወደማፈላለጉ ገቡ፡፡ ይህም የንግድ ዓለሙን መቀላቀል ሲሆን፤ ጥቅሙን የተረዱት ገና የ12ኛ ክፍል ትምህርታቸውን ሳይጨርሱም ነበር፡፡ እናም 12ኛ ክፍል ሲጠናቀቅ ቀጥታ ሥራ ሆነ ተግባራቸው፡፡

### የፋሽን ኢንዱስትሪ

“እኔና ወንድሜ ክረምት ውስጥ ትምህርት ቤት በሚዘጋበት ጊዜ እናትና አባታችን ሥራ ሲሄዱ ጠብቀን ዓመቱን ሙሉ በተማርንበት ደብተራችን የኪስ ወረቀት እየሰራን ወደ ሱቅ በመውሰድ በኪሎ እንሸጥ ነበር” ሲሉ የሚያስታውሱት ወይዘሮ ፀደይ፤ የ12ኛ ክፍል ትምህርታቸውን እንደጨረሱ ፈጥነው ወደ ፋሽን ኢንዱስትሪው ነበር የገቡት፡፡ በእርግጥ ለዚህ መሰረቱ የልጅነታቸው ፍላጎት ነው፡፡

“ሞዴሊንግና ማስታወቂያ መልክ ይጠይቃል። ተመልካችም የሚመርጠው ይሄንኑ ነው” የሚሉት ወይዘሮዋ፤ ያኔ የፋሽን ሞዴሊንግ ሥራውን በቅጥር ሲቀላቀሉ የ17 ዓመት ታዳጊ ነበሩ፡፡ ዛሬም ከ30 ዓመት በኋላ በጅም እየታገዘ የትናንቱን ያህል ባይሆንም መልከ መልካም ናቸው፡፡ የሰውነት ቁመናቸውም ምንም እንከን አይወጣለትም፡፡ ቁንጅና አስተሳሰብንና በራስ መተማመንን ያካትታል፡፡ ውስጣዊ ውበትም ነውና ወደዚህ ሥራ ያስገባቸው ይህ ነገር እንዳላቸው ስለሚያምኑ ነው፡፡

ዛሬ የቁንጅና ውድድር አለባበስን፣ መልክና የሰውነት አቋምን ብቻ ሳይሆን በራስ መተማመንና ውስጣዊ ስዕብና ጭምር ይጠይቃል፡፡ ይሄ ሁሉ ተደምሮ ነው አንድን ሴት ውብ ናት ማለት የሚቻለው፡፡ ስለዚህም ይህንን የሚያሟሉ ሴቶች ደግሞ እንደ ሀገር በርካታ ናቸው፡፡ ነገር ግን ራሳቸውን ማውጣት ስላልቻሉ ጎልተው አልታዩም ይላሉ፡፡

የወይዘሮ ፀደይ እናትና አባት የሚፈልጉት ልጃቸው በአንድ ሙያ ተምራ በአንድ የመንግስት መሥሪያ ቤት በፀሐፊነት ወይም በሌላ የሴት በሚባል ሙያ ተቀጥራ የራሷ ጌታ ሆና ሕይወቷን እንድትመራ ነው፡፡ ያኔ አንዲትን ሴት ልጅ ስኬታማ የሚያስብለውም ይሄው ነበርና ምኞታቸው ትክክል ነበር፡፡

“ለሽያጭ በወጣው ማስታወቂያ ስመዘገብ ለወላጆቼ አልነገርኩም፡፡ የእናቴን ቀሚስ ለብሼ ሄድኩና ከሚወዳደሩት መካከል ተመርጬ ለቃለ መጠየቅ ቀረብኩ፡፡ ፈተናውንም አለፍኩ” የሚሉት ባለታሪካችን፤ የምስራቹን እቤት መጥተው ለወላጆቻቸው ሲናገሩ ግን የገጠማቸው የጠበቁትን አልነበረም፡፡ ከፍተኛ ቁጣን አስተናገዱ እንጂ፡፡ በወቅቱ እናታቸው ‹ምንነት ነው የምትቀጠሪው› ብለው ሲጠይቋቸው ‹ሴልስነት› ሲሏቸው ‹ምን ሴልስ ብለሽ ታሰማምሪዋለሽ አሻሻጭ ማለት እኮ ነው›› ብለዋቸው የነበረውን አሁን ድረስ አይረሱትም፡፡

‹‹ውስጣችን የሚለንን እንጂ ሰዎች የሚነግሩንን መስማት የለብንም›› የሚሉት እንግዳችን፤ ወላጆቻቸውን በጣም ያከብራሉ፤ ይወዳሉም፡፡ ነገር ግን በውሳኔያቸው ውስጥ ጣልቃ አያስገቧቸውም፡፡ ለዚህም አንዱ ማሳያ ጆሮ ሳይሰጡ በቀጥታ የፋሽን ኢንዱስትሪውን መቀላቀላቸው ነው፡፡ ቁጣውን እንደቀልድ ቆጥረው ሕልማቸውን አሳክተዋል፡፡ ሥራውንም ጀምረውታል፡፡

በእነሱ ጊዜ የሞዴልነት ሙያ በጣም የማይደገፍና የተዋረደ ሥራ ተደርጎ ይቆጠራል፡፡ በዚህም ‹‹አባቴ ልጅህ እንዲህ ስትሆን ሞተሃል እንዴ ዝም ብለህ የምታየው? ይባል ነበር›› ይላሉ፡፡ ከዚያም አልፎ ከመድረክ ወርደው ወደ ቤት ሲሄዱ ይገረፋሉ፡፡ ነገር ግን በቀጣይ ቀን መልሰው ወደዚያው ሥራ ከመሄድ አይቆጠቡም፡፡ እንዲህ እንዲህ እያሉም ነው በፊሊፕስ፤ በኮካና በንግድ ባንክ ተቋማት ውስጥ ማስታወቂያ መሥራት የቻሉት፡፡ መድረኮች ላይም በርካታ ማስታወቂያዎችን ሰርተዋል፡፡ በካላንደር መልክ መጽሔቶችና ሌሎች ላይ በመውጣት የማስታወቂያ ሥራውን ሲሰሩ ለሁለት ዓመታት ቆይተዋል፡፡

ፋሽን የሳባቸው እኚህ እንስት ከውድድር ባሻገር ቢዝነስ የሚሰሩበትን ሁኔታም ፈጥረዋል፡፡ ጅማሯቸውን ያደረጉትም የነበረውን አለባበስ የበለጠ ለማዘመንና ሴቶች ተፈጥሮ ከቸረቻቸው ውበት በተጨማሪ የተለያዩ ዘመናዊ አልባሳት ፋሽኖችን በመከተል አምረው ደምቀው እንዲታዩ ለማድረግ በሚያስችለው የልብስ መሸጫ ቡቲክ በመክፈት ሥራ ነው፡፡ ሥራው የተጀመረው ከጓደኛቸው ጋር በመመካከር በጋራ በመሆን ሲሆን፤ እሳቸው ለፋሽን ኢንዱስትሪ ሊያግዙኝ ይችላል በሚልም ሁኔታዎችን አመቻቹ፡፡ በመስቀል ፍላወር አካባቢ ሥራቸውን አሀዱ አሉም፡፡ በዚህ ቡቲክም በጣም ስኬታማ ሆኑ፡፡

ቡቲኩ ለእርሳቸው ገቢ ብቻ አይደለም የሰጣቸው። ውሃ አጣጫቸውንም እንጂ፡፡ እኚህ የትዳር አጋራቸው የኢትዮጵያ አየር መንገድ ፓይለት በመሆናቸውም ለቤተሰብ የሚሰጣቸውን ነፃ ትኬት ተጠቅመው ከተለያዩ አገራት ብራንድ ልብሶችን በማምጣት ቡቲኩን አሟሙቀዋል፡፡ ይሄ ስኬታማ ሆኖላቸው እየሰሩ እያሉም



ወይዘሮ ፀደይ አስራት፣

ሁለተኛውን ቡቲካቸውን ቦሌ መድኃኒዓለም ድልድይ አካባቢ መክፈት ችለዋል፡፡

### አሳዛኙ ገጠመኝ

ሁለተኛው ቡቲክ ከበፊቱ የበለጠ ገበያ ነበረውና እጅግ ደማቅ ነው፡፡ ይሁንና መልካም ዕድልን ግን ይዞላቸው አልመጣም፡፡ ምክንያቱም በተከፈተ በ15ኛው ቀን የመጀመሪያው የመስቀል ፍላወሩ ቡቲክ ችግር ላይ ወደቀ፡፡ ያለበት ቦታ ለግንባታ ይፈለጋል ተባለ፡፡ የዛኑ ዕለት በአስቸኳይ እንዲለቁ ተነገራቸውም፡፡ ስለዚህም ምንም አማራጭ አልነበራቸውምና እዛ የነበሩትን ልብሶች በሙሉ ወደ ቦሌው ቡቲክ ማዛወሩን ተያያዙት፡፡ ይህ ብቻም አልነበረም፡፡ ይህ ቀን ሌላ አስደንጋጭ ፈተናም ይዞ መጥቷል፡፡

አስደንጋጩና አሳዛኙ ሁለተኛው ችግርን ሲያወሱትም እንዲህ ነበር ያሉት ‹‹አንድ ረዥም ሰውዬ ወደ ቡቲኩ መጣና ተዋወቀኝ፡፡ በጣም ጥሩ እየሰራሽ ነውም አለና በአድናቆት አበረታታኝ፡፡ ከዚያም ‹ታውቂኛለሽ› ወይ ሲልም ጠየቀኝ፡፡ ‹አላውቅህም› አልኩት፡፡ ‹‹ይሄንን ሱቅ ገዝቼ ፎቅ ልሰራበት ነው›› አለኝና ቢቻለኝ የዛኑ ዕለት ፈጥኜ እንድለቅለት ጠየቀኝ፡፡ በድንጋጤ ዕጤ ዱብ ነው ያለው፡፡ በ15 ቀን ውስጥ ሁለቱንም ቡቲክ እንድለቅ ተደረገ፡፡ በጣም አዝኜ አለቀስኩ፤ እጅግም ከፋኝ››፡፡

ችግሩ ከተፈጠረ በኋላ ከባለቤታቸውና ከጓደኞቻቸው ጋር ሆነው ምሳ ሲበሉ መከፋታቸውን ያዩ የባለቤታቸው ጓደኞች ‹ባለቤትህ ዛሬ ምን ሆና ነው እንዲህ የተከፋችው› አሏቸው፡፡ ከሁለቱ ቡቲክ በአንድ ጊዜ እንዲለቁ መደረጋቸውን ሲነግሯቸው አንዱ ባለሀብት ጓደኛቸው ‹‹ምን ችግር አለው ታዲያ ቦታ ትፈልጋ›› አሏቸው፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ ካልዲስ ኮፊ የተከፈተበት አሁን ኤድናሞል ያለበት አካባቢም ቦታ ተከራዩ፡፡ የሁለት ዓመት ኪራይ ከፈሉላቸውም፡፡ በወቅቱ ሁለተኛ ልጃቸውን ነፍሰ ጡር ነበሩናም ተፈራረሙና ልጃቸውን ለመውለድ ወደ አሜሪካ ሄዱ፡፡

### የባል ገጸ በረከት

‹‹ካልዲስ ኮፊ የባለቤቴ ሀሳብ ነው፡፡ እሱ ነው በተለያዩ ዓለማት ሲበርር የካፌ ኢንዱስትሪ ዕድገት የደረሰበትን ከፍተኛ ደረጃ ተረድቶ ሀሳቡን ያመነጨው›› የሚሉት ወይዘሮ ፀደይ፤ የኢትዮጵያ አየር መንገድን በካፒቴንነት ለ31 ዓመታት ያገለገሉት ባለቤታቸው ከዓመት ፈቃዳቸው ሳይቀር ወስደው ለዝግጅቱ ጉድ ጉድ ሲሉ ቆይተዋል። ሙሉ የቤት ሥራውንም ጨርሰው እርሳቸው ሁለተኛ ልጃቸውን ወልደው ከአሜሪካ እንደተመለሱ አሁን ላይ በአገር ውስጥና በውጭ 40 ቅርንጫፎች ያሉትን፤ ታዋቂነትንና ተወዳጅነትን ያተረፈውን የካልዲስ ኮፊን ‹ሦስተኛ ልጅሽን እንሆ› በማለት አበርክተውላቸዋል፡፡

### ካልዲስ ኮፊ

ካልዲስ ኮፊ የኮፊ ኢንዱስትሪው ፈር ቀዳጅ ነው ይባልለታል፡፡ የካልዲስ ኮፊን በባለቤታቸው ሀሳብ አመንጭነት የመሰረቱት እንግዳችንም ልክ እንደልጃቸውና መሰረት ጣይነቱ እንዲቀጥል ብዙ ታትረዋል፡፡ በዚህም ‹‹ማርሽ ቀያሪዬ፤ መልካም ነገሮችን አመላካቹ ነው። ምክንያቱም ሁለቱንም ቡቲክ በአንድ ቀን እንድለቅ በመደረጌ የደረሰብኝን ሀዘን የረሳሁበት ነው፡፡ ከችግሮች መልካም አጋጣሚን መፍጠር እንደሚቻልም የተማርኩበት ነው፡፡›› ይሉታል፡፡ አክለውም‹‹ባለቤቴ ለሥራ ውጭ ሲወጣ ያየውን ኢትዮጵያ ውስጥ ማቋቋም ፈልጎ እንድመሰርተው ያደረገው ነው›› ይላሉ፡፡

ካልዲስ ኮፊ የዛሬ 19 ዓመት በ30 ሰራተኛ የተጀመረ ሲሆን፤ በወቅቱ ይሄ የሠራተኛ ቁጥር ብዙ ቢሆንም ሰው ሲኖር ሰው ይመጣል ብለው ስለሚያምኑ መልካም ነገሮችን አምጥቶላቸዋል፡፡ በዚያ ላይ ሀሳቡ አዲስ በመሆኑ ከተከፈተበት ዕለት ጀምሮ ተወዳጅነትን አትርፏል፡፡ ተጠቃሚው በመበራከቱ ደግሞ ሰራተኛው መብዛቱ ጠቅሟቸዋል፡፡ ቤቱ በመለመዱም በዓመቱ ሁለተኛውን ቅርንጫፍ ለመክፈትም አስችሏቸዋል። አሁን ቅርንጫፎቹ አሜሪካ፤ ለንደንና አውስትራሊያ ያሉትን ጨምሮ 40 ደርሰዋል፡፡ የሠራተኞቹም ብዛት ከሁለት ሺህ በላይ ደርሷል፡፡

የተጀመረበት1 ነጥብ 5 ሚሊዮን ብር በወቅቱ ገበያ በጣም ትልቅ ብር እንደነበርም አይረሱትም፡፡ ሆኖም ዛሬ የወተት ላም ፋብሪካውን ጨምሮ ሁለት ሼር ካምፓኒዎች ስላሉት ካፒታሉ ይሄን ያህል ነው ብሎ ለመግለጽ አስቸጋሪ ቢሆንም በብዙ እጥፎች ግን እንዳደገ ይናገራሉ፡፡ ‹‹ካልዲስ ኮፊ ከአንድ ወደ 40 መድረሱ ቀላል ይመስላል፡፡ ሆኖም በ19 ዓመት ውስጥ ያጋጠሙን ችግሮች ብዙ ናቸው›› ሲሉም ፈተናዎቹን ያስታውሳሉ፡፡ የካልዲስ ችግሮች ከመንግስት ቢሮክራሲ እንደሚጀምርም ያወሳሉ፡፡

ፓርኪንግ በጣም ይጠቀሙ ነበርና ከትራፊክ ጋር የነበረው ግብግብ በራሱ ትልቅ በሥራ ላይ የሚጋረጥ ችግር ነበር፡፡ ከዚያ ባሻገርም ከገቢዎች ጋር በመካሰስ እርሳቸው በጣም የታወቁ እንደነበሩም አይሸሽጉም፡፡

**ማህበራዊ**

# የሕይወት ገጽታ

«ፍርድ ቤት ውስጥ ከዚሁ ጋር የተያያዙ መአት ፋይሎች አሉኝ» ይላሉ፡፡ ምክንያቱ ከላይ እንዳሉት የቢሮክራሲ ችግር ነው፡፡ ስለዚህም ይሄንና ሌሎች ችግሮች አልፈው ነው ዛሬ ያሉበትን ስኬት የተቀዳጁት፡፡

ወይዘሮ ፀደይ ኮቪድ 19ኝም አንዱ ችግራቸው እንደነበርም አይረሱትም፡፡ ኮቪድ የካልዲስ ኮፊን ኢንዱስትሪ ክፉኛ ጎድቶት ነበር፡፡ በኮቪድ ምክንያት ሰባት የካልዲስ ኮፊ ቅርንጫፎችን ለመዝጋት ተገደዋል፡፡ ሆኖም እንደፈሩት ስላልሆነ የዘጓቸውን ቅርንጫፎች መልሰው ከፍተዋል፡፡ ለዚህም እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል፡፡

ሌላው የካልዲስ ችግር አርሶ አደሩ የሚያቀርብላቸው ቡና ጥራት መጓደል ሲሆን፤ ይሄ ደግሞ የካፊውን ደረጃ ዝቅ አድርጎት ነበር፡፡ ይህም በብልሀት ተፈቷል፡፡ ችግሩን እንደ መልካም አጋጣሚ ወሰዱትና ቡና ከሰው ላይ ሳይሆን ከታወቀ አቅራቢ ድርጅት ጨረታ እየተሳተፉ መግዛትና መጠቀም ጀመሩ፡፡ ከዚሁ ጎን ለጎንም ጥራት ያለው ቡና እራሳቸው በመቁላትና በመፍጨት ለሱፐር ማርኬትና ለሌሎች ተጠቃሚዎች ወደ ማቅረብ ገቡ፡፡ አሁን ይሄንኑ ምርት ወደ ውጭ በመላክ ላይ ናቸው፡፡

ከዚህና ከካፌው ግብዓት ጋር ተያይዞ ትጉኋን ነጋዴ ፀደይን የውጭ ምንዛሪ እጥረትም በብርቱ ፈትኗቸው እንደነበር ያስታውሳሉ፡፡ “አገሪቱ ለመድኃኒትና ለማዳበሪያ መግዣ የውጭ ምንዛሪ አጥታለች በሚባልበት አስቸጋሪ ወቅት እኔ ለኬክና አይስክሬም ግብዓት ስጠይቅ አግባብ አለመሆኑ ይገባኛል” ሲሉም እጥረቱን አየር መንገድ ተርሚናል ውስጥ ባለውና በውጭ ምንዛሪ በሚሸጥበት ቅርንጫፍ ካፊያቸው ከሚያገኙት፤ ብሔራዊ ባንክ በሚፈቅደው ደረጃ እያደረጉ የተወሰኑ ዕቃዎችንም ቢሆን ከውጭ በማምጣት መፍታታቸውን ያስታውሳሉ፡፡

ካልዲስ ኮፊን የገጠመው ችግር ይሄ ብቻም አልነበረም፡፡ አርሶ አደሩ የሚያቀርብላቸውና ለማኪያቶ የሚጠቀሙበት ወተት ውሃና በአድ ነገሮች እየገባበት ፈትኗቸዋል፡፡ ሆኖም የተበላሸው አርሶ አደሩ በሚያቀርብላቸው ወተት ምክንያት መሆኑን ሲረዱ «ችግር ብልሃትን ይወልዳል» ብለው የራሳቸውን ወተት አቀነባብሮ የሚያቀርብ ፋብሪካ አቋቋሙ፡፡

«ፋብሪካው ወደ ሥራ ሲገባ ወተቱ በብዛት አልገኝ አለን» የሚሉት ወይዘሮ ፀደይ፤ የወተት እጥረቱን ለመቅረፍ የወተት ከብቶች ወደ ማርባት ገቡ፡፡ ፋብሪካው ለካልዲስ ኮፊ ቅርንጫፎች በሙሉ ወተት የሚያቀርብ ሲሆን፤ ሱፐር ማርኬቶችና የተለያዩ ተቋማትም ጥራቱን የጠበቀ የወተት ምርት ተጠቃሚ መሆን ቻሉ፡፡ የካልዲስ ቅርንጫፎችም ከአገር አልፎ በአሜሪካ፤ በለንደንና አውስትራሊያ እንዲስፋፉ እድል ሰጣቸው ይላሉ እድገቱ በምን አይነት ፈተና ውስጥ አልፎ እንደመጣ ሲያወሱ፡፡

እንግዳችን በባለቤታቸው ሀሳብ አቅራቢነት «ጉስቶ» የተሰኘ የጣሊያን ሪስቶራንትም የከፈቱ ሲሆን፤ ደረጃውን በጠበቀ ሬስቶራንት በመክፈትም ይታወቃሉ፡፡ ይሄንኑ ዓይነት ሪስቶራንትም ደግመው በመክፈታቸው በስማቸው ያሉ ሪስቶራንቶቻቸው ወደ ሁለት አድገዋል፡፡ በውጭና በአገር ውስጥ ያለ በካፌ የሚሸጥ ቡና ኢንዱስትሪ እንዲያድግም መሰረት ጣይ ናቸው፡፡ «ካልዲስን ስጀምር ሪስቶራንት ይኖረኛል፤ የከብት እርባታ ላይ እሰማራለሁ ብዬ አልነበረም» የሚሉት እንግዳችን፤ ሀሳብ አያልቅምና ሌሎች አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶችን ደግሞ በማቋቋም ሊቀጥሉ እንደሚችሉም ይናገራሉ፡፡ የበለጠ ማተኮር የሚፈልጉት ግን ካልዲስን በማስፋፋት ላይ መሆኑን ያወሳሉ፡፡

«እኔ ካልዲስን የከፈትኩት ተሰጥቶኝ ነው፡፡ እኔስ የተሰጥኝን የጋራ የማደርገው ምን ሰጥቼ ነው» ከሚለው የዘወትር የውስጣቸው ጥያቄ በመነሳት “እንማማር” የሚልም ሳምንታዊ ዩቱብ ቻናል ከፍተው ማህበረሰቡን ያገለግላሉ፡፡ ከማህበረሰቡ የሚያዩትን፤ የሚሰሙትንና የሚያነቡትን ችግሮች እያወጡ ሰው እንዲማርበት ያደርጋሉ፡፡

ወይዘሮ ፀደይ 50 ሴት ልጆችን ዩኒቨርሲቲ ያስተምራሉ፡፡ ሴት አርሶ አደሮችን ያበረታታሉ፡፡ በተለይም ከሥራቸው ጋር ተያይዞ በቅርብ ያውቋቸዋልና ብርቱነታቸውን ይመሰክራሉ፡፡ ምክንያቱም ካልዲስን ተወዳጅ ያደረጉላቸው እነርሱም ጭምር እንደሆኑ ያምናሉ፡፡ ከብቶች ተንከባክበው፤ አልበው፤ ካልዲስ ካፌ እስኪደርስ ድረስ ያለው ሂደት በብርቱ ጉልበታቸው አገልግለውታል ይላሉም፡፡ ለእሳቸው ወተት ያቀርቡላቸው የነበሩት የሱልልታ ሴት አርሶ አደሮች ለዚህ ዋንኛ ማሳያዎች እንደሆኑም ያወሳሉ፡፡

«ሴቶቹ እንዲህ የደከሙበት ወተት ሽያጭ ገንዘብ የሚቀመጥበት የባንክ ቡክ በአባወራው እጅ ነው። ወጪው በእሱ ብቻ ይወሰናል፡፡» የሚሉት ወይዘሮ ፀደይ፤ የእነዚህን ሴቶች ሕይወት ለመታደግም ብዙ የሰሩ ናቸው፡፡ ለአብነት ሴቶቹ ለእነሱ ከሚያቀርቡት ወተት ጎን ለጎን እዛው ቤታቸው ውስጥ ሆነው የሚሰሩትና በባለቤትነት የሚያስተዳድራቸውን ተጨማሪ የገቢ ምንጭ የሚያገኙበትን ሥራ ፈጥረውላቸዋል፡፡ ይህም በማህበር አደራጅተዋቸው በነፍስ ወከፍ ከ60 እስከ 100 እንቁላል ጣይ ዶሮዎችን ገዝተው በመስጠት እንዲገለገሉ ያደረጉበት ነው፡፡



**«እኛ ሴቶች ልብስ ስመልበስ ወይም ተውቦ ስመታየትና ፋሽን ስመከተል የግድ ኢንዱስትሪ ውስጥ መሆን የለብንም**

እንግዳችን ከዶሮዎቹ አልፈው መድኃኒትና መኖም አቅርበውላቸዋል፡፡ ስለዚህም የእነርሱ ድርሻ እንቁላሉን ሸጦ መጠቀም ነው፡፡ የመሸጥ ችግር እንዳይገጥማቸው ሁሉ ምቹ ሁኔታዎችን ፈጥረዋል፡፡ ይህም በቀን አራት ሺህ እንቁላልን የሚረከባቸው ካልዲስ ነው፡፡

### ሴትነትና የስኬት ጥበብ

አሁን ያለውን የፋሽን ኢንዱስትሪ እንዴት እንደሚያዩትና በተለይ ሴትነት፤ ውበትና ፋሽንን ሲያነጻጽሩት የዘንድሮ ልጆች በጣም ዕድለኞች ናቸው ይላሉ፡፡ ምክንያታቸው ደግሞ ድሮ እኛ የፋሽንን ምንነት ለመረዳት ብዙ ልፋትን ይጠይቃል የሚለው ነው፡፡ መጽሔት ማገላበጥ፣ የውጭ ፊልም ማየት ግድ ነው፡፡ አሁን ላይ ግን የዘመኑ ፋሽን ምንድነው የሚለውን ጨምሮ ማህበራዊ ሚዲያው በየስልካቸው ላይ ያመጣላቸዋል፡፡ በዚህም የበለጠ ተሻሽሎ ለሁሉም ይደርሳል ባይ ናቸው፡፡

ከፋሽን ኢንዱስትሪ የወጡት ከማግባታቸው በፊት ቢሆንም አሁንም ይወዱታል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞም «እኛ ሴቶች ልብስ ለመልበስ ወይም ተውቦ ለመታየትና ፋሽን ለመከተል የግድ ኢንዱስትሪ ውስጥ መሆን የለብንም ብለው ያምናሉም፡፡ በንግድና በቢዝነስ ደረጃ አልየው እንጂ እንደማንኛዋም ሴት ጅም እየገባሁ የሰውነቴን ቅርጼን ጠብቄ አምሬ በመታየት መቀጠል እችላለሁ፡፡ ከፀጉር ጀምሮ እስከ ጥፍር ድረስ ባሉ ቁመናዎች አምሮና ተውቦ መታየት ደግሞ ግድ ነው፡፡ ይህ ሀሳብ እኔ ላይ ብቻ ሳይሆን ሁሉም ሴት ላይ ያለ ይመስለኛል፡፡ በመሆኑም በእንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ እቀጥልበታለሁ እንጂ የፈለገ ቢሆን አልወጣበትም» ይላሉ፡፡

«ሴትነትን ማዕከል ያደረገ ችግር አላጋጠመኝም። ግን ብዙ የምሰማቸው ስላሉ ሌሎቹ ሴቶች አላጋጠማቸውም ማለት አይደለም» የሚሉት ወይዘሮዋ፤ ሴቶችን የማብቃትና የስኬት ጥበብን የማጋራት የአመራርነት ዘዴን በጣም ይወዱታል፡፡ ከ70 በመቶ በላይ ሰዓታቸውን የሚያውሉትም ለሠራተኞቻቸው በተለይ ለሴት ሠራተኞቻቸው ስልጠና በመስጠት ነው፡፡ እንዲያውም የሰው ሀብት አስተዳደር የካልዲስ የሁልጊዜ መፈክር «ካልዲስ ስለሚሰፋ ሁልጊዜ ቅጥር አለ፤ ስልጠና አለ፤ ዕድገት አለ» የሚል ነው፡፡ በመሆኑም ካልዲስ ውስጥ ያሉት ሠራተኞች ቢያንስ ከ15 ዓመት በላይ አብረዋቸው የቆዩ ሲሆኑ፤ ምክንያቱ ደግሞ ትምህርት መማራቸው ነው፡፡ የሥራ ላይ ስልጠናም ማግኘታቸው፤ የሰለጠኑት ሠራተኞችም እያደጉ የአስተዳደሩን ቦታ መያዛቸው፤ ቦታውን ወደውት እንዲሰሩ አድርጓቸዋልም፡፡

«ከእኔ በዕድሜ ያነሱ ወይም እኩዮቼ የሆኑ እየመጡ እንዳንቺ ስኬታማ ለመሆን ምን ማድረግ አለብኝ ይሉኛል» የሚሉት ወይዘሮ ፀደይ፤ በእርሳቸው እሳቤ ስኬት የሚባለው ሴቶችን ማብቃት ነው፡፡ ስኬታማ ለመሆን መጀመሪያ ምን መሆን እንደምንፈልግ ማወቅ ያስፈልገናል፡ ፡ ከዚያ እርግጠኛ ከሆንን መሆን የምንፈልገው ላይ ለመድረስ መጣር ነው፡፡ ስኬት መስኩም፤ መገለጫውም ፈርጀ ብዙ እንደሆነ ያምናሉ። ለአብነትም አንዲት 50 ዓመት በትዳር የቆየች ሴት ስኬታማ ነች ብሎ ሊወሰድ የሚችልበት ሁኔታ አለ ይላሉ፡፡ ምክንያቱም ምን መሆን እንደምትፈልግ ልቧ የነገራትን ሆናለች፡፡ እሳቸው ስኬታማ እንደሚሆኑ የተረዱት ቀድመው ነው፡፡ ይህም በካልዲስ ኮፊ ሳይሆን ገና በአሮጌ ደብተራቸው ኪስ ወረቀት በመሥራት በኪሎ ለመሸጥ በሞከሩበት ንቃተ ህሊና ጊዜ ሲሆን፤ ለዚህ ደግሞ የቤተሰቦቻቸው ማበረታታት ትልቁን ድርሻ እንደሚወስድ ያወሳሉ፡፡ እንዲያውም በወላጆቿ መክሊቷን እንድታውቅ የተደረገች ሴት ስኬታማ መሆኗን ገና የምትፈልገው ላይ ሳትደርስ ታውቃለች ብለው ያምናሉ፡፡ «ያም ሆነ ይህ እኔ በግሌ ስኬታማ ነኝ የሚለው ከመነሻ መድረሻ ላይ ስደርስ ነው፡፡ ደርሰሻል ወይ ከተባልኩ ገና ጉዞ ላይ ነኝ» ይላሉ፡፡

### ማህበራዊ ሕይወት

ወይዘሮ ፀደይ 40ውን የካልዲስ ካፌ ብቻ ሳይሆን ሁሉንም ድርጅቶቻቸውን መምራት አስበው ሰርክ ከመኝታቸው የሚነሱት ከሌሊቱ 10 ሰዓት ላይ ነው። በመሆኑም በሰዓት ገብጋባ ናቸው፡፡ ከዚህ የተነሳ ስልክም አያነሱም፡፡ እንዲያውም ከዚሁ ጋር ተያይዞ አስቂኝ ገጠመኞች አሏቸው፡፡ አንደኛው ተደጋጋሚ ጊዜ እየደወሉ ስልክ ሳያነሱላቸው በመቅረታቸው ተማረው ስልክ ለእሳቸው መደወል ያቆሙት አባታቸው ዕድል ገጥሟቸው በአካል በአገኟቸው ጊዜ «መቼም ለቀብሬ አትደርሽም፤ በይ ለሰልስቴ እንዳትቀሪ» ብለው በአደራ መልክ የሚያሳስቧቸው ነው፡፡

ሁለተኛው ገጠመኛቸው ቢያንስ በቤተሰብ ደረጃ ስልክ የማንሳት ባህላቸውን እንዲያሻሽሉ ካስገደዳቸው ከትንሹ ልጃቸው ጋር የተያዘው ጉዳይ ነው፡፡ ዕለቱ ለሠራተኞቻቸው ስልጠና እየሰጡ ያለበት ጊዜ ነበር። ትንሹ ልጃቸው በተደጋጋሚ ይደውላል፡፡ እያዩ ቢያስቀምጡትም ልጁ «አስቸኳይ ነው» የሚል መልዕክት በቴክስት ያደርሳቸዋል፡፡ መደወሉንም አላቆመም፡፡ እንደምንም ብለው ሲያነሱትና የፈለገውን ሲጠይቁት «ጠረጴዛው ላይ ያለውን ቸኮሌት ልብላው ወይ» አላቸው። ተናድደው ጆሮው ላይ ስልኩን ዘጉበት። አሜሪካ ላለችው እህቱ ደወለላትና ደውላ «ለምን ስልኩን ጆሮው ላይ ዘጋሽበት» ስትላቸው እርባና ቢስ ጥያቄ ስለጠየቃቸው መሆኑን ይነግሯታል፡፡ ልጃቸው እናቷን «የሰባት ዓመት ህፃን ታዲያ ከዚህ ሌላ ምን እንዲጠይቅሽ ትፈልጊያለሽ?» አለቻቸው፡፡ ፀደይም ይሄው የሴት ልጃቸው አስተያየት ትምህርት ሆናቸውና አሁን ላይ በቤተሰብ ደረጃ የሚደወሉ ስልኮችን አልፎ አልፎም ቢሆን ያነሳሉ፡፡ ከስልኩ ወጣ ሲባል ደግሞ ማህበራዊ ሕይወት ግድ ነውና ሰዓት ቢያንሳቸውም አንዳንድ የማይቀሩ የሚሏቸው ሰርግና ለቅሶዎች ላይ ለመታደም ወደኋላ አይሉም። የወይዘሮ ፀደይ የሕይወት ገጠመኝና ተሞክሮ ዓባይን በጭልፋ ነው፡፡ ይሁንና ለእናንተ ይጠቅማል የሚለውን ጨልፈን ይህንን ያህል ከአቀበልናችሁ በቂ ነውና ለዛሬ አበቃን፡፡ ሰላም!!

ኢኮኖሚ

# ባህልና ቱሪዝም

# ‹‹የገዛ ራሳችንን ቅርሶች በውሰት ወስዳችሁ አስጎብኙ የሚሉ ሀገሮች አሉ››

**የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሙዚየም ዳይሬክተር**
**አቶ ደምረው ዳኜ**



ዳግም ከበደ

ኢትዮጵያ በአርኪዮሎጂና በታሪክ ቅርስነት መዝግባ ካሰፈረቻቸው የመስህብ ሃብቶቿ መካከል ጥቂት የማይባሉት ሃብቶች ተዘርፈው በልዩ ልዩ የዓለማችን ክፍሎች ይገኛሉ፡፡ በጦርነት፣ በህገወጥ ንግድ እና በልዩ ልዩ ምክንያቶች ከአገር የወጡ እነዚህ ሃብቶች እስካሁንም ድረስ በባእዳን እጅ ተቀምጠው የሙዚየሞቻቸው ማድመቂያ ሆነዋል፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን ለተለያዩ ጨረታዎች በሚያወጧቸው ድረገፆች ላይ በግለሰቦች በግላጭ እየተቸበቸቡም ይገኛሉ፡፡

የኢትዮጵያ መንግስት እና ዘርፉን የሚመሩት ተቋማት ሃብቶቹን በተደራጀና በሚመጥን ሙዚየም አደራጅተው ከመጠበቅ ባሻገር ተዘርፈው ከአገር የወጡ ቅርሶችን በዲፕሎማሲያዊ መንገድ ለማስመለስ ጥረቶች እንደሚያደርጉ በተደጋጋሚ ይገለጻል፡፡ በዚህና በመሳሰሉት መንገዶች ተዘርፈው የወጡ ቅርሶች የተመለሱበት ሁኔታም አለ፡፡ ይህንንም የኢትዮጵያ ብሄራዊ ሙዚየምም በተለያዩ ምክንያቶች ከአገር ወጥተው የቆዩና ባለፉት ጥቂት ዓመታት የተመለሱ ቅርሶችን በቅርቡ በጊዜያዊ አውደ ርእይ ለተከታታይ 10 ቀናት ካስጎበኘበት ሁኔታ መረዳት ይቻላል፡፡

የዝግጅት ክፍላችንም የኢትዮጵያ ቅርሶች አስተዳደር፣ የሙዚየም ስርዓትና ቅርሶች አያያዝ፣ በልዩ ልዩ ምክንያት ከአገር የወጡ ሃብቶችን ለማስመለስ ስለሚደረግ ጥረት እና ሙዚየምን የመጎብኘት ባህልን በተመለከተ ከኢትዮጵያ ቅርስ ባለስልጣን የብሔራዊ ሙዚየም ዳይሬክተር አቶ ደምረው ዳኜ ጋር ቆይታ አድርጓል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ብሔራዊ ሙዚየሙ ከውጪ የተመለሱ ቅርሶችን በቅርቡ በጊዜያዊ አውደ ርዕይ ለእይታ አቅርቧል፡፡ የእዚህ አውደ ርዕይ ዋና ዓላማ ምን ነበር?**

**አቶ ደምረው፡-** የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሙዚየም በዋናነት ከተሰጡት ተልዕኮዎች መካከል አውደ ርዕይ ማዘጋጀት ቀዳሚው ነው፡፡ ይህንን ስንል የተለያዩ አይነት አውደ ርዕዮች መኖራቸው ይታወቃል፡፡ ከእነዚህ መካከል ቋሚ የምንለው አንደኛው ሲሆን፣ በዚህም በብሔራዊ ሙዚየም በዋናው ህንፃ ውስጥ ከአምስትና አስር ዓመት በላይ ቆይታ የሚያደርጉ አውደ ርዕዮች አሉ፡፡ ይህም የተለያዩ ክፍሎች ያሉት ሲሆን፣ አርኪዮሎጂ፣ ስነጥበብና፣ ፓሎንቶሎጂን ያካትታል፡፡ ሌላኛው ተንቀሳቃሽ ኤግዚቢሽን ሲሆን በአንድ በተመረጠ ርእሰ ጉዳይ ላይ ከቦታ ወደ ቦታ እየተንቀሳቀሰ የሚታይ ነው፡፡

እኛም ይህንን መሰረት በማድረግ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ሙዚየም ያዘጋጀነው የአውደ ርዕይ አይነት ጊዜያዊ ሲሆን፣ በተለያየ ጊዜ ከአገር የወጡ ልዩ ልዩ ቅርሶችን ይዞ ለእይታ የቀረበ ነው፡፡ ከዚህ ቀደም ይደረግ የነበረው ቅርሶቹ በተመለሱበት ቀን ደማቅ ዝግጅት በማካሄድ ይፋ ማድረግ ነበር፡፡ እንዲህ አይነት ቅርሶች በጊዜያዊ አውደ ርዕይ ቀርበው አያውቁም ነበር። የመጀመሪያ በሆነው በዚህ አውደ ርዕይ ላይ ይህንን ለመስበር ተሞክሯል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በአውደ ርዕዩ ላይ የቀረቡት ቅርሶች ይዘት ምን ይመስላል? የት አገሮች ነበር የቆዩት?**

**አቶ ደምረው፡-** በዋናነት ከአራት አገራት የተመለሱ ናቸው፡፡ የተወሰኑት በህገ ወጥ መንገድ ከአገር የወጡ ናቸው፡፡ በህገወጥ መንገድ ሲባል ወይ በጦርነት ምክንያት የወጡ ቅርሶች ናቸው፡፡ ከመቅደላ በ1860 ዓ.ም የተወሰዱ ቅርሶች ይገኙበታል /ይህም ከ150 ዓመት በፊት የሆነ ነው/፡፡ በዚያን ጊዜ እንደሚታወቀው ከአፄ ቴዎድሮስ መውደቅ በኋላ በናፒር የተመራው የእንግሊዝ ጦር መቅደላን በሙሉ ዘርፏል፡፡ ከእነዚህ መካከል የተወሰኑ ቅርሶች ባለፈው ዓመት /በ2014 ዓ.ም/ ወደ ሀገር ቤት ተመልሰዋል፡፡ እነዚህ ቅርሶች የተመለሱት በእንግሊዝ አገር በግለሰቦች ለጨረታ ሊቀርቡ ሲሉ በእንግሊዝ የኢትዮጵያ ኤምባሲና አገር ወዳድ ግለሰቦች ጨረታው እንዲቆም አድርገው ባደረጉት ውይይት ነው፡፡ ሌሎችም ከኔዘርላንድ፣ ከዴንማርክና ከአሜሪካ የተመለሱ ይገኙበታል፡፡ ይህ ሊሆን የቻለው በተለይ የኢትዮጵያ ጉዳይ ያገባናል በሚሉ ትውልደ ኢትዮጵያውያንና ሌሎች አካላት ጥረት ነው፡፡

ለእይታ ከቀረቡት ውስጥም ረጅም ዘመናትን ያስቆጠሩ መስቀሎች፣ ጎራዴዎች፣ ጠልሰም ፅሁፍና ስዕል፣ የብራና መፃህፍት እና ሌሎችም ቅርሶች ይገኙበታል፡፡ በአጠቃላይ ለመጀመሪያ ጊዜ 20 የሚደርሱ ቅርሶች ለእይታ ቀርበዋል፡፡ በዚህም የተመለሱ ቅርሶች በአግባቡ እንደሚያዙና እንደሚጠበቁ ለማሳየት ተሞክሯል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በስፍራው ተገኝተን እንደተመለከትነው ተዘርፈው ከሀገር ከወጡት ሃብቶች አንፃር ተመልሶ ለእይታ የቀረበው ውስን መሆኑን ነው፡፡ ይህ ቅርሶችን ለማስመለስ የሚደረገው ጥረት ደካማ መሆኑን አያመላክትምን?**

**አቶ ደምረው፡-** ቅርስን ማስመለስ እጅግ ፈታኝ ጉዳይ ነው፡፡ በዋናነት የሚገጥመው ችግር አገራት የሚያወጡት ህግ ነው፡፡ ለምሳሌ እንግሊዝ አንዴ ቅርሶች ወደ ሀገሪቱ ከገቡ ሃብት ሆነው እንዲመዘገቡ የሚደነግግ ህግ አላት፡፡ ይህን በመሰሉ ምክንያቶች አንድ ጊዜ በሙዚየም ውስጥ ያሉትን ሃብቶች እንዳይመለሱ ፈተና ይሆናሉ፡፡

ዩኔስኮም ሆነ የተባበሩት መንግስታት ቅርስን ለማስመለስ ያወጡት ህግ ቢኖርም አብዛኛውን ጊዜ በዲፕሎማሲያዊ መንገድ የሚደረግ ጥረትን የሚያበረታቱ እንጂ አስገዳጅ ሁኔታን የሚያስቀምጡ አይደሉም፡፡ ይህ ምክንያት ነው ለእይታ የቀረቡት ቅርሶች ውስን እንዲሆኑ ያስገደደው፡፡ ይሁን እንጂ የተመለሱትም ቢሆኑ ትልቅ መልእክት ይኖራቸዋል። እነዚህ መመለሳቸው ለምሳሌ በፈረንሳይ በርካታ ቅርሶች አሉ፡፡ እነርሱ / ፈረንሳዮች/ ለመመለስ ፍላጎት እንዳላቸው ገልፀው፣ ነገር ግን ቅርሶቹ በተሻለ ሁኔታ ላይያዙ ይችላሉ የሚል ነገር ያነሳሉ፡፡ ይህን ለመሰለው አግባብነት የጎደለው አስተያየት ምላሽ ለመስጠት መሰል የማሳያ ስፍራዎችና ተጠብቀው የሚቆዩበት አግባብ እንዳለ ለማሳየት ይረዳናል፡፡

በሀገር ቤት የኢትዮጵያ ቅርስ አስመላሽ ብሔራዊ ኮሚቴ አለ፡፡ በውጪ ደግሞ ኤምባሲዎችና ትውልደ ኢትዮጵያውያን አሉ፡፡ በእነዚህ አካላት ልዩ ልዩ ጥረቶች ይደረጋሉ፡፡ ለምሳሌ በእንግሊዝ አገር በመቅደላ ጦርነት ወቅት የተዘረፉ ሃብቶችን የያዘው ሙዚየም ቅርሶቹ እንዲመልሱ ለሚቀርበው ጥያቄ የሚሰጠው ምላሽ “በጊዜያዊነት ወይም በውሰት ወስዳችሁ ለእይታ አቅርቡና መልሱ” የሚል ነው፡፡ ይሄ የራሱ አሉታዊ ትርጉም አለው። ይህ አባባል ለአገር ክብር የማይመጥንና ትርጉሙም አሉታዊ ነው፡፡ በቋሚነት ቅርሶቹን ለማስመለስ የሚደረገው ጥረት ይቀጥላል፡፡

ከዚህ በተጓዳኝ የማህበረሰቡን ግንዛቤ በማሳደግ አገር ውስጥ ያሉ ቅርሶችን በተመሳሳይ ላለማጣት የቅድመ መከላከል ስራም እንሰራለን፡፡ ከውጪ የሚገኙትን ደግሞ በዲፕሎማሲም በህግ አግባብም እንዲመለሱ ይሰራል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሙዚየም በርካታ አስርት ዓመታትን ያስቆጠረና የኢትዮጵያን ዋና ዋና ቅርሶች የያዘ ነው፡፡ ይህን ለማስፋፋት፣ ለመጠበቅ፣ የበለጠ ለማደራጀት እንዲሁም ለማልማት ምን እየሰራችሁ ነው?**

**አቶ ደምረው፡-** የኢትዮጵያ ቅርስ ባለስልጣን መስሪያ ቤት ከ200 ሺህ በላይ የቅርስ ስብስቦች አሉት። በተለይ ከሰው ዘር መገኛ ጋር የሚያያዙ እጅግ በርካታ መረጃዎችና ቅርሶች ይገኙበታል፡፡ ከዚህ አንፃር በቅርቡ የተጀመረና በእቅድ ላይ ያለ “የሰው ዘር መገኛ ሙዚየም” ለመገንባት ሃሳቡ አለ፡፡ ሃሳቡን ወደ መሬት ለማውረድ ዛሬ ሳይሆን ከረጅም ጊዜ በፊት በቀድሞው የአዲስ አበባ ከንቲባ ኩማ ደመቅሳ የአስተዳደር ወቅት ከ4 ሺህ ሄክታር በላይ ቦታ ብሔራዊ ሙዚየም ፊት ለፊት ተፈቅዶ ነበር፤ እስካሁን ድረስ ግን የቦታው ርክክብ አልተፈፀመም፡፡ ለአራዳ ክፍለ ከተማ ለሚነሱ የግል መኖሪያ ቤቶች ከ9 ሚሊዮን ብር በላይ ለካሳ ክፍያ በ2011 ዓ.ም ቢከፍልም እስካሁን ግን በልዩ ልዩ ቢሮክራሲዎች ቦታውን ማስረከብ አልቻለም፡፡

እንደምታየው ብሔራዊ ሙዚየም ካሉት ሃብቶች አንፃር አነስተኛ ነው፡፡ ከተሰራም ረጅም ጊዜን አስቆጥሯል፡፡ የተቋቋመውም በ1930ዎቹ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር እስካሁን ሊያድግና ሊደራጅ የሚገባውን ያህል ማደግ አልቻለም፡፡ ይህ የሰው ዘር መገኛ ሙዚየም ቢቋቋም ብዙውን የቅርስ ስብስብ መውሰድና በተደራጀ መንገድ ለእይታ ምቹ ማድረግ ይቻል ነበር፤ ለከተማውም ሆነ ለዘርፉ ትልቅ አስተዋጽኦ ያደርጋል። በምርምር ዘርፍ ላይ የሚገኙ የውጭ ዜጎችን ወደዚህ ለማምጣት ምቹ አጋጣሚም ይፈጥራል፡፡ ይህ ባለመሆኑ የተሻለ ነገር እንዳንሰራ አግዶናል፡፡

ከዚህ ውጭ ባሳለፍነው ዓመት ትልቅና ራሱን የቻለ ብሔራዊ ሙዚየም ይገነባል የሚል በእቅድ ላይ አለ። ይሄ በአገሪቱ ጥቅል እቅድ ላይ የተቀመጠ ነው። ይህ በቻ ሳይሆን በክልሎች የመስራት እቅድ አለ። ለምሳሌ በአፋር ክልል አካባቢ ከ2016 እስከ 2018 ለመስራት ለፕላን ኮሚሽን የተላከ እቅድ አለ፡፡ እነዚህ ሁሉ በሂደት ላይ ያሉ ናቸው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ብሔራዊ ሙዚየሙ የተፈቀደለትን መሬት ለመረከብ እንዲችል ወደ ሌሎች ውሳኔ ሰጪ አካላት አልሄደም?**

**አቶ ደምረው፡-** እውነት ለመናገር እንደ ተቋም ይህን አላደረግንም፡፡ ነገር ግን በቀድሞው የባህልና ቱሪዝም አደረጃጀት የተለያዩ ደብዳቤዎችን አጠናክረን ሰጥተን እስከ ከንቲባው ፅህፈት ቤት ለማድረስና ውሳኔ እንዲያገኝ ለማድረግ ጥረት ተደርጓል፤ ይሁን እንጂ በግሌ ይሄም በቂ ነው ብዬ አላምንም፡፡ አሁንም ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የማሳወቅ ነገር ቢኖርም፣ ጥያቄው ግን አሁንም ድረስ እንደተንጠለጠለ ይገኛል። በዚህ ምክንያት የሚፈለገውን ያህል ሄደናል አልልም። በበላይ አካላት የጎንዮሽ ስራ መሰራት ነበረበት የሚል እምነት አለኝ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ቦታው ቢፈቀድ ሙዚየሙን ለመስራት የሚያስችል በጀት አለ?**

**አቶ ደምረው፡-** እንደተባለው በአንድ ዓመት ውስጥ የሚገኝ ሳይሆን በመንግስት የሚመጣ ነው። የሰው ዘር መገኛ ሙዚየሙ የኢትዮጵያ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን የተለያየ ፍላጎት ያላቸው የውጭ አካላትም የሚሳተፉበት ነው፡፡ እንደ ምሳሌ የፈረንሳይ መንግስትን መጥቀስ ይቻላል፡፡ ሌላው ድጋፍ ማሰባሰብ የሚችል በክብርት ፕሬዚዳንቷ የሚመራ ቦርድም አለ። ስለዚህ በጀቱ ከዚህ አካባቢ የሚመጣ ነው፡፡ ከ2016 እስከ 2018 በሶስት ዓመት እቅድ እስከ 3 ቢሊዮን ብር በጀት ተጠይቆበታል፡፡ ስለዚህ ስራው ቢጀመር በጀት ከውጪም ከውስጥም ሊገኝ ይችላል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- አሁን ያለው ብሔራዊ ሙዚየም ለአገር ውስጥም ሆነ ለውጭ ጎብኚዎች ተደራሽ እንዲሆን ምን እየሰራችሁ ነው?**

**አቶ ደምረው፡-** በአገር ውስጥ የጉብኝት ባህል ደካማ ነው፡፡ ይሄ አገራዊ ችግር ነው፡፡ የክበባትና አገርህን እወቅ እንቅስቃሴዎች ከዚህ ቀደም የነበሩ ቢሆንም፣ አሁን ተቀዛቅዟል፡፡ በተለይ ከዚህ አንፃር ብሔራዊ ሙዚየም ላይ ብዙ የሰራነው ስራ የለም፤ የሚዋሽ ነገር የለውም፡፡

በቀጣይ ግን በሙዚየሙ በር ላይ አንድ ራሱን የቻለ ትልቅ ስክሪን የማቆም ሃሳብ አለን፡፡ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ተግባራዊ የሚሆኑ ሁለት አዳዲስ አሰራሮችንም እየተከተልን ነው፡፡ የመጀመሪያው የብሔራዊ ሙዚየም የገበያና ፕሮሞሽን የስራ ክፍል አለ፡፡ በዚህ መንገድ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን ለመድረስ በቅንጅት ለመስራት እያሰብን ነው፡፡ ከዚህ ውጭ አሁን ተቀርፆ ተግባር ላይ የሚውለው የትምህርት ስርዓት “የተግባር ትምህርትን” የሚያበረታታ ስለሆነ ጎብኚዎች ወደ ብሔራዊ ሙዚየም በስፋት እንዲመጡ የሚያበረታታ እንደሆነ እናምናለን፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ለቃለ ምልልሱ ሳደረጉልን ትብብር በእጅጉ እናመሰግናለን!**

**አቶ ደምረው፡-** እኔም አመሰግናለሁ!!

ስፖርት እና መዝናኛ

# ሳምንቱን በታሪክ

## የበጋው መብረቅ




ሌተናል ጀኔራል ጃገማ ኬሎ

**ጃገማ ገና በለጋ እድሜው «አባቱ የመረጠው« እየተባለ ለዳኝነት መቀመጥን፣ ፈረስ ግልቢያን፣ ጦር ውርወራን፣ ምክክቶሽን፣ ጋሻ አነጋገብን፣ ረሀብንና ውሃ ጥምን መቋቋምን፣ ውሃ ዋናን ... እየተማረ በጥሩ ስነ ምግባር ያደገ ነው**

**ዋለልኝ አየለ**

«ስም ከመቃብር በላይ ይውላል» የሚባለው ዝም ብሎ አባባል ብቻ አይደለም፡፡ የሚናገረው ትልቅ መልዕክት ስላለ ነው፡፡ ከመቃብር በላይ የሚውለው ስም ከመቃብር በታች የሆነውን ሥጋ ሕያው ያደርገዋል፡፡ «ጀግና አይሞትም!» የሚባለው ለዚህ ነው፡፡ ጀግና አይሞትም ሲባል በሥጋ ቢያርፍም በሥራው ሕያው መሆኑን ለመግለጽ ነው፡፡ ሕያው ነው ማለት በሠራው ሥራ ሌሎችን ያሰራል ማለት ነው፡፡ የዓድዋ ጀግኖቻችን ዛሬ በሕይወት የሉም። ሥራዎቻቸው ግን ዛሬም የጀግንነት ወኔ እንዲኖር አድርገዋል፡፡

በዛሬው ሳምንቱን በታሪክ ዓምዳችን በጀግንነታቸው ስማቸው ከመቃብር በላይ ሆኖ ሕያው ካደረጋቸው ጀግኖች የዚህ ሳምንት ክስተት የሆነውን እናስታውሳለን፡፡

ይህ ሳምንት አንድ ታላቅ ጀግና ያስታውሰናል። በፋሽስት ጣሊያን ወረራ ጊዜ የአገራቸውን ነፃነት ለማስጠበቅ የተዋጉና በኢትዮጵያ የአርበኝነት ታሪክ ውስጥ ደማቅ ስም ያላቸው ጀግና ናቸው፡፡ ለዚህም ጀግንነታቸው «የበጋው መብረቅ» የሚል ቅጽል ስም ተሰጥቷቸዋል፡፡ የበጋ መብረቅ ልዩ ክስተት እንደማለት ነው፡፡

እኚህ ጀግና ሌተናል ጀኔራል ጃገማ ኬሎ ናቸው። ያረፉት ከስድስት ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት መጋቢት 29 ቀን 2009 ዓ.ም ነው፡፡

ሌተናል ጀኔራል ጃገማ ኬሎ የተወለዱት ጥር 21 ቀን 1913 ዓ.ም በቀድሞው አጠራር በጅባትና ሜጫ አውራጃ፣ በደንዲ ወረዳ ዮብዶ በተባለ ስፍራ ነው። አባታቸው ኬሎ ገሮ (አባ ጃገማ) የሕፃኑ ጃጋማ መወለድ እጅግ ከፍ ያለ ደስታ አሳደረባቸው፡፡ « ... ለሰባ ዓመታት ሙሉ የጠበቅሁት አንበሳ ይህ ነው ... የፈረሴን ስም ሰጥቼዋለሁ» ብለው «ጃገማ» ብለው ስም እንዳወጡለት ይነገራል፡፡

ሕጻኑ ጃጋማ በተወለደ በዓመቱ እናቱ ወይዘሮ ደላንዱ በአካባቢው ተከስቶ በነበረ በሽታ ምክንያት በመሞታቸው በአክስቱና በሞግዚት እንዲያድግ አባቱ ወሰኑ፡፡ አክስቱም ጃገማን ከወንድሙ ጋር ፀበል አስጠምቀው፤ ቄስ ቀጥረው ዳዊት እንዲማር አደረጉ። በ1923 ዓ.ም ደግሞ አባቱ ኬሎ ገሮ (አባ ጃገማ) አረፉ፡፡

ጃገማ ገና በለጋ እድሜው «አባቱ የመረጠው» እየተባለ ለዳኝነት መቀመጥን፣ ፈረስ ግልቢያን፣ ጦር ውርወራን፣ ምክክቶሽን፣ ጋሻ አነጋገብን፣ ረሀብንና ውሃ ጥምን መቋቋምን፣ ውሃ ዋናን ... እየተማረ በጥሩ ስነ ምግባር አደገ፡፡ በልጅነት ዘመኑ ስለቅድመ አያቱ ጎዳና ነሞ የጀግንነት ታሪክ በተደጋጋሚ ስለሰማ እርሱም እንደቅድመ አያቱ ጀግና መሆንን ያልም ነበር፡፡

ፋሺስት ኢጣሊያ በ1928 ዓ.ም ኢትዮጵያን ስትወር ጃገማ ገና በ15 ዓመቱ አርበኛ ሆኖ የፋሺስትን ጦር ለመፋለም ወሰነ፡፡ ከአጎቱ ልጅ አሰፋ አባ ዶዮ ጋር ወደ ጫካ ገቡ፡፡ እህቱና ወንድሞቹም ተከተሉት። ገበሬዎች፣ ወታደሮች፣ ሾፌሮች ... ከጃገማ ጋር ተቀላቀሉ፡፡ አሰፋ አባ ዶዮን ጨምሮ መጀመሪያ ከጃገማ ጋር ለአርበኝነት የወጡ ብዙ ወጣቶች በቤተሰቦቻቸው ተግሳፅ አማካኝነት ከጫካ ወጥተው ወደ መንደራቸው ቢመለሱም ጃገማ ከእርሱ በእድሜም ሆነ በሌሎች ነገሮች የሚበልጡ በርካታ ሰዎችን በስሩ ማሰለፍ ቻለ፡፡

የጃጋማ አባት በአካባቢው ዘንድ ይወደዱና ይከበሩ ስለነበር የአካባቢው ሕዝብ በታዳጊው ጃገማ የሚመሩትን አርበኞች በልዩ ልዩ መንገዶች ያግዝ ነበር፡፡ አርበኞቹም በፋሺስት ጦር ላይ ድንገተኛ ጥቃት በመሰንዘር ጦሩን መፈተን ጀመሩ። ፋሺስቶች ጥይት የሚጭኑባቸውን እንስሳት በመምታት ፋሺስቶችና ባንዳዎች ሲሸሹ አርበኞቹ መሳሪያና ጥይት እየሰበሰቡ ማከማቸት ቀጠሉ። ጣሊያኖችም ጃገማንና ተከታዮቹን ለመደምሰስ ቢሞክሩም አልተሳካላቸውም፡፡

አርበኞቹ በጊንጪና አካባቢው በነበረው የፋሺስት ጦር ላይ ተደጋጋሚ ጥቃት በመሰንዘራቸው ጣሊያኖች በጊንጪና በአካባቢው ጠንካራ ምሽግ ሰርተውና ጦራቸውን ጠምደው ተቀመጡ፡፡ ሐሮታና ጀልዱ የነበረው የጠላት ጦር ግንኙነት ፈጥሮ ስለነበር አርበኞቹ መተላለፊያ መስመሩን ለመቁረጥ ጥቃት ሰነዘሩ፡፡ ከጥቃቱ ባገኙት መሳሪያም ትጥቃቸውን አጠናከሩ፡፡ የጃገማ ተከታዮች ቁጥራቸው ጨመረ፡፡ ፋሺስቶች ተጨማሪ ምሽጎችን ለመገንባት ቢያስቡም ቀድመው በገነቧቸው ምሽጎች ውስጥም እንደልባቸው መንቀሳቀስ ሳይችሉ ቀሩ፡፡ አርበኞቹ በሚያዝያ ወር 1931 ዓ.ም ሐሮታና ጀልዱ የነበረውን የጠላት ጦር ግንኙነት ለመበጣጠስ የወሰዷቸው እርምጃዎች አዲስ አበባ ድረስ ተሰሙ፤ ብዙ የነፃነት ተዋጊዎችም እነጃገማ ያሉበት ድረስ ሄደው ተቀላቀሉ፡፡

በጃገማ የሚመራው የአርበኞች ጦር ምዕራብ ሸዋ በነበረው የኢጣሊያ ጦር ላይ ተደጋጋሚ ጥቃት በመክፈት ብዙ ጉዳቶችን አደረሰበት፡፡ አርበኞቹ ድንገተኛ ጥቃቶችን ሰንዝሮ በፍጥነት ከአካባቢው በመሰወር የጠላት ጦር ጥይት እንዲያባክን በማድረግ፣ የአካባቢው ሰው ከፋሺስት ወታደሮችና ከባንዳዎች ላይ ጥይት እንዲገዛ በማስተባበርና ጥይት በጫኑ እንስሳት ላይ ጥቃት ፈፅሞ ጥይቱን በመውሰድ የመሳሪያ ክምችታቸውን ያጠናክሩ ነበር፡፡

በጥቅምት ወር 1933 ዓ.ም ጃገማን ለማጥቃት ወደ ሰንጎታ ተራራ የሄደው 350 የፋሺስት ጦር ጃገማ በሚመራቸው 17 አርበኞች ተሸነፈ፡፡ የጃገማ አርበኞች ብዙ የጠላት ወታደሮችን ገደሉ፤ ባንዳዎች የዘረፉትን ንብረት አስመለሱ፤ወታደሮችንና መሳሪያ ማረኩ፡፡ የጃገማ ጀግንነትም እየገዘፈ ሄደ። የአካባቢው ሕዝብም የጃገማን ጀግንነት ከቅድመ አያቱ ጀግንነት ጋር እያነፃፀረ በማውራት በጠላት ጦር ካምፕ ውስጥ ፍርሃቱ እንዲጨምር አደረገ። ወደ ወሊሶ ሄዶ በአካባቢው ከፋሺስት ጦር ጋር ሲዋጉ ወደነበሩት ወደ ደጃዝማች ገረሱ ዘንድ ሄደ፡፡ የፋሺስት ጦር በደጃዝማች ገረሱ ላይ ውጊያ ከፍቶ ስለነበር ጃገማም በውጊያው ላይ ተሳትፎ የማታ ማታ ድሉ የአርበኞቹ ሆነ፡፡ ደጃዝማች ገረሱም « ... አንተን የመሰለ ጀግና የወለደች እናት ትባረክ ...» ብለው ጃገማን አመሰገኑት፡፡

ጃገማ በአንድ ውጊያ ላይ የማረከውን የኢጣሊያ ወታደር እንዳይገደል አድርጎ ስለአርበኞቹ ኃይል እንዲሁም ስለፋሺስቶች ፈሪነትና አረመኔነት ከነገረው በኋላ «ከምርኮኝነት ነፃ የምትወጣው ለጥይት መግዣ የሚሆነኝን 10 ሺህ ሊሬ ከከፈላችሁኝ ብቻ ነው» አለው፡፡ በአንድ ኢጣሊያዊ መልዕክተኛ አማካኝነት ጃገማ 10 ሺህ ሊሬ ተቀብሎ ምርኮኛውን ፈታው፡፡ ምርኮኛውም ወደ ጦር ሰፈሩ ሄዶ ስለጃገማ ጀግንነት ለአለቆቹ ሲነግራቸው ደስ ባለመሰኘታቸው ወደ ሌላ ስፍራ አዛውረውታል፡፡

ጃገማ በአርበኝነት ዘመኑ ከፈጸማቸው አኩሪ ገድሎች መካከል የፋሺስት ጦር ይመካበት የነበረው የአዲስ ዓለም ምሽግ ሰበራ ፈፅሞ የሚዘነጋ አይደለም። ጃገማ ደጃዝማች ገረሱን ለመርዳት ወደ ወሊሶ ሄዶ በነበረበት ወቅት « ... ጃገማ ያን የተመካከርንበትን ጉዳይ ጨርሻለሁና ዛሬ ነገ ሳትል ሰራዊትህን ይዘህ ቶሎ ና ...» የሚል መልዕክት ከስመ ጥሯ የውስጥ አርበኛ ወይዘሮ ሸዋረገድ ገድሌ ደረሰው፡፡ ጃገማም በፍጥነት ወደ አዲስ ዓለም አቅንቶ የምሽግ ሰበራው የጦር አዝማች ሆነ፡፡ ጥቃቱን አፈፃፀም የሚያሳይ መመሪያ ለባልደረቦቹ አስረድቶ የሥምሪት ትዕዛዞችን ሰጠ፡፡ ራሱ ምሽጉ ውስጥ ገብቶ ቦምብና ሌሎች መሳሪያዎችን ይዘው የነበሩ የፋሺስት ጦር ባለስልጣናትን ገድሎ የመሳሪያ ዝርፊያው እንዲፈጸም አደረገ፤ እስረኞችንም አስፈታ፡፡ በዘመቻው ላይ ከአርበኞቹ ወገን የሞቱት ሁለት ሰዎች ብቻ ነበሩ። ከጠላት ወገን ግን ከ100 በላይ ጣሊያናውያንና ጠባቂዎቻቸው ተገድለዋል፡፡

በመጋቢት ወር 1933 ዓ.ም ጃገማ የጭልሞን ምሽግ ከቦ በፋሺስት ጦር ላይ ተኩስ ከፈተ። «እጃችሁን ካልሰጣችሁ አንላቀቅም!» የሚል መልዕክትም አስተላለፈ፡፡ «እንደራደርና እጅ እንሰጣለን» ካሉ በኋላ አዘናግተው ሊያመልጡ ሲሉ ከአርበኞቹ ተኩስ ተከፈተባቸውና 13 የኢጣሊያ ወታደሮችና አንድ ሺህ 500 ባንዳዎች ተማረኩ፡፡ ጊንጪ በጃገማ አርበኞች ቁጥጥር ስር ዋለች፡፡ ወዲያውኑም ጃገማ የኢጣሊያ ጦር የሚተማመንበት የሐሮታ ምሽግ ላይ ጥቃት እንዲከፈት አዘዘ፡፡ የጠላት ጦር አንድ ጊዜ እየሸሸ፤ ሌላ ጊዜ እያጠቃ መፋለሙን ቀጠለ፡፡ በዚህ ጊዜ ጃገማ ብቻውን ሆኖ ቦታ እየቀያየረ መድፍ ሲተኩስ የፋሺስት ጦር ተስፋ ቆርጦ ለመጨረሻ ጊዜ ሸሸ፤ ከሞት የተረፈውም ተማረከ፡፡ የጃገማ ጦር በድል አዲስ ዓለም ገባ፡፡ ሆለታንም በቁጥጥሩ ስር አደረገ።

ከግንቦት 1934 ዓ.ም ጀምሮ ሆለታ ገነት ጦር ማሰልጠኛ ትምህርት ቤት በመግባት የውትድርና ስልጠና አጠናቆ የሻለቃነት ማዕረግ አገኘ፡፡ ከዚያም ለጥቂት ጊዜያት ያህል በአምቦና በቢሾፍቱ ተመድቦ አገልግሏል፡፡ ከዚያም በአምባላጌና በራያ አዘቦ በግዳጅ አፈፃፀም ላይ ባሳየው ብቃት በሜጀር ጀኔራል አበበ ዳምጠው ተመስክሮለት ሻለቃ ጃገማ የብርጌድ አዛዥ ሆኖ ተሾመ፡፡

በ1947 ዓ.ም የሌተናንት ኮሎኔልነት ማዕረግን አገኘ፡፡ የዩጎዝላቪያ ፕሬዝደንት የነበሩት ማርሻል ቲቶ ኢትዮጵያን በጎበኙበት ወቅት የተደረገላቸውን የክብር ሰልፍ የመሩት ሌተናንት ኮሎኔል ጃገማ ነበሩ፡፡

በ1953 ዓ.ም የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ወቅት የመፈንቅለ መንግሥቱን ሙከራ ለማክሸፍ ለጥቃት የተንቀሳቀሰው ኃይል አዛዥ ሌተናንት ኮሎኔል ጃገማ ኬሎ ነበሩ፡፡ በ1958 ዓ.ም የሜጀር ጀኔራልነት ማዕረግን አግኝተዋል፡፡ በ1965 ዓ.ም ደግሞ የብሔራዊ ጦር አዛዥ ሆነው ተሹመዋል፡፡

በፈረስ ስማቸው «አባ ዳማ» የሚባሉት፣ ሌተናንት ጀኔራል ጃገማ አንድ ወንድና አምስት ሴት ልጆችን አፍርተዋል፡፡ ጀግናው ሌተናንት ጀኔራል ጃገማ ኬሎ መጋቢት 29 ቀን 2009 ዓ.ም አርፈው፣ ሥርዓተ ቀብራቸው ልክ በዛሬዋ ቀን እና በዛሬዋ ዕለት እሑድ ሚያዝያ 1 ቀን 2009 ዓ.ም በአዲስ አበባ መንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ተፈጽሟል፡፡

# የዝነኞች ገጽ

# የኢትዮጵያ ረቂቅ ሙዚቃ እናት

**ሙሉጌታ ብርሃኑ**



እማሆይ ጽጌ ማርያም ገብሩ

እማሆይ ጽጌ ማርያም ገብሩ፣ ምናልባት ይህን ስም ሲጠራ የሰማ ሰው አንዲት ገዳም ገብተው የመነኮሱ፣ ዓለማዊ ሕይወት በቃኝ ብለው የመነኑ ሴት ስለመሆናቸው ብቻ ያስብ ይሆናል። እርግጥ ነው እንዲህ ቢታሰብ ስህተት አይደለም፡፡ ነገር ግን እማሆይ ጽጌ ማርያም ከዚህም፣ ከሚባለውም ሆነ ከተባለው በላይ የረቀቁ የተለዩ መነኩሲት ናቸው። የግላቸው ብቻ የሆነና እሳቸው ብቻ የኖሩት የተለየ የሕይወት ዘይቤን ተከትለው ያለፉ፣ ለብዙ ነገሮች የመጀመሪያዋ ሴት መሆን የቻሉ ድንቅ ኢትዮጵያዊት ናቸው።

አንዲት ዓለም በቃኝ ብለው የመነኑ መነኩሲትን ከሙዚቃ መሳሪያ ፊት ስንመለከት ያልተለመደ ነገር በመሆኑ ግራ ሊገባን አሊያም ግርምትን ሊያጭርብን ይችላል። ነገር ግን እማሆይ ጽጌ ማርያም የኖሩት ሕይወት ነው። ብርቱዋ መነኩሴ ብዙ የማይቻሉ የሚመስሉ ነገሮችን ሆነውና ኖረው አሳይተዋል። ለመሆኑ እኚህ ሴት ማናቸው? አንዲት መነኩሲትና ሙዚቃስ እንዴት ተዋወቁ? የእኚህን ሴት ዝና ከብዙ በጥቂቱ እናውጋ።

እማሆይ ጽጌ ማርያም ገብሩ ከምንም በላይ የኢትዮጵያ የረቂቅ ሙዚቃዎች እናት ናቸው። 1916 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ ከእናታቸው ወይዘሮ ካስዬ የለምቱና ከአባታቸው ከንቲባ ገብሩ ተወለዱ። አባታቸው ገብሩ የጎንደር ከተማ ከንቲባ ነበሩ። እማሆይ በወቅቱ የባለስልጣን ልጅ እንደመሆናቸው በልጅነታቸው እንደ አብዛኛው ኢትዮጵያዊ ልጅ ሆነው ቢያድጉም፣ እንደ አብዛኛው ኢትዮጵያዊ ልጅ የኑሮ ችግርና መከራን ቀምሰዋል ለማለት አያስደፍርም። ምክንያቱ ደግሞ ሁሉ ነገር ሞልቶ ከተትረፈረፈበት ቤተሰብ ውስጥ ነበር ተወልደው ያደጉት። መቼስ የሰው ልጅ ሁሉን አያድለውምና የሚወዷት ሙዚቃ ከወቅቱና ከጊዜው ሁኔታ አንጻር አልጋ በአልጋ ልትሆንላቸው አልቻለችም ነበር። እሳቸው በቻሉት አቅም ሁሉ በእጃቸው ጭምር እየዳሁ የሙዚቃን የቀሚስ ጫፍ ለመያዝ ሲታገሉ በተቃራኒው ሙዚቃ እየሸሸቻቸው ብዙ ውጣ ውረድን አይተውባታል። ቢሆንም ግን ሽሽታ ልትሰወርባቸው አልፈለገችም ነበርና እሳቸው በተስፋ መቁረጥ ውስጥ ሆነው እንኳን ዳግም እየመጣች ትቀሰቅሳቸዋለች። እንደገና ሌላ የተስፋ ብርሃን ታሳያቸውና አሁንም እንዲከተሏት ታደርጋቸዋለች። የሙዚቃ ሕይወታቸው ሙሉ በመውደቅ መነሳት የታጨቀች ነበረች። በዚህ ሁሉ መሃል እማሆይ ምናልባትም የታላቁ የሙዚቃ ጥበበኛ የያሬድን ታሪክ ሳያስታውሱ አይቀሩም። ሙዚቃ በመውደቅ መነሳት፣ እንደገናም መውደቅ ደግሞም የመነሳት ውጣውረዶች ውስጥ በብዙ ትዕግስት የምትገኝ ጣፋጭ ፍሬ ናትና።

የእማሆይ የሙዚቃ ጉዞ የሚጀምረው መነኩሲት ከመሆናቸው ብዙ አመታትን ቀደም ብሎ ገና የስድስት አመት ልጅ ሆነው ነበር። የስድስት አመት ልጅ ሆነው የዘመናዊ ትምህርት ለመከታተል ከአዲስ አበባ ወደ ጅቡቲ በባቡር አቀኑ። ጅቡቲ ከደረሱ በኋላም የጉዞ መስመራቸውን ከሃዲድ ወደ ባህር በመቀየር በመርከብ ተሳፍረው እያቆራረጡ የሲውዘርላንድ ምድር ላይ አረፉ። እዚያም የአዳሪ ትምህርት ቤት ውስጥ በመግባት የዘመናዊ ትምህርታቸውን መከታተል ጀመሩ። በአዳሪ ትምህርት ቤቱ ውስጥ ሳሉ የምዕራቡን ዓለም የክላሲካል ወይንም በሙዚቃ መሳሪያ ብቻ የተቀናበረ ሙዚቃ በተደጋጋሚ ከጆራቸው ይገባ ነበር። እናም እለት እለት በሰሙት ቁጥር የልባቸውን አጥር እየነቀነቀ የሙዚቃው አፍቃሪ ሆነው ቀሩ። ከማፍቀርም አልፈው የሙዚቃ መሳሪያው ባለበት ሁሉ እያሳደዱ በልባቸው ያለውን ፍቅር በጣቶቻቸው መደርደር ጀመሩ። የሙዚቃ ፍቅራቸው እየጨመረ፣ የማወቅ ጉጉታቸውም እየነጎደ ሄደና ሳያስቡት ከሙዚቃ ከተማ ውስጥ ራሳቸውን አገኙት። ከዚህ በመሳሪያ ብቻ የተቀናበረ (ክላሲካል) ሙዚቃ ጋርም ተዋወቁ። ከሀገራቸው የዘመናዊ ትምህርትን ለመከታተል ወደ ሲውዘርላንድ የሄዱት እማሆይ ጽጌ ማርያም የሰብዓዊ ትምህርትን ያጠኑ ሲሆን ከሙዚቃው ጋር በነበራቸው ቆይታ ደግሞ ቫዮሊንን መጫወት ቻሉ። ከመጫወትም አልፈው ገና የዘጠኝ አመት ልጅ ሳሉ አንድ ትርኢት ላይ በመሳተፍ ችሎታቸውን ለማሳየት ችለዋል።

ገና በለጋ የልጅነት እድሜያቸው ከኢትዮጵያ የወጡት እማሆይ የነበራቸውን የሲውዘርላንድ ቆይታ አጠናቀው ውብ ኮረዳ ልጃገረድ ሆነው ወደ ሀገራቸው ተመለሱ። ወደ ኢትዮጵያ ከገቡ በኋላ የሙዚቃ ፍቅር ለሚያናውዛቸው ለእኚህ ሴት ብዙ ሁኔታዎች ጥሩ አልነበሩም። በዚያን ጊዜ ሴት ልጅ ሙዚቃ ለመጫወት አይደለም በቅጡ እንደፈለገች ከቤት ወጥታ ለመግባትም ሆነ የዘመናዊ ትምህርት ለመከታተል ይናፍቃት ነበር። የዚያን ጊዜ ሙዚቃ በሴቷ አይደለም በወንዱም እጅ የማያምርና ለማህበረሰቡ ጆሮ የማይጥም ጉዳይ ነበር። እማሆይም ይህንን ተቋቁመው እድል አግኝተው የሙዚቃ ጥማቸውን ለማርካት ትልቅ እንቅፋት ሆነባቸው። በማይሆን ጊዜ በሙዚቃ ፍቅር ወደቁና ከማይሆን የሙዚቃ በረሃ ንዳድ ጋር ትግል ገጠሙ። እንደ ውሃ ጥም ከሚቃጠሉበት በረሃ አምልጠው ለመውጣት ብዙ ትግል ቢያደርጉም አሸዋው እያንሸራተተ መልሶ ይጥላቸው ጀመር። ከሙዚቃው ፍትጊያ ባሻገርም ሌላ የሕይወት ቀውስ ሰተት ብሎ ወደ እሳቸው መጣ። ጊዜው የጣሊያኑ ፋሽስት ኃይል ኢትዮጵያን ለመውረር ትግል የገጠመበት ነበር። እማሆይም ከመላ ቤተሰባቸው ጋር በመሰደድ የጥቁር አንበሳ ጦርን ተቀላቀሉ። በጦርነቱም በሽምቅ ውጊያ ሲፋለሙ የነበሩት ሶስት ወንድሞቻቸው ተገደሉ። ጦርነቱ ሲፋፋምም ቤተሰባቸው በሙሉ ተግዘው ወደ ኔፕልስ፣ ጣሊያን በግዞት ተወሰዱ። ኋላም ኢትዮጵያ አሸንፋ ከጦርነቱ ወላፈን ሀገር ምድሩ ቀዝቀዝ ሲል ወደ ሀገራቸው እንዲመለሱ ተደረገ።

ከዚህ በኋላም ቢሆን የሙዚቃ ፍቅሩ ያልበረደላቸው እማሆይ ጽጌ ማርያም በሀገር ውስጥ አልሆን ቢላቸው ጊዜ ወደ ውጭ ሄደው የሚማሩበትን ሌላ እድል የማግኛ መንገድ ሲያሰላስሉ ቆዩና በመጨረሻም የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት ጸሐፊ ሆነው ተቀጠሩ። የሙዚቃን መግቢያ በር በዚህ አገኛለሁ ብለው የገቡበት መንገድም ሳይሳካ ቀረ። ለስራ ሳይሆን ሙዚቃን ፍለጋ ነበርና የገቡት፣ ይሄኔ ላይ ታቹን ቢያዩ ምንም ጠብ የሚል ነገር ጠፋ። ከሀገር ውጭ ወጥተው ሙዚቃ ለመማር የሚያስችላቸውን የይለፍ ፈቃድ ተከለከሉ። ከዚያ የራሱ ጉዳይ ሲሉ ስራውን ለቀው ወጡ። ተስፋ በመቁረጥ ውስጥ ተስፋን መቁረጥ የተሳናቸው እኚህ ሴት እንደምንም ብለው አባታቸውን በማሳመን በ21 አመታቸው ከያኔው ታዋቂ ቫዮሊን ተጫዋች አሌክሳንደር ኮንትሮዚ ስር ሙዚቃን ለመማር ወደ ግብጿ ካይሮ ከተማ በማቅናት የሙዚቃ ትምህርታቸውን ቀጠሉ። የሙዚቃ ሕይወት እማሆይን የምትፈትነው እያስተማረች ቢሆንም ፈተናው ግን ማብቂያ አነበረውም። ከካይሮ ከትመው የሙዚቃ ትምህርታቸውን ገና ከመጀመራቸው የጤና እክል ገጠማቸውና አቋርጠው በድጋሚ ወደ ሀገራቸው ለመመለስ ተገደዱ።

አሁን ግን እኚህ ታላቅ ሴት ትግላቸውን የምርም ለማቆም የወሰኑ ይመስላሉ። ሁለተኛው የሕይወት ምርጫቸውም የሚጀምረው እዚህ ጋር ነው። 1940 ዓም በወቅቱ የ25 አመት ኮረዳ ነበሩ። የዛኔ ስማቸው እማሆይ ጽጌ ማርያም ገብሩ አልነበረም። የውብዳር ገብሩ ተብለው ነበር የሚጠሩት። ከዚያ ሁሉ ውጣውረድ ተላቀው ቀሪውን የሕይወት ዘመን ለፈጣሪያቸው ለመስጠት ወሰኑ። ሁሉንም ተውና ወደ ግሸን ማርያም ገዳም መነኑ። ከሁለት አመታት በኋላም አዲስ ማንነትን ይዘው በአዲስ የምናኔ ስም መጡ። በዚያው የግሸን ማርያም ውስጥ የውብዳር የሚለውን የዓለም ስማቸውን ገፈው ወደ ጽጌ ማርያም ቀየሩ።

በንጉሥ ኃይለሥላሴ ዘመን እማሆይ ጽጌ ማርያም የከንቲባ ልጅ እንደመሆናቸው የተለያዩ ትላልቅ ዝግጅቶች በሚኖርበት ወቅት ይጠሩ ነበር። ብዙ ጊዜም ንጉሡ ፊት እየቀረቡ ያንጎራጉሩላቸው ነበር። እማሆይ ከመነኑ ከአመታት በኋላ ወላጅ አባታቸው በጠና መታመማቸውን ሰምተው ቢመጡም ከንቲባ ገብሩን ግን በሕይወቱ አላገኟቸውም። ንጉሡም እማሆይን በማስጠራት ምን እንደሚፈልጉ ጠየቋቸው። እማሆይም ከእናታቸው ጋር አብረው ወደ ኢየሩሳሌም መሄድ እንደሚፈልጉ ገለጹላቸው። ከእናታቸውም ጋር ወደዚያው በማቅናት ቆይታቸውን በቤተክርስቲያንና በገዳማት አደረጉ። በቤተክርስቲያን ውስጥም በአስተርጓሚነት ያገለግሉ ነበር። ኑራቸውንም አንዴ ኢትዮጵያ አንዴ እስራኤል ሀገር እያሉ ቢቆዩም ከ1975 ዓ.ም ወዲህ ግን ወደ ኢትዮጵያ አልተመለሱም ነበር።

እማሆይ ጽጌ ማርያም በ1959 ዓ.ም በጀርመን ሀገር ሆነው የመጀመሪያውን የሀገራችንን የፒያኖ የረቂቅ ሙዚቃ ሸክላ አሳትመዋል። በኢትዮጵያ የሙዚቃ ታሪክ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ የኢትዮጵያን ሙዚቃ በሸክላ ያስቀረጹት ነጋድራስ ተሰማ እሸቴ ሲሆኑ፣ እማሆይ ፅጌ ማርያም ደግሞ የኢትዮጵያን ክላሲካል ሙዚቃዎችን በሲዲ በማስቀረጽ ለዓለም ሕዝብ ያስተዋወቁ የመጀመሪያዋ እንስት ሆነዋል። እንዲያው እሳቸው በሁሉም ነገር የመጀመሪያዋ ሴት መሆን አይታክታቸውምና ከሙዚቃው ሌላም በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ለመስራት እንዲሁም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ-ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ በይፋ መዝሙርን የዘመሩ የመጀመሪያዋም ሴት ጭምር ናቸው። እንግሊዝኛ፣ ጀርመንኛ፣ ዕብራይስጥኛ፣ አማርኛና ግዕዝን ጨምሮ ወደ 7 የሚጠጉ ቋንቋዎችን አቀላጥፈው የሚናገሩ ሲሆን እድሜያቸው ገፍቶ ካረጁ በኋላ እንኳን መኪና ማሽከርከርና ፈረስ መጋለብ ያዘወትሩ ነበር። የተለያዩ የሙዚቃ ስራዎቻቸውንም በተለያዩ ኮንሰርቶች ላይ በማቅረብ የሚገኘውንም ገንዘብ ለድሆች መርጃ አውለዋል። ከእነዚህም አንዱ የ1966 ዓ.ም በድርቅ ለተጎዱ ወገኖች መርጃ እንዲውል 'ደ ፋሚን ዲዛስተር' የተሰኘው የሙዚቃ ስራቸው ነው። በፈረንጆቹ ሚያዚያ 17 ቀን 2017 ዓ.ም የ93 አመት አዛውንት ስለነበሩት እማሆይ ጽጌ ማርያም ዘጋርዲያን 'ቤት-አልባዋ ከርታቴ' በሚል አርዕስት ሰፊ ሀተታ ይዞ ወጥቶ ነበር። በሀተታውም የልዩ ተሰጥኦ ባለቤት ስለሆኑት ስለ እኚህ የ93 አመት አዛውንት በደንብ አድርጎ ከትቦላቸዋል።

የረቂቅና ጥዑም ሙዚቃ እናት የነበሩት እማሆይ ጽጌ ማርያም በርከት ያሉ የረቂቅ ሙዚቃ አልበሞችን አሳትመዋል። 'ኢትዮ ፒክ' የተሰኘው አልበምም ከቀድሞ ቅንብራቸው የተመረጡ ስራዎች የተካተቱበት የመጨረሻው አልበማቸው ነበር። ከመነኮሱ በኋላ አብዛኛውን ጊዜያቸውን በእግዚአብሔር ቤትና በኢየሩሳሌም ያሳለፉ ቢሆንም በተለያዩ ጊዜያት ኮንሰርቶችን ከማዘጋጀት አልቦዘኑም ነበር። የሚያቀርቧቸው ስራዎችም በፒያኖና ቫዮሊን አማካኝነት ሲሆን አስቀድመው በቂ ዝግጅት በማድረግ በተጠና መልኩም ነበር። ጆሮውን ከፍቶ ሙዚቃቸውን ለሚያደምጥም በችሎታቸው እጅን በአፍ የሚያስጭኑ ድንቅ የሙዚቃ እናት ነበሩ።

የሙዚቃ ሕይወታቸው እጅጉን ፈተና የበዛባትና በውጣ ውረዶች የተሞላች ባትሆን ኖሮ ምናልባትም ከነሞዛርት እኩል ዛሬ ዓለም በሙዚቃው ከምታወድሳቸው ሰዎች መሃከል አንዷ እማሆይ ጽጌ ማርያም በሆኑ ነበር። ያም ሆነ ይህ ግን ዛሬም ሊወደሱ የሚገባቸው ታላቅ የሙዚቃ እናት ናቸው። የሙዚቃን ጉዞ ገና በስድስት አመታቸው ጀምረው እየወደቁና እየተነሱ ለ94 አመታት ተከተሏት። እድሜያቸው አንድ መቶ አመት ሲደፍን ሞት ጥላውን አጠላባቸውና ሁሉንም ጉዞ አቆሙ። የአንድ ክፍለ ዘመን ሩጫቸውም ከሰሞኑ መጋቢት 18 ቀን 2015 ዓ.ም ተቋጨ። የኢትዮጵያ የረቂቅ ሙዚቃ እናት አረፉ። አፈሩን ያቅልልላቸው።

# ዓለም አቀፍ



## በኮንጎ የጣልያንን አምባሳደር ገድለዋል የተባሉ የዕድሜ ልክ እስራት ተበየነባቸው

በዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ የሚገኘው ወታደራዊ ፍርድ ቤት የጣልያንን አምባሳደርን ገድለዋል ባላቸው ስድስት ግለሰቦች ላይ የዕድሜ ልክ እስራት በይኖባቸዋል። አምባሳደሩ የተገደሉት በአውሮፓውያኑ 2021 ነው። ሉካ አታናሲዮ ሲጓዙ የነበረበት የተባበሩት መንግሥታት መኪና በደፈጣ ጥቃት ከደረሰበት በኋላ ከተገደሉ ሶስት ሰዎች መካከል አንዱ ናቸው።

መኪናውን ሲያሽከረክር የነበረው የአምባሳደሩ ሹፌር ወዲያውኑ የተገደለ ሲሆን ጠባቂያቸውም ታግቶ ነበር። ሆኖም ጠባቂያቸውን ከታጋቾች ለማስመለጥ በነበረው ዘመቻ ስህተት በመሰራቱ ሕይወቱ አልፏል። ክስተቱ የተፈጸመው የታጠቁ ቡድኖች በሚንቀሳቀሱበት በአገሪቱ ምስራቃዊ ክፍል ውስጥ ነው።


አምባሳደሩ የተባበሩት መንግሥታት የዓለም የምግብ ፕሮግራም ምገባ ፕሮግራም ለመጎብኘት የዩኔስኮ የዓለም ቅርስ ስፍራ በሆነው ቪሩንጋ ብሔራዊ ፓርክ በኩል እየተጓዙ እያለም ጥቃት እንደተፈጸመባቸው ተገልጿል። አምባሳደሩን በመግደል ከተከሰሱት ስድስት ሰዎች መካከል አምስቱ ባለፈው ዓመት ጥር ላይ በቁጥጥር ስር ውለው በመዲናዋ ኬንሻሳ በሚገኘው በንዶሎ ወታደራዊ እስር ቤት ይገኛሉ። ስድስተኛው ተጠርጣሪ በሽሽት ላይ ነው ተብሏል።

ተከሳሾቹ አሽከርካሪውን ሙስጠፋ ሚላምቦን ከገደሉ በኋላ አምባሳደሩን እና ጠባቂያቸውን ቪቶሪዮ ኢኮቫቺን በማገት ካሳ ለመጠየቅ አስቦ የነበረ “ወንጀለኛ ቡድን” አካል መሆናቸውን አቃቤ ህግ አስታውቋል። አቃቤ ህግ ጎዶ ባሙሳምባ ካባምባ ግለሰቦቹ በሞት ቅጣት እንዲቀጡም ጠይቀዋል።

ችሎቱ ጥቅምት ወር የጀመረ ሲሆን ተከሳሾቹ የእምነት ክህደት ቃላቸውን በሚሰጡበትም ወቅት ያሰቃይዋቸው እንደነበር ተናግረዋል። የተከሳሾቹ ጠበቃ ጆሴፍ አምዛቲ ለቢቢሲ እንደተናገሩት በእድሜ ልክ እስራት ላይ ይግባኝ እንደሚጠይቁ ነው።

ችሎቱ ፍትሃዊ እንዳልሆነ የገለጹት ጠበቃው ከጥቃቱ የተረፉ አራት ግለሰቦች አንዳቸውም ለምስክርነት በችሎት ላይ አለመቅረባቸውንም ጠቅሰዋል። እንደ ጠበቃቸው ገለጻ ሁሉም ተጠርጣሪዎች በሞተር ሳይክል ሹፌርነት ተቀጥረው ይሰሩ የነበሩ ሲሆን ለተጎጂ ቤተሰቦች 2 ሚሊዮን ዶላር ካሳ እንዲከፍሉ መወሰኑን የዘገበው ቢቢሲ ነው።

## በሩሲያ ለአሜሪካ ሲሰልል ነበር የተባለ አሜሪካዊ ጋዜጠኛ በይፋ ክስ ቀረበበት



አሜሪካዊው ጋዜጠኛ ኢቫን ገርሽኮቪች ላይ በይፋ ክስ መቅረቡን የሩሲያ ሚዲያዎች ዘገቡ።ጋዜጠኛው ሩሲያ ውስጥ ለዎልስትሪት ጆርናል ጋዜጣ ወኪል ሆኖ ሲሠራ ነበር። ይሁንና የሩሲያ የደኅንነት መሥሪያ ቤት ይህን አሜሪካዊ ጋዜጠኛ በስለላ ሥራ ላይ ተሰማርቶ ሳለ እጅ ከፍንጅ ይዘነዋል ይላል።

አሜሪካዊው ጋዜጠኛ ኢቫን ገርሽ ኮቪች በቁጥጥር ሥር ውሎ የነበረው ባለፈው ሳምንት ነበር። ምንም እንኳ ሞስኮ አሜሪካዊውን የያዝኩት እጅ ከፍንጅ ነው ብትልም ጋዜጠኛው ግን የተመሰረተብኝ ክስ የፈጠራ ነው ብሏል። ቀጣሪው ዎል ስትሪት ጆርናል ጋዜጠኞችን ያለምንም ማመንታት አሁኑን ይልቀቅ ሲል በይፋ ጠይቋል።

የ31 ዓመቱ ጋዜጠኛ ገርሽኮቪች በሞስኮ ለውጭ ሚዲያ ወኪል ሆነው በሚሠሩ ጋዜጠኞች ዘንድ በብርታቱ የሚታወቅ ባለሙያ ነው። በሩሲያ የቢቢሲ አርታኢ ስቲቭ ሮሰንበርግ ጋዜጠኛውን “በሙያው የታነጸ” ሲል ይገልጸዋል። ዋይት ሐውስ የርሱን መታሰር በብርቱ ያወገዘ ሲሆን በርካታ ሴናተሮችም ዜጋቸው እንዲለቀቅ እየወተወቱ ነው።

ሪፐብሊካኑ ጎምቱ እንደራሴ ሚች መክኔል እና የዲሞክራቱ አቻቸው ቸክ ሹመር በጋራ በሰጡት መግለጫ “ጋዜጠኝነት በፍጹም ወንጀል አይደለም፤ እርሱ ላይ የተመሠረተበት ደንበኛ የፈጠራ ክስ ነው፤ ሩሲያ አሁኑኑ እንድትፈታው እንጠይቃለን” ብለዋል።

እስሩን ተከትሎ የአሜሪካ ባለሥልጣናት ጋዜጠኛውን ለመጎብኘት እንዲፈቀድላቸው የጠየቁ ሲሆን የሩሲያ መንግሥት ግን ለጊዜው ያን አልፈቀደም። ይሁንና በጠበቆቹ እንዲጎበኝ ሆኗል። የሩሲያ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በበኩሉ ጋዜጠኛው እንዲጎበኝ ሁኔታዎችን እንደሚያመቻች ገልጾ ይሁንና ሩሲያ ላይ ጫና በመፍጠር አንድን ሰላይ ለማስፈታት የሚደረገው ሙከራ ‘ከንቱ የከንቱ ከንቱ ነው’ ብሏል።

ዎል ስትሪት ጆርናል ጋዜጠኞችን ባለፈው ረቡዕ ከምሥራቅ ሞስኮ 1600 ኪሎ ሜትር በምትርቀው የካተሪንበርግ ከተማ ሥራ ላይ ሳለ ከደወለልን በኋላ ነው ደብዛው የጠፋብን ይላል። የአሜሪካ ባለሥልጣናት በበኩላቸው ጋዜጠኛውን የግል ሾፌሩ አንድ ሬስቶራንት ካደረሰው በኋላ ስልኩ እንደተቋረጠና ከዚያ በኋላ በቁጥጥር ሥር ሊውል እንደቻለ ተናግረዋል።

የሩሲያ ደኅንነት እንደሚለው ደግሞ ይህ አሜሪካዊ ጋዜጠኛ ሕገ ወጥ ሥራ ሲሠራ እንደነበረና በአሜሪካ የተሰጠውን የስለላ ተልእኮ ሊፈጽም ሲል እጅ ከፍንጅ እንደተያዘ ይገልጻሉ። የአገር ምሥጢር የሆኑ መረጃዎችን ከሩሲያ መከላከያ ኢንተርፕራይዝ ሲለቅም ነበር ብለዋል።

ከትናንት ወዲያ ዓርብ ጋዜጠኛው በሞስኮ ሌፍሮቶፍ አካባቢ ምድብ ችሎት የቀረበ ሲሆን እስከ ግንቦት መጨረሻ እስር ቤት ቆይቶ ምርመራው እንዲቀጥል ትእዛዝ ተሰጥቶበታል። አንድ በስለላ ተግባር የተሰማራ ሰው በሩሲያ ሕግ ጥፋተኛ ሆኖ ሲገኝ እስከ 20 ዓመት ጽኑ እስር እንደሚቀጣ ቢቢሲ ዘግቧል።


## የጨረታ ማስታወቂያ
## CN/NCB/24/2015

ኮሜርሻል ኖሚኒስ ኃ/የተ/የግል ማህበር ለሚሰጣቸው የተለያዩ አገልግሎቶች የኮስትና ትመና (Consultancy Service to Develop Cost and Pricing manual) በውጭ አማካሪዎች በግልጽ ጨረታ ለማስጠናት ይፈልጋል፡፡

በመሆኑም ተጫራቾች የታደሰ የንግድ ፈቃድ፣ በጨረታ ላይ መሳተፍ እንደሚችሉ የሚገልጽ ደብዳቤ፣ በአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ የተመዘገቡትን ማስረጃ፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ የምዝገባ ሰርተፍኬት የጨረታ ማስከበሪያ ሲ.ፒ.ኦ እና የዕቃው ዝርዝር መግለጫ በተለየ በሰም በታሸገ ፖስታ እንዲሁም ዕቃዎቹን የምታቀርቡባቸውን ዋጋ በተለየ በሰም በታሸገ ሁለተኛ ፖስታ በማድረግ እንድትወዳደሩ ይጋብዛል፡፡

የጨረታ ዶክመንቱን ቦሌ ደንበል የገበያ ማዕከል ጀርባ በድርጅቱ ዋና መ/ቤት ህንፃ 5ኛ ፎቅ የግዢ ዋና ክፍል ብር100.00 በመክፈል ከሰኞ እስከ አርብ (ጠዋት 2፡00-6፡00 እንዲሁም ከሠዓት 7፡00-11፡00) ማግኘት ይቻላል፡፡ የጨረታ ማስከበሪያ ብር 100,000 በባንክ በተረጋገጠ ሲ.ፒ.ኦ. (የባንክ ጋራንቲ ማቅረብ የሚቻለው ከዋናው መ/ቤት ብቻ ነው) ከመጫረቻ ዶክመንት ጋር መቅረብ ይኖርበታል፡፡ ተጫራቾች የመጫረቻ ዶክመንታቸውን ከላይ በተጠቀሰው አድራሻና የሥራ ሰዓት በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ውስጥ እስከ ሚያዝያ 17 ቀን 2015 ዓ.ም 4፡00 ድረስ ማስገባት ይችላሉ፡ ጨረታው በዚሁ ዕለት በ 4:30 ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በድርጅቱ የመሰብሰቢያ አዳራሽ ይከፈታል ያሸነፈው ተጫራች የዕቃዎች ርክክብ የሚደረግበት ቦታ ገርጂ የድርጅቱ ግምጃ ቤት ይሆናል ከላይ የተጠቀሱትን መስፈርቶች ያላሟላ ተጫራች ያለተጨማሪ ማስታወቂያ ከውድድሩ ውጪ ይደረጋል፡፡

ድርጅቱ ጨረታውን በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

ኮሜርሻል ኖሚኒስ ኃ.የተ.የግ ማ
ቦሌ ደንበል የገበያ ማዕከል ጀርባ በድርጅቱ ዋና መ/ቤት ህንፃ 5ኛ ፎቅ
ስልክ ቁጥር 011-1-569992

**ኮሜርሻል ኖሚኒስ ኃ/የተ/የግል ማህበር**



ቡና ባንክ BUNNA BANK የባለራዕዮች ባንክ

## Invitation to Local Competitive Bid -no.- BB/007/2023

Bunna Bank S.C. (BB) invites all interested and eligible bidders to participate on the bid for the supply of Planner Book (Agenda) for 2023/24 Fiscal Year.

| S/N | Description of items | Qty | Bid Closing Date | Bid Opening Date |
|---|---|---|---|---|
| 1. | -Executive Agenda | 1000 pcs | April 25 ,2023 After noon at 3:00PM | April 25 , 2023 Afternoon at 3:20PM |
| | -Medium Size Agenda | 12000 pcs | | |

Instructions:

1. A complete set of bidding documents shall be obtained from the office of Procurement Management Directorate located at BB's Head Office, 5th floor (around Bole road next to Wello Sefer roundabout up on producing receipt of non -refundable fee birr 200.00 (Two Hundred birr only) by depositing to Account no 1019601000609 at Bunna Bank branch, starting from April 11, 2023 to April 26, 2023 during office hours.
2. Bid should be accompanied by an unconditional bid security amount stated in the bid documents in the form of Bank guarantee or CPO from recognized financial institutions.
3. Bid opening shall be held as per stated schedule at board room in the presence of bidders and /or their legal representatives who wish to attend.
4. The Bank reserves the right to accept or reject fully or partially at its own discretion.

Tel: 011-158-08-69/0111-26-21-44

**Bunna Bank**
"Bank of the Visionaries"


# ስፖርት





## የዓለም አትሌቲክስ- በአራት አስርት ዓመታት

**ብርሃን ፈይሳ**




እኤአ ከ1990ዎቹ መጀመሪያ አንስቶ የእሱን ያህል በተደራራቢ ክብር የተንቆጠቆጠ አትሌት ማግኘት ያዳግታል፡፡ በዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና መድረክ ብቻ 4 የወርቅ፣ 2 የብር እና 1 የነሃስ በጥቅሉ 7 ሜዳሊያዎችን በማጥለቅ የአትሌቲክስ ቤተሰቡን አጀብ አሰኝቷል። አስደማሚው የዚህ አትሌት ብቃት በተለይ በ10ሺ ሜትር ሲሆን፤ በ5ሺ ሜትር ካገኘው አንድ የብር ሜዳሊያ በቀር ሁሉም የተመዘገቡት በዚሁ ርቀት ነው፡፡ የዓለም አትሌቲክስም በዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና የ40 ዓመት ታሪክ ከ1993-2001 የኢትዮጵያዊውን ጀግና አትሌት ሻለቃ ኃይሌ ገብረስላሴን ያህል በድል የደመቀ የለም ሲል ምስክርነቱን ይሰጣል፡፡

በአትሌቲክስ ስፖርት ትልቁ፣ የኦሊምፒክን ያህል በድምቀት የሚካሄደውና በስፖርት ቤተሰቡም ዘንድ በጉጉት የሚጠበቀው የዓለም ቻምፒዮና መካሄድ ከጀመረ በተያዘው ዓመት አራት አስርት ዓመታትን ይደፍናል፡፡ የዓለም አትሌቲክስም ይህንን ክብረ በዓል ከአምስት ወራት በኋላ በሃንጋሪ ቡዳፔስት በሚካሄደው የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና ያከብራል፡፡ እአአ ከ1983 ጀምሮ ባለፉት ዓመታት በርካታ አስደናቂና አስገራሚ የአትሌቲክስ ሁነቶች ታይተዋል፡፡ በዓለም አቀፉ ተቋም የክብር መዝገብ በልዩ ሁኔታ ተመዝግበው ከሚገኙት መካከልም፤ በ1980ዎቹ የጦር ወርዋሪዋ አትሌት ቲና ሊላክ ትውስታ፣ በ1990ዎቹ የሻለቃ ኃይሌ ገብረስላሴ የ10ሺ ሜትር ርቀት ገድል እንዲሁም ከ2ሺ ወዲህ የዓለም ፈጣን ሰው የተባለው ዩሴን ቦልት ተጠቃሾቹ ናቸው፡፡

ከዚህ ውድድር እአአ እስከ 2022 ድረስ በተካሄዱ 18 የዓለም ቻምፒዮናዎችን የዓለም አትሌቲክስም ሆነ የስፖርቱ ቤተሰብ ስፖርቱ (የሩጫ፣ ውርወራ፣ ዝላይ እና እርምጃ ስፖርቶች) የደረሰበትን የእድገት ደረጃ በቀላሉና በግልጽ ሊመለከት ይችላል፡፡ በቡዳፐስቱ ቻምፒዮና ላም ከውድድር ባሻገር እንዲህ ያሉ ጉዳዮች በጉልህ ለዕይታ የሚቀርቡ ሲሆን፤ ሌሎች መርሃ ግብሮችም እንደሚከናወኑ ማህበሩ ከወዲሁ አሳውቋል፡፡ ከእነዚህ መካከልም የስፖርት ቤተሰቡ ድምጽ በመስጠት የሚሳተፍበት የምርጥ 10 ሴት እና 10 ወንድ ምርጥ አትሌቶች ምርጫ አንዱ ነው፡፡ ለዚህም ዓለም አቀፉ ማህበር ዘርፈ ብዙ ዝግጅት በማድረግ ላይ እንደሚገኝም በፕሬዚዳንቱ ሰባስቲያን ኮ በኩል አሳውቋል፡፡

የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና በአንጻራዊነት ከሌሎች ቻምፒዮናዎች ያነሰ ዕድሜን ያስቆጠረ ውድድር ነው ለማለት ይቻላል፡፡ ለዚህም ምክንያት የሆነው ኦሊምፒክ ላይ የሚካሄዱት የአትሌቲክስ ውድድሮች በማህበሩ በኩል ልክ እንደ ዓለም ቻምፒዮና የሚቆጠሩ ስለነበረ ነው፡፡ በዚህም መሰረት እአአ ከ1913 ጀምሮ ባሉት 50 ዓመታት በአራት ዓመት አንዴ የኦሊምፒክ መካሄድን ተከትሎ ታላቁ ውድድር ይካሄድ ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት የማህበሩ አባል የሆኑ ሀገራት የራሳቸውን ትንንሽ ቻምፒዮናዎች ያዘጋጁ ነበር፤ ይህ ሁኔታ እያደገና እየሰፋ በመጣ ጊዜም ማህበሩ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከኦሊምፒክ ተለይቶ የሚካሄድ ውድድር መኖር እንዳለበት በማመኑ እአአ በ1970ዎቹ ጀምሮ ሃሳቡ መብላላት ጀመረ፡፡

የሃሳቡ ተግባራዊነት ላይ እምነት በመጣሉም እአአ በ1983 በፊንላንድ ሄልሲንኪ ላይ የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና ለመጀመሪያ ጊዜ ሊካሄድ ቻለ፡፡ በወቅቱም ከ153 ሀገራት የተወጣጡ 1ሺ333 አትሌቶች የተካፈሉ ሲሆን፤ በ41 የውድድር ዓይነቶችም ተካሂደዋል፡፡ እአአ እስከ 2022ቱ የዩጂን ዓለም ቻምፒዮና ድረስም ውድድር የሚካሄድባቸው የስፖርት ዓይነቶች እየተጨመሩ 49 የግል እና የቡድን ውድድሮች ሊደርስ ችሏል፡፡ ባለፉት ዓመታት በተካሄዱ ቻምፒዮናዎችም 35 የዓለም ክብረወሰኖች ተመዝግበዋል፤ ከእነዚህ ውስጥም 18 የሚሆኑት በወንድ አትሌቶች፣ 15ቱ በሴት አትሌቶች እንዲሁም 2ቱ በድብልቅ ሪሌ ናቸው፡፡

በመጀመሪያው የሄልሲንኪው ቻምፒዮና አንድ ክብረ ወሰን በ400 ሜትር ሲመዘገብ፤ በጀርመኗ ስቱትጋርት በተደረገው 4ኛው የዓለም ቻምፒዮና ደግሞ 5 የዓለም ክብረወሰኖች ነበሩ የተሰባበሩት፡፡ እጅግ ፈጣኑ ጃማይካዊ አትሌት ዩሴን ቦልት ደግሞ በ100ሜትር፣ 200ሜትር እንዲሁም በ400ሜትር ተደራራቢ ክብረወሰኖችን በመሰባበር ወደር ያልተገኘለት አትሌት ነው፡፡




## ስራ ፈጣሪዋ ታዳጊ ዘምዘም

**በስጦታቸው ልዑልሰገድ**



ሰላም ልጆች እንዴት ናችሁ ሳምንቱ እንዴት አለፈ? ጎበዝ ልጅ ሁሌ ሳምንቱን የሚያሳልፈው በትምህርት ነው። እናንተም ጎበዝ ተማሪ ስለሆናችሁ ሳምንቱን ያሳለፋችሁት በትምህርት እንደሆነ እርግጠኛ ነኝ፡፡ ጎበዝ ተማሪ የጊዜን ጥቅም በሚገባ ያውቃል ስለዚህ ያለውን ጊዜ በአግባቡ በመከፋፈል ይጠቀማል፤ ማንበብ ባለበት ሰዓት ያነባል መጫወት ባለበት ሰዓት ይጫወታል መማር ባለበት ሰዓት ደግሞ ይማራል፡፡ እናንተም ሰዓታችሁን እንደዚህ በስርዓት ከፋፍላችሁ እንደምትጠቀሙበት አምናለሁ፡፡

ልጆች ስራ የአንድ ሰው ጠንካሬ መገለጫ መሆኑን ታውቃላችሁ? ስንፍናን ያሸነፈና ሁልጊዜ ሳይሰለች፤ በሚገጥሙት ችግሮች ተስፋ ሳይቆርጥ፤ በተስፋ ተሞልቶ እንደሚያልፈው እርግጠኛ በመሆን ስራውን በአግባቡና በታታሪነት የሚሰራ ሰው የጥንካሬ መገለጫ ምሳሌ ነው። ታዲያ ይህንን ለማዳበር ከልጅነት ጀምሮ የስራ ባህልን ማሳደግ በጣም አስፈላጊ እና ሊታሰብበት የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡ ልጆች ዛሬ የማስተዋውቃችሁ በታታሪነቷ እና በስራ ወዳድነቷ እውቅና ያገኘችውን ጠይሟን እና የተስፋ ጮራ ከፊቷ የሚንፀባረቀውን ታዳጊ ዘምዘም ከድርን ነው፡፡

ልጆች ዘምዘም በሻሸመኔ ከተማ የምትኖር ሸንኮራ በመሸጥ ቤተሰቧን የምትደግፍ የአስራ አራት አመት ታዳጊ እና የአምስተኛ ክፍል ተማሪ ናት፡፡ ልጆችዬ ዘምዘም የሸንኮራ መሸጥ ስራዋን የጀመረችበት አጋጣሚ ምን መሰላችሁ፤ ከዕለታት ባንዱ ቀን ዘምዘም እንደተለመደው ከሰፈር እኩዮቿ ጋር ከትምህርት ቤት ተመልሰው ሰፈር ውስጥ ሰብሰብ ብለው በመጫወት ላይ ሳሉ ሸንኮራ የሚሸጡ ሰዎች ወደ እነሱ ይመጣሉ፤ ዘምዘም ታዲያ ሸንኮራውን ገዝታ ከመብላት ይልቅ ቀልቧን የሳበው የሰዎቹ ሸንኮራ የመሸጥ ስራ ነው፡፡ ወዲያው እነሱ የሚሰሩትን ስራ ለምን አልሰራም የሚል ሃሳብ ወደ አዕምሮዋ መመላለስ ጀመረ፤ ሰዎቹ ርቀው ከመሄዳቸው በፊትም ከምትሸጡት ሸንኮራ ላይ በዱቤ ስጡኝና ሽጬ እከፍላችኋለሁ በማለት ትጠይቃቸዋለች። ነገር ግን ሰዎቹ ሰርታ መክፈል መቻሏን ባለማመናቸው ሸንኮራውን ሊሰጧት አልፈለጉም፡፡

ልጆችዬ ዘምዘም ግን ተስፋ አልቆረጠችም ወደ እናቷ በመሄድ የሸንኮራ መሸጥ ንግድ መጀመር እንደምትፈልግና ለመነሻ የሚሆናትን የሸንኮራ አገዳ ሰዎቹን አነጋግራ እንድትቀበልላት ትጠይቃታለች፡፡ የዘምዘም እናትም የልጃቸውን ፍላጎት ለማሟላት ወደ ሰዎቹ በመሄድ የሸንኮራ አገዳውን ሰጥተዋት ንግዱን እንድትጀምር ይጠይቁላታል፤ ሰዎቹም ዘምዘም በእናቷ በኩል ስለመጣችባቸው እውነትም የመስራት ፍላጎት ቢኖራት ነው በማለት የሸንኮራ አገዳውን በዱቤ ሰጧት፤ ዘምዘምም የሸንኮራ መሸጥ ስራዋን በዱቤ በተቀበለችው የሸንኮራ አገዳ ሀ ብላ ጀመረች፡፡ ሸጣ ከምታገኘው ላይ እዳዋን እየከፈለች የምታገኘውንም ትርፍ ማጠራቀሙን ተያያዘች፡፡ ከጥቂት ጊዜ በኋላ እዳዋን ከፍላ ጨርሳ ባተረፍችው ብር ሸንኮር እያመጡ የሚሰጧት ሰዎች ሸንኮራውን ከሚያመጡበት ቦታ ድረስ በመሄድ ሸንኮራ አምጥታ መሸጥና ከበፊቱ የተሻለ ትርፍ ማግኘት ጀመረች። ዘምዘም ታዲያ ሸንኮራ ሸጣ በምታገኘው ገንዘብ እራሷን ብቻ ሳይሆን ወላጅ እናቷንም ታግዛለች፡፡

ልጆች ዘምዘም ወደፊት ትልቅ ልጅ ስትሆን ምን መሆን እንደምትፈልግ ታውቃላችሁ? መሐንዲስ መሆን ነው የምትፈልገው፡፡ በምህንድስና ሙያ ተመርቃ በሻሸመኔ ከተማ ውስጥ በስሟ የሚጠራ ትልቅና ታዋቂ ሆቴል መክፈትና ለእናቷም ትልቅ የመኖሪያ ቤት መስራት ትፈልጋለች፡፡ ልጆች ዘምዘም ይህንን ስራ ለመጀመር ያነሳሳት ሃሳብ ምን መሰላችሁ፤ ለፍታና ጥራ ያሳደገቻትን እናቷን ከድህነት ኑሮ አላቃ ነገ ጥሩ ኑሮ እንድትኖር ለማድረግ ስለምትፈልግና ከሷ በፊት የተወለዱ ታላላቆቿ ወላጅ እናታቸውን ምንም ሲረዱ አይታ ስለማታውቅ እሷ ግን እንደነሱ ላለመሆንና የእናቷን ልፋት ላለመርሳት በመፈለግ ካሁኑ ከልጅነት ጊዜዋ ጀምራ እናቷን ስራ እየሰራች በምታገኘው ገቢ ለማገዝ በማሰብ ይህንን ስራ ጀመረች፡፡

ልጆች ዘምዘም በአጠቃላይ የሸንኮራ ሽያጭ ሥራውን የጀመረችው በብዙ ነገር ስትቸገር የምታያትን እናቷን ካሁኑ ከልጅነት ጊዜዋ ጀምራ ስራ እየሰራች በምታገኘው ገቢ ለማገዝ በማሰብ ጀመረች፡፡

ልጆችዬ ዘምዘም ሰርታ የምታመጣውን ገንዘብ ማባከን አትፈልግም፡፡ ስራ ሰርታ ለፍታ የምታመጣው ገንዘብ ያለአግባብ እንዲባክን ስለማትፈልግ ከቀን ገቢዋ ላይ በየቀኑ ሃምሳ ብር ትቆጥባለች፡፡ በምታገኘው ገቢ ለራሷ የሚያስፈልጓትን ነገሮች በማሟላት ባሻገር እናቷንም በቻለችው ሁሉ ትደግፋለች፡፡

ልጆችዬ ስራ እንደሚያስከብር እና ዝቅ ብሎ ስራ ሳያማርጥ ጠንክሮ የሰራ ሰው ሁልጊዜም ቢሆን የሚከበርና ለጥንካሬውን እውቅና የሚሰጠው ይሆናል፡፡ ዘምዘምም ታዲያ ታታሪነቷ ከፍ አድርጎ በሰዎች ፊት ቀና ብላ በኩራት እንድትቆም አደረጋት እንጂ አላሳፈራትም፡፡ በቅርቡ ከኦሮሚያ ክልል ፕሬዝዳንት አቶ ሽመልስ አብዲሳ እጅ ታዳጊ ስራ ፈጣሪ በሚል የእውቅና የምስክር ወረቀት ወስዳለች፡፡ ልጆች በርትተን ቤተሰቦቻችንን በመርዳት እና ትምህርታችንን በመማር ትልቅ ደረጃ መድረስ ይኖርብናል ስትል መልዕክቷን ታስተላልፋለች፡፡

ልጆች ከዘምዘም ብዙ እንደተማራችሁና ወደፊትም እንደሷ ጠንካራና ጎበዝ ስራ ወዳድ እንደምትሆኑ እርግጠኛ ነኝ፡፡ ለዛሬ የዘምዘምን መልእክት ተግባራዊ እንድታደርጉ አደራ በማለት ፅሁፌን በዚሁ ላብቃ ሳምንት በሌላ አስተማሪ ፅሁፍ እስክንገናኝ መልካም የትምህርት ሳምንት ይሁንላችሁ።